# ጂሃድ

## (የእስልምና ጦርነት በሃይማኖቶች ላይ?)

## አክራሪነት እና ሽብር

ተርጓሚና አዘጋጅ

አብይ ጣሰው

(tassewabiy2@gmail.com)

ርዕስ፦ ጂሃድ፣ አክራሪነትና ሽብር

ተርጓሚና አዘጋጅ፡ አብይ ጣሰው

ከቨር ዲዛይን፡ ዩስራ አሕመድ

(yusra_ao@yahoo.com)

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጲያ

2007 እንደ ኢትዮጲያ አቆጣጠር





ማውጫ ገጽ

የተርጓሚው ማስታወሻ 5

ጂሃድና ሃይማኖት
ዶ/ር ሪዛ አስላን 11

ጂሃድና ሽብር
ፕ/ር ጆን ኤስፒሲቶ 48

አክራሪነትን የሚፈጥረው ምንድን ነው?
ፕ/ር ጆን ኤስፒሲቶ እና
ያስሚን ሞጋሂድ 69

ከ"ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው" ባሻገር
ፕ/ር ያሚድ ሳፊ እና
ዶ/ር አቡ አል ፋድል 87

## የተርጓሚው ማስታወሻ

ቶማስ ሆብስ ሌቭያታን በሚለው ሥራው፣ ጠንካራ የሚቆጣጠረው አካል ከሌለ፣ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ወደ ብጥብጥና ረብሻ የተዘነበለ ነው ሲል ይከራከራል። የሰውን ልጅ ተፈጥሮ በተመለከተ የቶማስ ዕይታ ወደ እውነታው የቀረበ ይመስላል። ብጥብጥና ረብሻ የሰው ልጆች አንድ እውነታ ነውና።[1] ስቶይሲንገር የመስኩ ምሁራን ጦርነት አይቀሬም እንደሆነ እንደሚከራከሩ ፅፏል።[2] ቶማስ ሆብስ ሃሳብ ያቀረበለት ጠንካራ አካል ተጠያቂነት የሌለበት መንግስት ነው። ነገር ግን መንግስታት የሰውን ነፍስ የማጥፋት ህጋዊ ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፤ አጅግ አሰቃቂ ጦርነቶችን አካሂደዋል። አቅም ያላቸው የሰውን ዘር በጅምላ የሚጨርስ የኒውክሌር ቦምብ ታጥቀዋል። አሁንም መንግስታት ለጦር መሣሪያዎች ግዢ እና ብልፅግና የሚመድቡት ባጀት ጭንቅላት ያዞራል ብል አጋንኜው ይሆን?[3]

በሰው ልጆች ዕለታዊ ውጫዊና ውስጣዊ ህይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በማድረስ ረገድ ሃይማኖት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። ሃይማኖቶች በበኩላቸው የፍቅር፣ መተሳሰብና ሰላም መገኛ ናቸው ይባላል። ነገር ግን ቢያንስ በአሁን ሰዓት እያየነው ባለነው እውነታ ነገሩ እንዲያ አይደለም። ሃይማኖቶች የሚጠበቅባቸውን ማህበራዊ ሃላፊነት እየተወጡ አይደለም። ሃይሞኖተኞች በበዛባቸው ሃገራት ማህበራዊው ቀውሱ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም አገራት በህዝብ እና መልካም ዕሴቶች ስም ወደ ጦርነት እንደሚገቡ ሁሉ ሰዎችና ስብስቦችም በሃይማኖት ስም ግጭት ውስጥ በተደጋጋሚ ገብተዋል። ይህ የሚጠበቅ ነው፤ የትኛውም ሃይል አንድ

[1]www.huffingtonpost.co.uk/2014/11/religion-war-cause-responsible-evidence_n_6156878.html፣ በ11/3/2007 የወረደ

[2]Stoessinger, John G. (2001). Why Do Nations Go To War, BEDFORD/ST. MARTINE, ገፅ xv.

[3] Stockholm International Peace Reséarch Institute በ2013 ባወጣው ዓመታዊ መጽሐፉ የዓለማችን ወታደራዊ በጀት 1.756 ትሪሊዮን ዶላር እንደደረሰ ፅፏል። ለዝርዝር መረጃ በተጨማሪ www.globalissues.org. ይመልከቱ፡

እርምጃ ሲወስድ መጥፎ ነገር አስቤ ነው አይልም። ጣሊያን አቡነ ጴጥሮስንና ሲገድል፣ ሽህ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅን ሲያስር ዛድቅ ሰው ገደልኩ፣ አሰርኩ አይደለም ያለው ሽብርተኛ እንጂ። ሱዩስ ሪድሊ እንደተመለከተችው ሃይማኖቶች በውስጣቸው የትክክለኛነት (ኦርቶዶክሲ) ፅንሰ ሃሳብ ስላለ፣ ፖለቲከኞች የእኛንና እነርሱን አስተሳሰብ በቀላሉ ማስረፅ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል።[4] በዚሁ መጣጥፏ ሪድሊ ሃይማኖቶች በፖለቲከኞች የሚጠለፉት ከሕይወት የበለጠ አምሳሎችና ዕሴቶች ማቅረብ ስለሚችሉ ነው።[5]

የሽብር ነገር ሲነሳ በማንኛውም ሰው ጭንቅላት ውስጥ አብሮ የሚመጣው ነገር እስልምና ወይም ከእስልምና ጋ የተያያዙ መጠሪያ ያላቸው ስብስቦች ብቻ ናቸው። መሬት ላይ ያለው እውነታ እንዲያ ባይሆንም (በሜንማር ቡድሃዎች፣ በስሪላንካ የቀድሞው የታሚል ታይገር ሴኩላሪስት ስብስብ፣ በአውሮፓ የባስክ ተገንጣይ እንስቃሴ፣ በዩጋንዳ ክርስቲያናዊው የሎርድ ረዚስታንስ አርሚ፣ በአሜሪካ አክራሪ የክርስቲያን ቡድኖች) ለመካከለኛው ምስራቅ ሥሡ ፖለቲካዊ ሁነት እና ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ምስጋና ይድረሳቸውና የሰው ጭንቅላት ውስጥ የተሳለው የሃይማኖቱና ሽብር ቁርኝት ስዕል ደስ አይልም።

ጦርነት የሁሉም ሃይማኖቶችና እምነት የለሾች ርዕዮተ-ዓለም አቀንቃኞች እውነታ ቢሆንም እስልምና በተለየ ሁኔታ ጥያቄ ይቀርብበታል። ኤቴስቶችም ቴዬስቶችም እንዲሁ እስልምና ላይ ጣታቸውን ይቀስራሉ። ያኤቴስቶቹ ለየት የሚያደርገው ሌሎችም ሃይማኖቶች "በጦረኝነት" ረገድ ልዩነት የላቸውም ማለታቸው ነው።[6] ቢያንስ ቢያንስ በከፊል ለእውነት የቀረቡ ናቸው። ሆኖም ግን ጦርነት የሃይማኖተኞች ዕውነታ ሳይሆን የሰው ልጆች ዕውነታ ነው።[7] እምነት የለሾቹ ኮሚኒስቶች በሩሲያ፣ ቻይና፣ ሃንጋሪ፣ አልባኒያ አሰቃቂ ግፍ ሰርተዋል። ዘመነኛዋ ኤቴስቷ ጃፓን እንኳ ጎረቤቷ ቻይና የጦር ሃይሏን ከማፈርጠሟ ጋ በተያያዘ እርሷም ወደዚሁ እንደገባች የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።[8]

የዓለማችንና የአገራችን ታሪክ በወፍ በረር ላነበበ ሃይማኖቶች በጦርነት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ሃይማኖት እንዳሁኑ የግል ሳይሆን "ዜግነትን ጭምር የሚወስን" ነበር። መንግስቱ ከተቀበለው ሃይማኖት ውጪ ያሉ እንደ ሌላ አገር ወይም ሁለተኛ ዜጋ መቆጠራቸውና በዚህም አሰቃቂ በደል እንደደረሰባቸው ለማወቅ ብዙም አስቸጋሪ አይደለም። አሁን ግን ሃይማኖት ድሮ የነበረውን መንግስታዊ ገናናነት አጥቷል።

ምንም እንኳ ሃይማኖት መንግስታዊ ክብሩ አሁን ባይኖርም ፖለቲካዊ ገናናቱ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሷል። በዚህም የተነሳ አንዳንዶች ስለ ስልጣኔዎች ግጭት እያወሩ ነው። በርግጥ አሁን መሬት ላይ እያየነው ያለነው ሁነት ለስልጣኔዎች ግጭት መንደርደሪያ ነውን?

---

[4] www.huffingtonpost.co.uk/2014/11/religion-war-cause-responsible-evidence_n_6156878.html፣ በ11/3/2007 የወረደ

[5] ዝኒ ከማሁ

[6] እንደ ፕሮፌሰር ቶም ሶረል (ዋርዊክ ዩኒቨርስቲ) ምልከታ አዲስ ትውልዶቹ ኤቴይስቶች ራሽናሊቲን እና ሳይንስን እናራምዳለን ስለሚሉ (ይቀጥላል) (የቀጠለ) ለጦርነቶች ምክንያት እንደሆኑ የሚታመኑትን ከሕይወት የገዘፉ አምሳሎችን ማቅረብ ስለማይችሉ የጦርነት መንስኤ ሊሆኑ አይችሉም። በተጨማሪም ኤቴስቶችን ሊያሰባስብ የሚችል፣ ምናልባት ለሃይማኖትካላቸው ጥላቻ ውጪ የጋራ ሃሳብ የላቸውም። ነገር ግን ለሃይማኖተኞች የጥቃት አደጋ ከተጋለጠ በአንድነት አሰባስቧቸው ጦር የማያስመዝዛቸው ነገር የለም። በተጨማሪም ሰው በማይረባ ነገር ሁሉ የመጋጨት ነገር አለበት። (ምንጭ፡ ዝኒ ከማሁ)

[7] ዝኒ ከማሁ፣ Stoessinger, John G. (2001). Why Do Nations Go To War, BEDFORD/ST. MARTINE ·

[8] ጦርነትን የመሠለ ውስብስብ የሰው ልጅ ሁነት ጥቁርና ነጭ በሆነ አረዳድ በአንድ ምክንያት ላይ መደፍደፍ የዋህነት ነው። ፍጹም የሃይማኖት ጦርነት የሚባሉት እንኳ በውስጣቸው ፖለቲካዊ ግብ አላቸው። አይኤስአይኤስ የኸሊፋ ሥርዓት ለማምጣት እዋጋለሁ ይላል። ኸሊፋ ግን ፖለቲካዊ ተቋምም ጭምር ነው። ሌላው አሶስዬትድ ፕሬስ የየመኑ አልቃይዳ አይኤስአይኤስን ያወገዘበትን ዘገባ ይዞ ወጥቶ ነበር። አልቃይዳ ተቃውሞውን ያቀረበው በከፍተኛ ሁኔታ የተፅእኖ'ሆን ክልል አስፋሁ ብሎ ነው። አልቃይዳ እንዲሁ ሃይማኖታዊ ድርጅት ነው ተብሎ የሚታሰበው። (ምንጭ፡ www.huffingtonpost.com/../al-qaeda-yemen.isis_n_61985... በ13/3/2007 የወረደ)

ሙስሊሞች የቱን ያህል ሃይማኖታቸው የሰላም እንደሆነ ቢናገሩም ሌሎች ሃይማኖቱንና ተከታዮቹን በጥርጣሬ መመልከታቸው ያደባባይ ምስጢር ነው። እስልምና ክርስትናንና ጁዳይዝምን ሊያጠፋ የመጣ ሃይማኖት ነውን? ሙስሊሞች በሃይማኖታቸው ክርስቲያን የገደለ ገነት ይገባል ተብለው ታዘዋልን? በቅዱስ ቁርአን ውስጥ ያሉት ስለ ግድያ የሚያወሱ የሰይፍ አንቀፆች የሚባሉትስ? በሙስሊሙ ዓለም የነገሰው ረብሻና ብጥብጥ መንስኤውና መግፍኤው ምንድነው? እሺ፤ እስልምና የሰላም ሃይማኖት ከሆነና እነዚህ አሻባሪዎች ብዙሃኑን የማይወክሉ ጥቂቶች ከሆኑ፣ ለምን በሃይማታቸው ስም የሚደረገውን አሰቃቂ ተግባር በግልጽ አይቃወሙም?

ጥያቄዎቹ ምክንያቲዊ ሆኑ አልሆኑ፣ ከሰዎች እውነተኛ ሃሳብ የመነጩ ናቸው። ምላሽ ያስፈልጋቸዋል። ከነዚህ ውስጥ እና መሰል ሌሎች ጥያቄዎች ሐሰን ታጁ *ሰይፉን ፍለጋ* በሚለው መፅሐፉ ለመመለስ ሞክሯል። መፅሐፍ ቅዱስን ያነበበ ማንኛውም ሰው ቅዱስ ቁርአን ውስጥ ለምን የሰይፍ አናቅፅት ኖሩ ብሎ መውቀስ የለበትም። በብሉይ ኪዳን የተገለፀው አምላክ የምድራዊ ጉዳይ እንደሚያሳስበው ምንም ጥርጥር የለውም። "በአምላክ መሪነት እስራኤላውያን ብዙ ጦርነቶች አካሂደዋል።" ሳምሶምም የተላጨው ፀጉሩ ሲያቀመቅምለት የሕንጻዎቹን ምሰሶ ነቅንቆ እራሱንና ሌሎችን አጥፍቷል።[9]

---

[9] እንደ ሰይድ ሁሴይን ናስር ምልከታ አንዳንድ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እስልምናን እና ነቢዩን በተመለከተ ላላቸው ወኸርንብር እንደኛው ምክንያት እርሳቸውን ከኢየሱስ ወይም ቡዳሐ ጋ በትይዩ ለመመልከት መሞከራቸው ነው። "የነቢዩን ትክክለኛ ሰብእና ለመረዳት፣ እርሳቸው ከኢየሱስም ሆነ ከቡድሃ ጋር መነፃፀር የለባቸውም። ምክንያቱም የኢየሱስና የቡድሃ መልዕክት በዋነኛነት የሚመለከተው ፃድቆችን እና የኋላ ኋላ የማህበረሰብ መገለጫ በሆነው ብህትውና ላይ ማህበረሰብን የመሰረቱትን ነው።፡ ነቢዩ መነጻጸር ካለባችው በነበራቸው የ"ንጉስነት" እና "ነቢይነት"- ሰዎችን በዚህና ለመጪው ዓለም የመምራት- ሚና በብሉይ ኪዳን ከተወሱት ንጉስ ነቢያት ዳዊትና ሰለሞን፣ በተለይ ከአብረሃም ወይም ከአብርሃማዊ ትውፊት ወጥቶ ምሳሌ መጥቀስ ካስፈለገ ከሂንዱይዚም ራማ እና ክሪሽና ጋ ነው። በማህባራታ እና ራማናያ እንደሰፈረው እነዚህ ሰብእናዎች የአምላክ መገለጫዎች (avatars) ብቻ አልነበሩም፤





ዞሮ ዞሮ ሰው በብዙ ጭንቀቶች በተወጠረበት በአሁኑ ወቅት የፍቅርና የሰላም ምንጭ ሊሆኑ የሚገባቸው ሃይማኖቶች የዕልቂት ምንጭ ሊሆኑ አይገባም። ሃይማኖት በመርሁና በተከታዮቹ እንደሚከፈል ይታወቃል። የማርታ ፍለጋ ፅንሰ ሃሳቡም ይህ ይመስለኛል- ተከታዩ ከመርሁ ሲያፈነግጥ ለጉድለቱ አምላኩን ምህረቱን እንዲለግሰው መማፀን። አንዴ መርሁ ከታወቀና ሰውየው ለምን ከመርሁ እንዳፈነገጠ ምክንያቱን[10] ከተረዳን፣ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሙስሊሞች ሃሳባቸውንና ጭንቀታቸውን ከተረዳን ነባራዊውን ሁኔታ በተሟላ መልኩ ለመረዳት ያግዘናል። ሙስሊሞች ከሌሎች ሰዎች በምንም መልኩ አይለዩም። እናም መፈታት ያለበትም ችግር ካለ ለውይይት በር ይከፍታል። የመፅሐፏ ዓላማም ይህ ነው።

ይህች መፅህፍ እናንተ ጋ እንድትደርስ ያላሰለሰ እርዳታቸውንና ጥረታቸውን ለለገሱኝ ሁሉ፣ በተለይ አሪፍ አብዱልቃድርን አመሰግናለሁ። ለመፅሐፏ መጠንሰስ ጓደኛዬ "ኮፒ" ምክንያት ስለሆነች ለርሷ ተሰጥቷል።

አብይ ጣሰው

---

ንጉሶችና በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የተሳተፉ፣ ቤተሰብ የመሰረቱ ነበሩ።" (Nasser, Seid Hossien. *Prophet and Prophethood.*)

[10] ይህን እውነታ የሚያጸናልን ገጠመኝ አንድ ወዳጄ ከፌስ ቡክ ላይ አነበብኩ ብሎ የነገረኝ ታሪክ አለ- እርሱ ታሪኩ እውነተኛ ነው ብሎኛል። አንድ ክርስቲያን ከባለቤቱ ጋ በሰሜን ናይጀሪያ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የቦኮ ሃራም ሰዎች ያገኙታል። "ክርስቲያኖች ናችሁ ሙስሊሞች?" ሲል ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። "ሙስሊሞች ነን" ብለው ምላሽ ይሰጡታል። "ሙስሊምነታችሁን ለማረጋገጥ ከቅዱስ ቁርአን የተወሰነ አንቀፅ አንብብልኝ" ይለዋል። ሰውየውም እሺ ብሎት ከመፅሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ አናቅፅት ያነብለታል። የቦኮ ሃራሙ ሽብርተኛም ሙስሊሞች ናቸው ብሎ (ይቀጥላል) (የቀጠለ) በነፃ ይለቃቸዋል። ራቅ እንዳሉ የሰውየው ባለቤት "መፅሐፍ ቅዱስ የምታነብለት ልታስጨርሰን ነውን? ቆይ አሁን ቢነቃብህስ" ስትለው "እነዚህ ሰዎች ቅዱስ ቁርአንን አያነቡም፤ ቅዱስ ቁርአንን ቢያነቡ ኖሮ እንዲህ አይነት ድርጊት አይሠሩም ነበር" ብሎ መልሶላታል።

# ጂሃድና ሃይማኖቶች

## በዶ/ር ሪዛ አስላን[11]

አንድ ቀን በየስሪብ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ህልም አዩ። በሰፊ መስክ ላይ ቆመዋል። ከብቶች በነጻነት እየጋጡ ነው። እርሳቸው በእጃቸው የሆነ ነገር ይዘዋል- በፀሐይ ብርሃን እየተብረቀረቀ ያለ ከሰገባው የተመዘዘ ሰይፍ። በሰይፉ ስለት ላይ ምልክት ተቀርጿል። ጦርነት እየቀረበ ነው። በሰላማዊው መስክ ላይ፣ ከሚግጡት ከብቶች መሃል ርጋታ ሰፍኗል። ሁሉም ነገር "መልካም" ይመስላል። ራሳቸውን ሲመለከቱ ጠንካራ የጦር መከላከያ ልብስ እንደለበሱ አዩ። የሚያሳስብ ነገር አልነበረም። ሰይፉን በእጃቸው ይዘው ወሰን አልባውን አድማስ እየተመለከቱ ነው። ጦርነቱ ወደ እርሳቸው እስኪመጣ በልበ ሙሉነት በረጅሙ ቆመው እየተጠባበቁ ነው።

ከዕንቅልፋቸው ሲነቁ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የህልሙ ፍቺ ገባቸው- ቁርየሾቹ እየመጡ ናቸው። በዚያች ቅፅበት ቁርየሾቹ ነቢዩን ከነእንቅስቃሴያቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሬት ጭረው ሊቀብሩ ሶስት ሺህ እስከአፍንጫው የታጠቀ ጦር እና ሁለት መቶ ፈረሰኞች ይዘው ወደ የስሪብ እየገሰገሱ ነበር። እንደ ባህሉ ጦሩ በተለያዩ ጌጣ ጌጦች

[11] ዶ/ር ሪዛ አስላን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኘ ፀሐፊ እና የሃይማኖቶች ሊቅ ነው። አስላን ከሳንታ ክላራ ዩኒቨርስቲ በሃይማኖቶች ጥናት የመጀመሪያውን ዲግሪ ሲያገኝ (ሜጀር አዲስ ኪዳን፣ ማይነር ግሪክ)፣ ከሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ በነገረ መለኮት ጥናት የድህረ ምረቃ ዲግሪ፣ ከካሊፎርኒያ፣ ሳንታ ባርባራ፣ ዩኒቨርሲቲ በሶስዮሎጂ ኦፍ ሪሊጂንስ፣ ከአዮዋ ዩኒቨርስቲ በፋይን አርትስ የማስተርስ ዲግሪ አለው። የአስላን የመጀመሪያው መፅሐፉ *No god but God: The Origin, Evolution and Future of Islam* ሲባል ወደ 17 የሚሆኑ ቋንቋዎች የተመለሰ ሲሆን ካለፉት አስርት ዓመታት አስፈላጊ ከሆኑ መፅሀፍት መካከል አንዱ ሆኖ ተሰይሟል። የሚከተለው ምዕራፍ ከዚህ መፅሐፍ Fighting in the way of God ከሚለው ምዕራፍ የተተረጎመ ነው።

በተንሸቆጠቆጡና በተዋቡ አልባሳት ባጌጡ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ሴቶች ታጅቧል።

ሴቶቹ በኃያሏና አስደማሚዋ የአቡ ሱፍያን (የቁረይሾች ሸኽ) ሚስት ሂንድ ነበር የሚመሩት። ከአንድ ዓመት በፊት፣ በ624[12] ቁረይሾቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዩቻቸው ጋር በበድር ሲጋጩ የሂንድ ወንድምና አባት በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት ሐምዛ (ረ.ዐ) ተገድለው ነበር። ከአየሩ እንቅስቃሴ ጋር የሚያሽረግደውን ሻሏን በሁለት እጆቿ ጨብጣ እያዘገመች ያለችው ሂንድ፣ ቁረይሾች ሂጃዝን ለመቆጣጠር ለምን ጦርነቱን ወደ ነቢዩ ደጃፍ ማምጣት እንዳስፈለጋቸው አካላዊ አስታዋሽ ሆናለች። ከፊት ለፊቷ እየተመሙ ወዳሉት ወንዶች "የበቀል ጥሜን ተወጡልኝ" ብላ ጮኸች፤ "የ'ናንተንም እንዲሁ!"

የስሪብ እየተቃረበ በመጣው ጦርነት ጉምጉምታ ሰላሟ ተረብሿል። በነቢዩና በመካውያኖቹ መካከል በሚደረገው በዚህ ጦርነት መሳተፍ ያልፈለጉ የአይሁድ ጎሳዎች በቅፅሮቻቸው መወሰን መርጠዋል። "ሙሃጂሮች" (ስደተኞቹ) ለማይቀረው ጦርነት (ዕገታ) ያገኙትን የጦ[illegible] መሳሪያ መሰብሰብና ማዘጋጀት ጀምረዋል። በአንደኛው ቀን፤ የንጋት ሶላ[illegible] ጥሪ አጠቃላይ የዕምነቱን ተከታይ ማህበረሰብ ወደ መስጊድ ሲሰበስብ [illegible] የጉምጉምታውን እውነተኛነት አረጋገጡ።

"ቁረይሾች ወደ የስሪብ እየተመሙ መሆናቸው ትክክል ነው" [illegible]ሉ ተናገሩ። "ወደ አውላላ ሜዳ ወጥተን ከምንገጥማቸው እዚህ እስኪመጡ እንጠብቃቸዋለን" ሲሉ ዕቅዳቸውን አካፈሉዋቸው። በህልማቸው ለብሰውት ያዩት ጠንካራ የጦር ልብስ የየስሪብ ጠንካራ መከላከያ ቅፅር እንደሆነ ተረድተዋል። ቁረይሾች ተሞኝተው ይህችን የበርሃ "ገነት" ከተማ የሚያጠቁ

[12] ከዚህ በኋላ በተሰየ መልኩ እስካልተጠቀሰ ድረስ የዘመን መቁጠሪያው በሙሉ እንደ አውሮፓውያኖቹ አቆጣጠር ነው።





ከሆነ ሴቶቿና ልጆቿ ከተምር ዛፎቿ አናት ላይ ድንጋይ እየወረውሩ፣ ወንዶቿ ደግሞ በየመንገዷ ይወጓቸዋል።

ተከታዩቻቸው ግን የነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ዕቅድ በጥርጣሬ ነበር የተመለከቱት። ከአመት በፊት ቁረይሾችን እንዴት እንዳዋረዱዋቸው በደንብ ያስታውሳሉ። እንዳሁኑ ሁሉ የያኔው የቁረይሾች ጦር እስከ አፍጢሙ የታጠቀ ቢሆንም የነቢዩ ጥቂት ሰዎች እጅግ አሳፋሪ ሽንፈት አከናነቧቸዋል። አሁንስ የያኔውን ድል እንዳይደግሙ ምን እክል ይገጥማቸዋል?

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ፈሪዎች እና ደካማዎች ናቸው ብለው እንዳያስቡን ወደ ጦር ሜዳ ምሩን" አሏቸው።

ህልሙን ከአላህ እንደተሰደደላቸው መልዕክት የቆጠሩት ነቢዩ በተከታዮቻቸው ምላሽ ግራ ተጋቡ። ነገር ግን ወንዶቹ ጠላትን ወጥተን እንግጠመው በሚለው አቋማቸው ላይ ጉትጎታቸውን ሲያጠናክሩ እርሳቸውም እጅ እየሰጡ መጡ። ሌላው ይቅርና የእርሳቸው ቅርብ አማካሪዎች ምን መደረግ እንዳለበት ሊስማሙ አልቻሉም። በመጨረሻም ውሳኔ መስጠት ነበረበትና ነብዩ የጦር ልብሳቸው እንዲመጣለቸው አዘዙ። ቁረይሾቹን በአውላላ በርሃ ሊገጥሙዋቸው ነው።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጥቂት መቶዎች ከሚቆጠሩ ወንዶችና የተወሰኑ ሴቶች እንዲሁም ሁሌም ከጦር ሜዳ ከአጠገባቸው ከማይጠፉት እናት[13] አይሻ (ረ.ዐ) እና እናት ዑም ሰልማንን (ረ.ዐ) ጋር ከየስሪብ በሰሜን ምዕራብ የተወሰኑ ማይልሶች ርቀት ወደሚገኘ ዑሑድ አመሩ። ቁርየሾቹ የሰፈሩትና የጥቃት ዕቅዳቸውን እያቀዱ ያሉት በእዚህ እንደሆነ መረጃ ደርሷቸዋል። በዑሑድ ሸለቆ አልፈው የመካውያኑ ጦር ከሰፈረበት ብዙም ሳይርቅ፣ ከደረቀ የወንዝ መውረጃ ተቃራኒ ባለ ቦታ ሰፈሩ። ከዚህ የቁረይሾችን

[13] የእስልምና ተከታይ የሆነ የነቢዩን ባለቤቶች "እናታችን" በሚል የክብር ስም ነው የሚጠራው።

ድንኳኖች መመልከት ይችላሉ። የቁርይሾችን በርካታ ድንኳኖች መመልከት ይችላሉ። የቁርይሾቹን በርካታ ቁጥር ያለውን ወታደሮችና የጦር መሳሪያ ብዛት አዩ። የ'ርሳቸው ወገን ሁለት ፈረሶች ብቻ ነው ያለው። ምንም ግመል አልነበራቸውም።

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወደኋላ አፈገፈጉ። ጎህ እስኪቀድ ድረስ እንዲጠብቁ ተከታዬቻቸውን አዘዙ። ሲነጋ፣ ሰማዩ እየቀላ ሲመጣ ፈረስ ላይ ወጥተው ለመጨረሻ ጊዜ የጦራቸውን ሁኔታ ተመለከቱ። ከወንዶቹ መሃከል ሰይፍ የታጠቁ ልጆችን አዩ። የተወሰኑት ከትልልቆቹ ጋ ለመመሳሰል እየተንጠራሩ ነው። በቁጣ ከመስመሩ አወጧቸውና ወደቤት እንዲመለሱ አዘዙዋቸው። ኋላ ላይ የተወሰኑት አታለው ወደ ጦርነቱ ቢቀላቀሉም። ቀስተኞቻቸውን ከጦራቸው ክንፍ አጠገብ ከሚገኘው ተራራ ላይ "ከናንተ አቅጣጫ እንዳንጠቃ ጠብቁ" ብለው አሰፈሩ። ለተቀሩት "እኔ እስካላዘዝኳችሁ ድረስ እንዳትዋጉ" ብለው ትዕዛዝ አስተላለፉ።

ነብዩ ጦራቸው እንዲያጠቃ ትዕዛዝ ከሰጡ ምንም ያህል ሳይቆይ ቁረይሾች ተበታትነው መሸሽ ጀመሩ። ቀስተኞቻቸው ጎስቋላ ጦራቸውን ለመጠበቅ ወደ ጦር ሜዳው ፍላጻዎችን ያዘንባሉ። መካዎቹ ደጀናቸውን ለቀው አፈገፈጉ። ነገር ግን የቁረይሾቹን መሸሽ የተመለከቱት ቀስተኞቹ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከቦታችሁ እንዳትለቁ ትዕዛዝ ጥሰው ምርኮ ለመሰብሰብ ተራራውን ለቀው ወደ ሜዳው ሮጡ። ይህን ክፍተት የተመለከቱት ቁርይሾች ራሳቸውን አቀናጅተው ክፍት በሆነው ክንፍ ነቢዩንና ተዋጊዎቻቸውን ከበቡዋቸው። ጦርነቱ ዕልቂት ሆነ።

የመካው ጦር በነቢዩ ሃይል ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ለማድረስ ጊዜ አልፈጀበትም። የሙታኖች አፀደ ገላ ሜዳውን ሞላው። ቁርይሾች ሽምቀቆዋቸውን እያጠበቁ ሲመጡ የተወሰኑ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰዎች እየቀረበ ከመጣው ጦርና ከሁሉም አቅጣጫ እየዘነበ ካለው ፍላፃ ጋሻ ሆኖ ለመከላከል ነቢዩን ከበቡዋቸው። ነገር ግን ጥቂት ሰዎች እስኪቀሩ ገላቸው በፍላፃዎቹ እየተበሳሳ አንድ በአንድ እግራቸው ሥር ረገፉ። በመጨረሻ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)





ወደቁ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከወደቁ ተዋጊዎቻቸው አጠገብ ያለምንም መከላከያ ብቻቸውን ቀርተዋል። ጥርሶቻቸው ተሰብረዋል፣ ከንፈራቸው ተሰንጥቋል፣ ግንባራቸው ተፈንክቷል፣ በደም ተሸፍነዋል። ከጠላት ጋር ለመጋጠም የቀረ ሃይላቸውን ሲያሰባስቡ አቡ ዱጃናህ  የሚባል ግዙፍ ጦረኛ ተንደርድሮ መጥቶ የተረፉ ቁስለኞች ቁስላቸውን እየተንከባከቡ ወዳሉበት ሸለቆው አፋፍ ወሰዳቸው።

የነቢዩ ከጦር ሜዳው በድንገት መሰወር ሞተዋል የሚል ወሬ እንዲናፈስ ሆነ። ወሬው ቁረይሾቹ ጥቃታቸውን እንዲያቆሙ አደርጋቸው፤ ጦርነቱ አበቃ። የተቀሩት የነቢዩ ሰዎች በታላቅ ውርደት ወደ መዲና ሲያዘግሙ አሸናፊው አቡ ሱፍያን ወደ አንድ ኮረብታ ወጥቶ ሰይፉን አየር ላይ እያወናጨፈ "ሁበል ተከበር! ተከበር!" ሲል ጮኸ።

በዑሑድ መረጋጋት እየወረደ ሲመጣ ሂንድና የቁረይሾች ሴቶች ከቅድመ እስልምና በፊት እንደነበረው የዐረቦች ባህል ሜዳውን እያሰሱ ሬሳዎችን መተልተል ጀመሩ። ሴቶቹ የአንገትና የተረከዝ ጌጦችን ለማበጀት የወደቁ የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተዋጊዎችን አፍንጫ መፎነን፣ ጆሮዎች መበጣጠስ ተያይዘዋል። ሂንድ ግን አንድ አንገብጋቢ ጉዳይ ነበራት። ከተቀሩት ሴቶች ተገንጥላ የአባቷንና የወንድሟን ገዳይ፣ የነብዩን አጎት የሃምዛን አፀደ-ገላ እየፈለገች ነው። በመጨረሻ ስታገኘው ከአፀደ-ገላው አጠገብ ተንበርክካ ሸረከተችው፤ በእጆቿ ጉበቱን አውጥታ አኘከችው። በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የነበራትን በቀል ተወጣች።

* * *

በአሁነኞቹ ምሁራን ሳይቀር ኢስላም እጅግ በተደጋጋሚ እንደ "እምነታቸውንና ህጋቸውን በጦር ኃይል ለማከስፋፋት ቆርጠው የተነሱ አክራሪ ጦረኞች ያሉት ጦረኛ ሃይማኖት" ተስሏል- የታሪክ ሰውን በርናንድ ለመጥቀስ። የእምነቱ ተከታዮች ልክ እንደ አንበጣ መንጋ ወደ ጦር ሜዳ የሚተሙ ሆነው መሳላቸው በምዕራቡ ዓለም እጅግ የቆየ

ወልጋዳ ምልከታ (Sterotype) ነው። ታዋቂው ሶሽዮሎጂስት ማክስ ዌበርን ለመጥቀስ "ኢስላም ጠረኛ እንጂ በርግጥ የደህንነት (Salvation) ሃይማኖት ሆኖ አያውቅም"፤ እንደ ሳሙኤል ሃንቲንግተን ደግሞ ኢስላም "በደም ክልል" ውስጥ የታጠረ ሃይማኖት ነው።

ይህ ስሩ ጥልቅ የሆነ ወልጋዳ ምልከታ መነሻው የመስቀለኞቹ (ክሩሴደርስ) የጳጳሳት ፕሮፓጋዳ ነው፤ ሙስሊሞች ቅዱሱን መሬት (እና በጣም አንገብጋቢውን ወደ ቻይና የተዘረጋውን የሐር ንግድ መሥመር) የያዙና ያረከሱ ፀረ-ክርስቶስ ወታደሮች ተደርገው እየተገለፁ በነበረበት ወቅት። ሙስሊም ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶችና የሒሳብ ሊቆች ያለፈውን ዕውቀት እየጠበቁና የመጪውን ጊዜ ሊቅነት እየወሰኑ በነበረበት መካከለኛው ዘመን፣ እየተፈረካከሰ ያለው ጠብ ወዳዱ ቅዱሱ የሮማ ኢምፓየር ከየአቅጣጫው እያስጨነቁት ካሉት ቱርኮች ራሱን ለመለየት፣ በዚያ ዘመን ድንበር ለማስፋፋት ከጦርነት ውጪ ሌላ አማራጭ እንዳለ ሁሉ ኢስላምን "የሰይፍ ሃይማኖት" ሲል ሰየመው። የአስራ ስምንተኛውና ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅኝ-ገዥዎች የመካከለኛውን ምሥራቅና ሰሜን አፍሪቃን የተፈጥሮ ሃብት በዘዴ እየዘረፉ እና አሁን በሰፊው ጥቅም ላይ የዋለውን "ኢስላማዊ አክራሪነት" እየተባለ የሚጠራውን ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ተግዳሮት እየተከሉ በነበሩበት ወቅት፣ "ረጅም ጥምጣም የጠመጠመ፣ በመንገዱ ላይ የተደቀኑ ከሃዲዎችን ለማረድ ሰይፉን እየወለወለ ዝግጁ የሆነ" አስቀያሚ ሙስሊም በሰፊው የታወቀ የሥነ-ፅሑፍ ዘዬ ሆነ። አሁንም ነው።

አሁን ደግሞ የዚህ ቀደሙ የሙስሊሞች መንጋ ምስል በአዲስ ምስል ተተክቷል- ለአላህ ሰማዕት ለመሆን ዝግጁ እና ከእርሱ ጋር የቻለው ያህል ንፁሐን ሰዎችን ለመቅጠፍ ጉጉ በሆነ በፈንጂ ጃኬት በተጠረነፈ ሙስሊም አሸባሪ። በቆየውም ሆነ በአዲሱ ምስል ያልተለወጠው ነገር ኢስላም ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ ጀምሮ





እስከ አሁን ድረስ ተከታዮቹ ማባሪያ በሌለው ቅዱስ ጦርነት፣ ጂሃድ የተጠመዱ ሃይማኖት ነው የሚለው ነው።

የጂሃድ ቀኖና እንደ ሌሎቹ የሃይማኖቱ ቀኖናዎች ሁሉ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አልፈው ሙስሊም ማራኪዎች የቅርብ ምስራቅ ባህሎችን እና ልምዶችን መቀበል እስከ ጀመሩበት ድረስ ባሉ ረጅም ዓመታት እንደ ርዕዮተ-ዓለም መገለጫነት አልዳበረም ነበር። መታወስ ያለበት ነገር ኢስላም የተወለደው በታላላቅ ኢምፓየሮች እና ዓለም አቀፋዊ ምርኪያዎች (conquests) ዘመን፣ ሁለቱ ሃይማኖታዊ ንጉሳዊ መንግስታት- ባዛንታይኖችና ሰሰንያኖች- በቋሚ ሃይማኖታዊ ጦርነት ውስጥ ተቀርቅረው ባሉበት ጊዜ ነው። ከአረቢያ ሰላጤ የተነሳው የሙስሊሞች ጦር ገዥ የነበረውን አውድ ነው የተቀላቀለው። ሙስሊሞች አውዱን አልፈጠሩትም፣ ምን መምሰል እንዳለበትም አልወሰኑም። ነገር ግን እጅግ በፍጥነት ተቆጣጥረውታል። በምዕራቡና ክርስትያኖች ዘንድ ካለው ገናና ግንዛቤ በተቃራኒ ሙስሊም ማራኪዎች የማረኳቸውን ሰዎች በሃይል አያሰልሙም፤ እንደውም ሙስሊምነትን አያበረታቱም ነበር። በስምንት እና ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓረብ ሙስሊም በመሆን የሚገኘው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ፣ እስልምና ዐረብ ያልሆኑ ሰዎች መጀመሪያ የዓረቦች "ተቀጣሪ" መሆንን ባጠቃለለ ውስብስብ ሂደት የሚቀበሉት የሊሂቃኖች መሰባሰቢያ ሃይማኖት ሆኖ ነበር።

ይህ የሆነበት ወቅት ሃይማኖትና መንግሥት ህብረ-አምሳል የነበሩበት ዘመን ነው። ከጥቂት ድንቅ ወንዶችና ሴቶች በስተቀር በዚህ ጊዜ የሚኖር አይሁድ፣ ክርስትያን፣ ዞሮስቶሪያን ወይም ሙስሊም የእርሱን ሆነ የእርሷን ሃይማኖት በግለሰባዊ ምስክርነት ውስጥ አልፎ/ፋ ነው የተከተለው/ችው የሚባልበት ጊዜ አልነበረም። በዚያን ጊዜ ነዋሪ ከሆንክ ሃይማኖትህ ዘርህ፣ ባህልህ እና ማህበራዊ መለያህ ነበር።

ፖለቲካህን፣ ኢኮኖሚህን እና ሥነ-ምግባርህን ይወስንልሃል። ከምንም ነገር በላይ ሃይማኖትህ ዜግነትህ ነበር። እናም የቅዱስ ሮማ ኢምፓየር የክርስትናን አንድ አንጃ በመንግሥት ሃይማኖትነት እንዳፀደቀው ሁሉ ሰሳንየኖችም ዞሮአስቶርያንን በመንግስት ደረጃ ተቀብለው በህግ አፅድቀዋል። በህንድ ንዑስ አህጉርም (ቪሽኑን እና ዳግም ውልደቱን የተቀበሉት) የቫይሰናቫ ንጉሳዊ መንግሥት (የሺቫ ተከታይ) ከሆነው ሳይቫ ንጉሳዊ መንግስት ጋር በምሬት ሲቆራቆሱ በቻይና ደግሞ ለፖለቲካዊ ሃይል ያበላይነት የቡድሃ ተከታይ መሪዎች ከታዎ መሪዎች ጋር እየተዋጉ ነበር። በነዚህ ክልሎች፣ በተለይ ሃይማኖት መንግሥትን በሚያቆምበት በቅርቡ ምስራቅ፣ ግዛት ማስፋፋት የሃይማኖት ተከታይ ከማብዛት ጋር አንድ ነበር። በመሆኑም እያንዳንዱ ሃይማኖት "የሰይፍ ሃይማኖት" ነበር።

ሙስሊም ማራኪዎች በሃይማኖታቸው ያለውን የጦርነትን አረዳድና እና አተገባበር እያዳበሩ በነበሩበት ወቅት የሰሰንያን እና የባዛንታይን ኢምፓየሮች በከፍተኛ ደረጃ ምንነቱን ያዳበሩት እና ነገሥታት የሚያካሂዱት ሃይማኖታዊ ጦርነት ገጠማቸው። በርግጥም "ቅዱስ ጦርነት" የሚለው ቃል የተፈጠረው በኢስላም ሳይሆን በክርስትያን የመስቀለኛ ጦረኞች ነው። ግዛት ለማስፋፋትና የንግድ መስመር በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ የሚያደርጉትን ትግል ህጋዊ ለማድረግ የተጠቀሙት ሃይማኖታዊ ሽፋን ነበር። ሙስሊም ማራኪዎች "ቅዱስ ጦርነት" የሚለውን ቃል አልነበረም የተጠቀሙት፤ ቃሉ ጂሃድ የሚለውንም ቃል በትክክል አይወክልም። ጦርነት የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ የሚወክሉ ብዙ የአረብኛ ቃላት ቢኖሩም ጂሃድ ግን አንዱ አይደለም።

ጂሃድ የሚለው ቃል "ትግል"፣ "ጥረት" ወይም "ታላቅ ጥረት" የሚል ትርጉም አለው። በመጀመሪያው ሃይማኖታዊ አንድምታው (አንዳንዴ ትልቁ ጂሃድ እየተባለ በሚጠራው) አንድ ሰው ወደ አምላክ





እንዳይቀርብ እንቅፋት የምትሆንበትን ነፍስያውን መቆጣጠር የሚል አረዳድ አለው። በዚህ ምክንያት ነው በቅዱስ ቁርአን ውስጥ "ጂሃድ" የሚለው ቃል ሲጠቀስ "በአላህ መንገድ" የሚለው ሐረግ የሚከተለው። ነገር ግን ኢስላም ውስጣዊውን ለፅድቅ እና ለሙስሊምነት የሚደረገውን ትግል ከውጫዊው ለሰብዓዊነት ደህንነት ከሚደረገው ትግል ነጥሎ ስለማያየው ጂሃድ የሚለው ቃል በሁለተኛው አንድምታው (ትንሹ ጂሃድ)- በጭቆናና ግፍ ላይ ከሚደረግ ወታደራዊ ሆነ የትኛውም አይነት ትግል- ጋር እየተቆራኘ መጣ። ይህን የጂሃድ አረዳድ ሚሊታንት እና አክራሪዎች ለሚያራምዱት ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አጀንዳ ያግቱት እንጂ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቃሉን በፍፁም እንደነሱ አልተረዱትም።

በቅዱስ ቁርአን ጦርነት ወይ ፍትሃዊ አሊያም ኢ-ፍትሃዊ ነው፤ "ቅዱስ" ሆኖ አያውቅም። በመሆኑም ጂሃድ- የ"ፍትሃዊ የጦርነት ንድፈ ሃሳብ" አረዳዱ- በ624 በነቢዩ ሙሐመድ እየተኮተኮተ ባለው ኮስማና ማህበረሰብና በግዙፉ የቁርየሽ ጦር መካከል በሚደረግ ደም እና ቀውስ በሞላበት ጦርነት ውስጥ በግዴታዊ አስፈላጊነት የዳበረ ነው።

* * *

እንግዳ በሆነ መልኩ ቁረይሾች የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጨቅላ ማህበረሰብ በየስሪብ ስኬታማ መሆን እምብዛም የተረበሹ (የተጨነቁ) አይመስልም። ነገር ግን በዚያ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ይከታተላሉ። ቁረይሾች በሰላጤው ሰላዩችን በማሰማራት ገናናነታቸውን እንዳስጠበቁ ነው። ሥልጣናቸውንም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን አደጋ ውስጥ የሚጥል ነገር አላገኙም። የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩች ቁጥር መበራከት ምቾት ባይሰጣቸውም ከየስሪብ እስካልወጡ ድረስ መካ ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ለመርሳት ተዘጋጅታለች። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ግን መካን ሊረስዋት አልቻሉም።

በየስሪብ የተከሰተው ትልቁ ለውጥ የተገለፀው ምናልባት በባህላዊው የጎሳ ሥርዓት ውስጥ ሳይሆን በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ነበር። በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ እየወረደ ያለው ወሕይ[14] ከጥቅል የመልካምነትና የአላህ ኃያልነት ንግግሮች ወደ ጻድቅና እኩልነት የሰፈነበት ማህበረሰብ ግንባታ ላይ የሚያተኩሩ ዝርዝር የህግና የሲቪል ድንጋጌዎች ሲለወጥ የነቢዩም ነቢያዊ ንቃተ ህሊና እያደገ መጣ። መልዕክታቸው "ይህም ያወረድነው የኸነ ብሩክ፣ ያንንም በፊቱ የነበረውን (መፅሐፍ) አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው፤ የከተሞችን እናት (መካን)ና በዙሪያዋ ያሉትን ሰዎች"(6፡92) ማስጠንቀቂያ ብቻ አይደለም። በየስሪብ የዑምማቸው ተዓምራዊ ስኬት ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አላህ "ቅርብ ዘመዶችህንም"(26፡213) አስጠንቃቂ ብቻ አድርጎ እንዳላካቸው እንዲገነዘቡ አድርጓቸዋል። ሚናቸው "ለዓለማትም እዝነት"(21፡107) እና "ለሰው ዘር" መልዕክተኛ (12፡104፣ 81፡27) እንደሆነ በሚገባ ተረድተዋል።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማህበረሰባቸው የቱን ያህል ታዋቂ ወይም ስኬታማ ቢሆንም የሂጃዝ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ማዕከል በተቃውሞው እስከቀጠለ ድረስ ከየስሪብ ድንበር መሻገር አይችልም። እናም ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቁረይሾችን መጋፈጥ፣ ከተቻለም ከእርሳቸው ጎን ማሰለፍ ግድ ነበረባቸው። ነገር ግን መጀመሪያ አትኩሮታቸውን ማግኘት አለባቸው።

ቁረይሾችን የመጋፈጫ ብቸኛው አዋጭ መንገድ በነርሱው "መጽሐፍ" በኩል በመሆኑ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የስሪብ የተጠበቀች (ሐራም) ከተማ እንደሆነች አወጁ። በርግጥ ይህ እጅግ ደፋር የሆነ እርምጃ ነበር። በመዲና ህገ-መንግሥት የፀደቀው ይህ አዋጅ የስሪብን አዲሷ የሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ማዕከል አደረጋት። (በጥንታዊዋ ዐረቢያ

---

[14] ወሕይ- ሰዎች እንዲመሩበት ከአምላክ በገብርኤል አማካኝነት በቀጥታ ወደ ነቢያት ሲላክ የነበረ መልዕክት ነው። ነቢዩ ሙሐመድ የደረሳቸው ጥቅል መልዕክት ቁርአን ይባላል።





ሃይማኖትና ኢኮኖሚ ሊለያዩ የማይችሉ ነገሮች ናቸው።) ይህ ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ብቻ አልነበረም። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የስሪብን የተቀደሰች ከተማ ሲያደርጉ መካውያንን በስላጤው ላይ ያላቸውን ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ የበላይነት እየተገዳደሩ ነበር። መልዕክቱ ለቁረይሾች በሚገባ እንዲደርሳቸው ተከታዩቻቸው ሲራራ ነጋዴዎችን እንዲፈልጉ ላኳቸው።

ከእስልምና በፊት በነበረው ዐረቢያ የሲራራ "ወረራ" አናሳ ጎሳዎች ከቱጃሮቹ ሐብት የሚጠቀሙት ህጋዊ መንገድ ነበር። እንደ ሌብነትም ተቆጥሮ አያውቅም። ብጥብጥም ሆነ ደም መፋሰስ እስካላስከተለ ድረስ ካሳም አይጠየቅም። "ወራሪዎቹ" ማንም ሳያያቸው ከሲራራው የመጨረሻ/ዎቹ ግመሎች በእጃቸው ያገኙትን ይዘው ይመለሳሉ። እንዲህ አይነት ወቅታዊ "ወረራ" ለሲራራው መሪዎች የሚረብሻቸው ነገር ቢሆንም እጅግ ግዙፍ ሃብት/ንብረት ደህንነቱ ባልተጠበቀ በርሃ ለማጓጓዝ ተቀባይነት ያለው አደጋ ነው ተብሎ የሚታሰበው።

አናሳ እና በተሰባጠሩ የ"ሲራራ ወረራዎች" የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩች ዑማው (ሕዝቡ) የሚያስፈልገውን እንንብጋቢ ኢኮኖሚያዊ ድጎማ ማግኘት ብቻ ሳይሆን ከመካ የሚወጣውንና ወደ መካ የሚገባውን ንግድ መረበሽ ጀመሩ። ወደ ተቀደሰችው የመካ ከተማ የሚመጡ ነጋዴዎች በክልሉ መጓዝ ለደህንነታቸው አስጊ እየሆነ እንደመጣ ለቁረይሾች አቤቱታ ሲያቀርቡ ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም። እንደውም ነብዩ ሙሐመድ እና ተከታዮቻቸው በገቡላቸው የጥበቃ ቃል የተወሰኑ ሲራራ ነጋዴዎች አቅጣጫቸውን ለውጠው ወደ የስሪብ መመላለስ ጀምረዋል። በመካ ንግድ እየቀዘቀዘ፣ ትርፍ እየቀነሰ መጣ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚፈልጉትን አትኩሮት አገኙ።

በ624፣ ከአስከፊው የኡሑድ ጦርነት ሽንፈት አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከፍልስጤም ወደ መካ እየመጣ ያለ እጅግ ግዙፍ ሲራራ እንዳለ ወሬ ይደርሳቸዋል። የሲራራው ግዝፈት በቸልታ የማያሳልፍ ነበር። ነቢዩ ስደተኞች (ሙሃጅሮች) የበዙበት ሶስት መቶ አባላት ያሉት ስብስብ ይዘው ወጡ። እርሳቸውና ተከታዮቻቸው በድር አካባቢ ሲደርሱ ድንገት ከአንድ ሺ የቁረይሾች ተዋጊዎች ጋ ተፋጠጡ። የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዕቅድ አፈትልኮ ለመካውያኑ ደርሷቸዋል። አሁን ቁርየሾች ለነዚህ ወራሪዎች የማይረሱትን ትምህርት ሊሰጡዋቸው ተዘጋጅተዋል።

ሁለቱ ጦሮች ከበድር ሸለቆ ተቃራኒ ቦታዎች ላይ ሆነው ሲተያዩ ቀናት አለፉ። ቁርይሾቹ ነጭ ካባቸውን እንደለበሱ እጅግ ረጃጅም እና ካጌጡ ፈረሶቻቸውና ቡናማ ግመሎቻቸው ጋር ሲሆኑ በተቃራኒው ዑማው ተራ ልብስ እንደለበሰ ነው፤ ለሲራራ "ወረራ" እንጅ ለጦርነት አልተዘጋጁም። መሬት ላይ ባለው እውነት ሁለቱም ወገኖች ለጦርነት ፍላጎት አልነበራቸውም። ቁርየሾቹ ምናልባት በጦራቸው ግዝፈት የሙሐመድ አባላት እጅ ይሰጣሉ ወይም ተፀፅተው ይቅርታ ይጠይቃሉ ብለው፤ ነቢዩ ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ሁነት ውስጥ መዋጋት የእርሳቸውን ሞት ብቻ ሳይሆን የዑማውን ጥፋት ያስከትላል ብለው አስበው ይሆናል። እናም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በታላቅ ጉጉት ከአላህ መመሪያ እየጠበቁ ነው።

"አላህ ሆይ! ይህ ስብስብ ከጠፋ አንተን የሚያመልክ አይገኝም" እያሉ በተደጋጋሚ ይፀልዩ ነበር።

ለነብዩ መሐመድ የጦርነት ፍላጎት ማጣት ከመክሰም ፍርሃት የዘለለ ነገር ነበረው። ነብዩ ቁርየሾች እጅ እስካልሰጡ ድረስ መልዕክታቸው ከዓረቢያ ውጪ ሊሰማ እንደማይችል ካወቁ ቆይተዋል። ቁርየሾችን ያለ ውጊያ እጅ ማስጠት እንደማይቻል ከማወቃቸው ጋ፣ በወሕዩ የቅድመ-እስልምናን ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ውቅር ሳይመለስ





እንደተቀየረው ሁሉ የቅድመ-እስልምና የጦርነት ስልቶችና ሞራሎች (ሥነ ሥርዓቶች/ምግባሮች) መለወጥ አለባቸው።

ከእስልምና በፊት ዓረቢያ የ"ጦርነት ህጎች" ሳይኖራት ቀርቶ አይደለም። ውጊያ መቼና የት መካሄድ እንዳለበት የሚወስኑ በአማውያን ነገዶች መሀከል የተደነገጉ ህጎችና ደንቦች ነበሩ። ነገር ግን እነዚህ ህጎች የየነገዶቹን ህልውና ለማስጠበቅ ውጊያን ለመቆጣጠርና ለመወሰን የሚያገለግሉ እንጂ ጦርነት በምንም አይነት ሥርዓት መካሄድ እንዳለበት የሚደነግጉ አይደሉም። ፍፁማዊ ሞራል በጎሳ ህግና ሥርዓት ፅንሰ-ሃሳብ ውስጥ ይህ ነው የሚባል ሚና እንደማይጫወተው ሁሉ በጦርነትና ሰላም ፅንሰ-ሃሳብ ውስጥ ምንም አይነት ሚና አይጫወትም።

በቅዱስ ቁርአን ውስጥ በሂደት እየዳበረ የመጣው የጂሃድ ቀኖና በእስልምናና በቅድመ-እስልምና መካከል ያለውን የጦርነት ዕሳቦት ለመለየት የታለመ፤ ከዚያን ጊዜ በፊት በዓረቢያ የማይታወቀውን "ሙስተንሲር ሚር" በመባል የሚጠራውን "ርዕሥተ ዓለማዊ ሥነ ሥርዓት ገጽታ" ያካተተ ነበር። የጂሃድ ቀኖና ዐስኳል ከዚያ በፊት የማይታወቀውን ተዋጊውን ተዋጊ ካልሆነው መለየት ነው። በመሆኑም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ መነኩሴዎችን፣ ራቢዎችን፣ አዛውንትን ወይም የትኛውም አይነት ተዋጊ ያልሆነን መግደል ፈፅሞ ተከልክሏል።

እነዚህን ክልከላት በማስፋፋት የጦር ምርኮኞችን ማሰቃየት (ቶርቸር)፣ አስከሬኖችን መቆራረጥ፣ አስገድዶ ደፈራን፣ የትኛውንም አይነት ፆታዊ ትንኮሳን፣ የልዑካንን ግድያ፣ ንብረትን ማጥፋት እና ሃይማኖታዊ እና የህክምና ተቋማትን ማውደም ፈፅሞ ተከልክለዋል። ሂልሚ ዛዋቲ እንደተመለከተችው "እነዚህ ሁሉ በዘመናዊው ዓለም አቀፍ የጦርነት ህጋጋት ውስጥ ተካተዋል።"

ምናልባት የጂሃድ ቀኖና እጅግ አስፈላጊ ፊጠራው ራስን ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር የትኛውንም አይነት ጦርነትን መከልከሉ ነው። *"እነዚያን የሚጋደሉዋችሁን (ከሐዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፣ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።"* (2:190) በሌላ ቦታ ላይ ቁርአን የበለጠ ግልፅ በመሆን *"ለነዚያ ለሚጋደሉት (ምእምናን) እነርሱ የተበደሉ በመሆናቸው (መጋደል) ተፈቀደላቸው፤ አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ ቻይ ነው።"* (22:39)

አንዳንድ የቅዱስ ቁርአን አንቀጾች ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዩቻቸውን **"የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሏቸው"** (9:5) እንዲሁም **"አንተ ነቢዩ ሆይ ከሐዲዎችንና መናፍቃንን ታገል"** (9:73) ሲሉ ማዘዛቸው እውነት ነው። ነገር ግን እነዚህ አንቀጾች የሚመለከቱት ከነቢዩ አናሳ ማህበረሰብ ጋ አስቃቂ ጦርነት ውስጥ የገቡትን ቁርየሾችን (በቅዱስ ቁርአን ውስጥ "አጋሪዎች" በመባል ነው የሚታወቁት) እና በየስሪብ የሚገኙትን ደጋፊዎቻቸውን (አሁንም እነዚህ በቅዱስ ቁርአን ውስጥ "መናፍቃን" ተብለው ነበር ሲጠሩ የነበሩት) ብቻ ነው።

ሆኖም ግን አንቀጾቹ በሙስሊሞችም ሆነ ሙስሊም ባልሆኑት አንዳንድ ምሁራን ኢስላም ሙስሊም ያልሆኑትን አማኝ እስኪሆኑ ድረስ ሙስሊሞች እንዲዋጓቸው ያነሳሳሉ የሚል መከራከሪያ ይነሳል። ነገር ግን ይህ ቅዱስ ቁርአንም ሆነ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያፀደቁት ሃሳብ አይደለም። ይህ ሃሳብ ብቅ ያለው መስቀለኞቹ ገናና በሆኑበት ጊዜ ነበር። ለመስቀለኞቹ ምላሽ በሚል በኋላ ላይ የመጡ የኢስላም የህግ ምሁራን አሁን "ብሉያዊ የጂሃድ ቀኖና" እየተባለ የሚጠራውን ይህን የጂሃድ ሃሳብ አዳበሩት። የዚህ የጂሃድ ቀኖና አመክኖዋዊ ውጤት የሆነውና ገናና ሆኖ የመጣው ዓለምን በሁለት ክበብ መክፈል ነበር- ዳሩል ኢስላም (የኢስላም አገር) እና ዳሩል ሐርብ (የጦርነት አገር)።





የመስቀለኞቹ ዘመቻ እየተገባደደ ሲመጣና የሮም አትኩሮት ከሙስሊሞቹ በአውሮፓ እያቆጠቆጡ ወዳሉት ክርስታኒያን የተሃድሶ እንቅስቃሴዎች ሲዞር ብሉያዊው የጂሃድ ቀኖና በአዲስ ትውልድ የሙስሊም ምሁራን ክፉኛ መብጠልጠል ጀመረ። ከነዚህ ምሁራን መካከል ዋናው ኢብኑ ተይሚያህ (1263-1328) ነበር። ኢብኑ ተይሚያህ በሙስሊሙ ዓለም ያለውን ተፅዕኖ ለመረዳት ይረዳ ዘንድ ቅዱስ አውግስቲንን በክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ማየት በቂ ነው። የብሉያዊው ጂሃድ ቀኖና መሠረት- እስልምናን አልቀበልም ያሉ ሰዎች መግደል- የነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) *መንገድ መቃረን* ብቻ አይደለም የቅዱስ ቁርአንን *መሠረታዊ መርህንም መጣስ* ነው- *"በሃይማኖት ማስገደድ የለም"* (2:256)። በርግጥም ቅዱስ ቁርአን በሌሎች ቦታዎች ላይም በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን አቋም ለጥርጣሬ እንኳ በር እንዳይከፍት ግልፅ አድርጎ አስቀምጧል። *"እውነቱም ከጌታህ ነው፤ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ በላቸው"*(18:29)። *"ለማንኛውም ነፍስ በአላህ ፈቃድ ቢሆን እንጂ ልታምን (ችሎታ) የላትም"* (10:100)። በመሆኑም ቅዱስ ቁርአን አማኞችን እንዲህ ብለው እንዲመልሱ ያዛል *"ለናንተ ሃይማኖታችሁ አላችሁ፤ ለኔም ሃይማኖቴ አለኝ።"* (109:6)

የኢብን ተይሚያህ ብሉያዊውን የጂሃድ ቀኖና መቃወም በአስራ ስምንተኛውና አስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያሉ የበርካታ ሙስሊም የፖለቲካ አብሰልሳዩች ላይ ተፅዕኖውን አሳርፏል። በህንድ ሰይድ አህመድ ካን (1817-98) "ከእንግሊዞች ጋር በሚደረገው ትግል ጂሃድን መጠቀም አይቻልም፤ ምክንያቱም እንግሊዞች የህንድን ሙስሊም ማህበረሰብ ሃይማኖታዊ መብት አልጨቆኑምና" ሲል ተከራክሯል- ጂሃድ ለማወጅ የቅዱስ ቁርአን ቅድመ-ሁኔታ ነውና። (በህንድ ሲካሄድ በነበረው የፀረ-ኮሎኒያል ትግል የሰይድ አህመድ ሃሳብ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት አይከብድም)። ቺራግ ዓሊ (1844-95) የአህመድ ካን የቅርብ ጓደኛ

እና የቅዱስ ቁርአን ትንታኔ ምሁራዊነት ምክናዊ ማዕቀፋዊነት እንዲኖረው የገፋ የመጀመሪያው ምሁር ነበር፡፡ "በዚህ ዘመን ሙስሊም ማህበረሰብ መቼ እና እንዴት ጦርነት መካሄድ እንዳለበት ለመረዳት የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ታሪካዊ ዑምማ እንደ ህጋዊ ምሳሌ መውሰድ የለበትም፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የነበረው ማህበረሰብ ዓለም በቋሚ ቀውስ ውስጥ በነበረችበት ጊዜ የተወለደና ያደገ ማህበረሰብ ነውና" ሲል ተከራክሯል፡፡ ግብፃዊው የተሃድሶ ሰው መሐመድ ሸልቱት (1897-1963) የቺራግ ዓሊን ማዕቀፋዊ የቁርአን አረዳድ በመጠቀም "ኢስላም በቀጥታ ለሚደረግ ጥቃት ከሚሰጥ የምላሽ ጦርነት ውጪ ያሉትን ጦርነቶች ብቻ ሳይሆን የሚቃወመው ተገቢ ሙስሊም የህግ ባለሙያ ወይም ሙጅተሂድ ያላፀደቀውን ጦርነትም ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

በመስከረም 11 በኒውዮርክ የደረሰው ጥቃት በኢስላም ላይ ለደረሰ ጥቃት የተሰጠ የመከላከል ጥቃት አለመሆኑን ለማወቅ የሃይማኖቱ ተከታይ መሆን እንኳ አያሻም፡፡ በተገቢ ሙጅተሂድ ውሳኔ የተሰጠበትም አይደለም፡፡ ጦረኞችን ከሰላማዊ የለየም አልነበረም፡፡ ሴቶችን፣ ሕፃናትን እና ወደ 200 የሚጠጉ ሙስሊሞችን የጨረሰ ነበር፡፡ በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለተከላካይ ጂሃድ ከተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች አንዱንም ያላሟላ በመሆኑ፣ ምዕራቡና ሙስሊም ያልሆነው ህዝብ ከሚያስበው በተቃራኒ በሰፊው የሙስሊም ማህበረሰብና ፀረ-አሜሪካ ሰባኪ የሆነው የሊባኖሱ ሂዝቦላ መንፈሳዊ መሪ ሼክ ፊድለላህ ሳይቀር ነበር የተቃወሙት፡፡ መሬት ላይ ባለው ሐቅ በዓለማችን ላይ ካሉ ነዋሪዎች ከአራቱ አንዱ ሙስሊም ነው፤ ዑሳማ ቢን ላዲን በምዕራብያውያን የፖለቲካ ሰዎች የሽፍጥ ተግባር ያለውን ቅሬታ የሚጋሩት ቢሆንም የእርሱን የጂሃድ አረዳድ ግን አይቀበሉትም፡፡

በርግጥ ይህ ቀኖና ለግላዊ የእኩይ አስተሳሰብ ቅየዳዎች (Prejudices) ሆነ ፖለቲካዊ ርዕዮተ-ዓለም ግልጋሎት ላይ ቢውልም፣ ጂሃድ በሙስሊሙ ዓለም ሁሉን ዓቀፍ ሆነ ሁሉን አስማሚ በሆነ





መልኩ አልዳበረም፡፡ አዎን! እያንዳንዱ ሙስሊም ኢ-ፍትሃዊነትንና ጭቆናን የመዋጋት ግዴታ አለበት፡፡ አለበለዚያ *"ገዳማት፣ ቤተ ክርስቲያኖችም፣ ምኩራቦችም፣ በውስጣቸው የአላህ ስም በብዛት የሚወሳባቸው መስጊዶችም በተፈረሱ ነበር፡፡"* (22:40) ይህም ሆኖ ግን የቅዱስ ቁርአን ጂሃድ ዕይታ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ኢ-ፍታሃዊነትንና ጭቆናን የመከላከል ብቻ እና በግልፅ በተቀመጡት የጦርነት ህጋት ውስጥ የሚተገበር እንደሆነ ነው፡፡ እንደ የፖለቲካ ንደፈ ሃሳብ ቀማሪው ማካዬል ዋልዘር (Michael Walzer) የ"ፍትሃዊ ጦርነት" መወሰኛ ቅድመ ሁኔታዎች "በጦርነት ውስጥ ፍትህ" (Jus in bello) እና "የፍትህ ጦርነት" (Jus ad bellum) ከሆነ የነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የጂሃድ ቀኖና ከየጥንታዊው ዓረቢያ "ፍትሃዊ ጦርነት" የተሻለ ማብራሪያ ልናገኝለት አንችልም፡፡

* * *

በድር ይህን የጂሃድ ንድፈ ሃሳብ በተግባር ለማዋል የመጀመሪያው ምቹ አጋጣሚ ነበር፡፡ ቀናት ባለፉ ቁጥር ሁለቱ ጦረኞች አስጊ በሆነ ሁኔታ በአጭር ርቀት እየተቀራረቡ ቢመጡም ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እስካልተጠቁ ድረስ ላለመዋጋት ወሰኑ፡፡ እንደ አረብ ባህል ከሁለቱ ወገኖች ተዋጊዎች እየተመረጡ የተናጥል ፍልሚያ እያደረጉና ሌሎች እየተተኩ ፍልሚያ ቢጀመርም ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ግን እግሮቻቸው ላይ ተቀምጠው ከአምላክ መልዕክት እስኪመጣ ይጠብቁ ነበር፡፡ አቡበክር (ረ.ዐ) ነበር ከዚህ ጥበቃ የገላገላቸውና ወደ ጦርነቱ እንዲቀላቀሉ ያደረጋቸው- "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አምላክዎን እንዲህ አይጥሩት፤ አላህ የገባውን ቃል ከዳን በርግጥ ይሞላልና" አላቸው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተስማምተው ወደ አናሳ ስብስባቸው ሄደው በአላህ እንዲመኩና ጠላቶቻቸው ላይ በቆራጥነት እንዲዘምቱ መከሯቸው፡፡

ከዚያ በኋላ የመጣው ነገር ፍራንሲስኮ ጋብሬሉ "ክረብሻ ትንሽ የዘለለ" ብሎ ያወረደው ከፍተኛ ግጭት ነበር። ረብሻ ብንለው እንኳ ጦርነቱ ሲያልቅና አቧራው ሲጠራ አሸናፊው ማን እንደሆነ በግልፅ ታውቋል። በሚገርም ሁኔታ ነብዩ ሙሐመድ አንድ ደርዘን ሰው ሲያጡ ቁረይሾች ሙሉ ለሙሉ ተባረዋል። የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ድል ብስራት የስረብ የደረሰው ባለድሎቹ ከመድረሳቸው በፊት ነበር። ከበድር በኋላ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሸኽም ሆነ ሐካም (ዳኛ) ብቻ ተደርገው ሊቆጠሩ አልቻሉም። እርሳቸውና ተከታዩቻቸው የሂጃዝ አዲስ የፖለቲካ ሃይል ሆኑ፤ የስሪብም የእርሻ ቦታ ሳትሆን የዚህ ሃይል መቀመጫ፣ የነብዩ ከተማ-መዲና ሆነች።

በድር በሂጃዝ ሁለት ተቀራኒ ስብስቦችን ፈጠረ- ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የሚደግፉ እና ለቁረይሾች ታማኝ የሆኑ። ወገን ተመረጠ። በሂጃዝ ውስጥ ያሉ የጎሳ መሪዎች ከነቢዩ ጋ ቃል ለመጋባት ወደ መዲና ሲጎርፉ ከመዲናም የቁርየሾች ደጋፊ ወደ መካ ሄደው ነበር። በሚገርም ሁኔታ ከነዚህ ደጋፊዎች መካከል አብዛኛዎቹ "የአብረሃም ኃይማኖት" ተከታዮች-ሐኒፎች- ነበሩ። ምናልባት የሐኒፎቹ ተግባር ምክንያት ቃል ኪዳን ከካዕባ ጋ በመጋባታቸውና የካዕባ ጠባቂዎች ቁርየሾች መሆናቸው ይሆናል።

ነገር ግን ከመዲና ወደ መካ የተደረገው "ቅልብስ ስደትም" ሆነ የሐኒፎቹ መንሸራተት ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) አላሳሰባቸውም። ከዚህ የበለጠ አንድ አሳሳቢ ጉዳይ ጭንቅላታቸውን ይዟቸዋል። በመካከላቸው ከዳተኛ፣ የቁርየሾችን ሲራራ የመውረር እቅዳቸውን ያሾለከባቸው አለ። ብዙ የይሆናል አማራጮች ቢኖሩም ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጥርጣሬያቸው በኑ ቃይኑቃ ላይ አረፈ።

የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጥርጣሬ እንዲሁ ከመሬት የተነሳ አልነበረም። በመዲና ያሉ ከአይሁዶች ጎሳዎች አብዛኛዎቹ ከቁርይሾች ጋር አስፈላጊ የንግድ ግንኙነት አላቸው። የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመዲና መገኘት በፋይናንስ ረገድ ችግር ውስጥ ከቷቸዋል። በአረብ ጎሳዎችና በነብዩ





ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መካከል እየተፈጠረ ያለው ፖለቲካዊ ቃል ኪዳን የመዲና አይሁዶች በአረቢያ ውስጥ ያላቸውን ሃይል ክፉኛ እየሸረሸረው ነበር። የነቢዩ ግብር-ነጻ የገበያ ፖሊሲ በተለየ መልኩ በኑ ቃይኑቃዎች በኢኮኖሚያዊው ላይ ያላቸውን ሞኖፖሊ አሳጥቷቸዋል፣ ሀብታቸውን አስልሎታል። ከመካ ጋር የሚደረግ አይቀሬው ጦርነት (የሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማህበረሰብ እያደገ ሲመጣ) ከቁረይሾች ጋ ያላቸውን የኢኮኖሚ ግኝኙነት ሙሉ ለሙሉ ይበጥሰዋል። ቁረይሾች አይሁዶች የሚያመርቱትን ተምር፣ ወይን (መጠጥ) እና ጦር መሳሪያ ግንባር ቀደም ሸማች ነበሩና። በኑ ቃይኑቃዎችን ለአስራ አምስት ቀናት በቅፅራቸው ውስጥ አገቷቸው። በመጨረሻ ቃይኑቃዎች እጅ ሰጡ።

በበድር ድል ቢገኝም ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቁርይሾችን ወዲያውኑ በሙሉ ይማርኳቸዋል የሚል ዕሳቤ አልነበረም። የኋላ ኋላ መካዎቹ ራሳቸውን አደራጅተው ነቢዩን ለመውጋት መመለሳቸው አይቀርም። ይህ ሲሆን የአይሁድ ነገዶች ታማኝነታቸው ከቁረይሾች ጋ እንደሆነ በማያወላውል ሁኔታ ግልፅ ማድረግ አለብን ብለው ማሰባቸው አይቀርም።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና ሲገቡ የታማኝነት ጉዳይ ሳያሳስባቸው አልቀረም። በዚህ ምክንያት እርስ በእርስ በመተባበር መዲናን ከአደጋ የመከላከል ስምምነት አጠናከሩ። የመዲና ህገ መንግስት መዲናን ከአደጋ የመጠበቅ ኃላፊነት በእያንዳንዱ ነዋሪዎቿ ላይ እንደተደነገገ የሚያስረግጥ ነበር። ህገ-መንግሥቱ የሃይማኖትና የማህበረሰብን ነፃነትን "ለአይሁዶች የራሳቸው ሃይምኖት ለሙስሊሞችም የራሳቸው ሃይማኖት" በሚል አንቀጽ ሙሉ ለሙሉ ሲያረጋግጥ፤ "በዚህ ሰነድ ሕዝቦች ላይ ጦርነት ያነሳን" የመከላከል ኀላፊነት ተጥሎበታል። በመዲና ህግ መንግሥት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እግረ መንገዳቸውን ማን ከርሳቸው ጋር እንደሆነና እንዳልሆነ ያረጋገጡበት ነበር። ስለዚህ ቃይኑቃዎች እምነታቸውን ሲያጎድሉ ወዲያውኑ ርምጃ መውሰድ ነበረባቸው።

በዓረቦች ባህል መሠረት በክህደት ተግባር ላይ ለተሠማራ የሚጣለው ቅጣት ግልፅ ነው- ወንዶች በሙሉ ይገደላሉ፣ ሴቶችና ልጆች ለባርነት ይሸጣሉ፣ ንብረታቸው እንደ ምርኮ ይከፋፈላል። ቃይኑቃዎችን ጨምሮ የመዲና ነዋሪዎች በሙሉ በቃይኑቃዎች ላይ ይወሰድባቸዋል ብለው የጠበቁት ይህ ቅጣት ነበር። ነብዩ ሙሐመድ የዓረቦችን ልምድ ወደ ጎን ትተው ቃይኑቃዎችን ንብረታቸውን ይዘው ሃገር እንዲለቁ ሲያደርጉ ሁሉም በታላቅ ድንጋጤ ነበር የተመለከተው። ነብዩ ሙሐመድ እንዲያ አይነት ደፋር ድርጊት በወቅቱ ቢያደርጉም በዓመቱ በዑሁድ ደግመውታል።

የዑሁድ ጦርነት የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ከተገቢው በላይ የራስ መተማመን ያዳበረውን ዑምማ ሞራል ተጎዳድሯል። ከሁሉም ሁሉም ደግሞ የመዲና አይሁዶችን ግምት- ቁርየሾች የኋላ ኋላ ሙሐመድን ማሸነፋቸው አይቀርም- ትክክለኛነቱን አረጋግጧል። በኑ ናዲር እና በኑ ቁረይዛ፣ በመዲና ያሉት ግዙፍ የአይሁድ ነገዶች፣ በዑሁድ ጦርነት ውጤት በጣም ተደሰቱ። በተለይ በኑ ናዲሮች- ከጦርነቱ በፊት ሽኻቸው በድብቅ ከአቡ ሱፍያን ጋር ይገናኝ ነበር- የነብዩ ሙሐመድን ድክመት ለማሳየት በጦርነቱ ውስጥ እርሳቸውን እስከ መግደል ደርሰው ነበር። ነብዩ ሙሐመድ ሴራውን እንደተረዱ ቁስሉ ሳይጠግላቸው ቃይኑቃዎችን እንዳደረጉዋቸው ናዲሮችንም ከበቡዋቸው። ናዲሮች ለወገኖቻቸው አይሁዶች የእርዳታ እጆቻቸውን እንዲዘረጉላቸው ሲጠይቁዋቸው የበኑ ቁርይዛ ሽኽ ከዓብ ኢብን ሰዓድ ራሳቸውን እንዲችሉ ግልፅ አድርጎ ነገራቸው። ናዲሮች እጅ ከመስጠት ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም። ልክ እንደ በኑ ቃይኑቃዎች የጦር መሣሪያዎቻቸውን አስረክበው ከሃብት፣ ንብረትና ቤተሰቦቻቸው ጋር ከመዲና የመውጣት እድል እንዲሰጣቸው ሃሳብ አቀረቡ። ተከታዮቻቸው ባይወዱትም ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተስማሙ። በኑ ናዲሮች ሃብታቸውን ንብረታቸውን ይዘው ወደ ኸይበር ወጡ።

ከዑሁድ በኋላ በመዲናና በመካ መሃከል አልፎ አልፎ ግጭት ይፈጠር ነበር። በመጨረሻ በ627 ቁርየሾች እየተካሄደ ያለውን ግጭት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ ለማድረግ የአነርሱንና





የደጋፊዎቻቸውን ሙሉ ሃይል አሰባስበው ወደ መዲና ተመሙ። ሃሳባቸው የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ሃይል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመስበር ነበር። አሁን ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እዚያው መዲና ሊጠብቋቸው ወሰኑ። ከርሷቸው በኋላ ለክፍለ ዘመናት የተቀዳ አዲስ ወታደራዊ ቴክኒክ- ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመዲና ዙሪያ ምሽግ እንዲቆፈር- አዘዙ። ቁርየሾች ይህን በዓረቦች የማይታወቅ የምሽግ ጦርነት ለማሸነፍ ለአንድ ወር ያህል ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። በአቅርቦት ማጣትና ድካም ቁርየሾችና የቅንጅት ሃይሉ ተስፋ ቆርጠው ተመለሱ።

ይህ ጦርነት ለነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በቁርየሾች ላይ ቁርጥ ያለ ድል ያስገኘላቸው ባይሆንም በውጤቱ ግን ደስተኛ ነበሩ። ከሁለቱም ወገኖች እጅግ ጥቂት ሰዎች ነበር የሞቱት። ነገር ግን "የምሽጉ ውጊያ" እየተባለ የሚጠራው ይህ ጦርነት እጅግ ታዋቂ የሆነው በጦርነቱ ውስጥ በተደረገው ውጊያ ሳይሆን ከዚያ በኋላ በተፈጠረው ነገር ነው።

ለአንድ ወር በዘለቀው ፅገታ የመዲና ጦር የመካ ወራሪዎች ከተማዋን እንዳይወሩ በምሽግ ውስጥ ሆነው ሲጠብቁ በኑ ቁረይዛዎች በግልፅና በከፍተኛ ደረጃ የቁርየሾችን ጦር ሲደግፉ ነበር። የጦር መሳሪያዎችን፣ ሌሎች አቅርቦቶችንና እርዳታ አድርገውላቸዋል። በኑ ቁርይዛዎች ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በአደባባይ እንዲከዷቸው ያደረጋቸው ምክንያት ምን እንደሆነ መናገር ይከብዳል። የወራሪዎቹን የዓረብ ነገዶች በማቀናጀትና በማነሳሳት ረገድ እና ጦርነቱ እየተካሄደ ሲጫወቱት የነበረው ሞራል ማነሳሳት ሚናዎች ምናልባት የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንቅስቃሴ የመጨረሻው ስለሚሆን አቧራው ሲገፍ ከትክክለኛው ወገን ጎን ለመሆን አስበው፤ ነብዩ ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) ቢያሸንፉ ሊደርስባቸው የሚችለው የከፋ ነገር እንደ በኑ ቃይኑቃዎችና በኑ ናዲሮች አገር ለቀው መውጣት ነው፤ እነዚህ ነገዶች ደግሞ በከይበር እየተመነደጉ ነው የሚልም ስሌት ኖሯቸው ይሆናል። የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቸርነትን ግን ከዕውነታዊነት ወሰን በላይ ተገፍቶ ነበር።

ለአንድ ወር ያህል በኑ ቁርይዛዎችን በቅጥራቸው ውስጥ አግተዋቸው በቅጣታቸው ላይ ከአማካሪዎቻቸው ጋር እየመከሩ ነበር። በመጨረሻ ወደ አገሩ ባህል ፊታቸውን አዞሩ። ይህ ጠብ ስለሆነ ዕልባት የሚያገኘው በዳኛ ነው። ነገር ግን ጠቡ ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ያካተተ በመሆኑ እርሳቸው ዳኛ ሆነው ሊቀርቡ አይችሉም። የዳኝነቱ ሃላፊነት በአውስ ነገዶች ሸኽ በሰዓድ ኢብን ሙዓዛ ላይ ተጣለ። በኑ ቁርይዛዎች የአውስ ነገዶች ሸሪካ በመሆናቸው በሰዓድ ቀጥታዊ ጥበቃ ስር ነበሩ። እናም የሰዓድን ዳኝነት በፀጋ ተቀበሉት። ሰዳድ በጦርነቱ ከደረሰበት ጉዳት እያገገመ ካለበት ድንኳኑ በመውጣት ፍርዱን አስተላለፈ- "በነርሱ ላይ ፈርጃለሁ፤ ተዋጊዎቻቸው እንዲገደሉ፣ ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው እንዲማረኩ፣ ሃብት ንብረታቸው ምርኮ እንዲሆን።"

የበኑ ቁረይዛ ግድያ በሁሉም መስክ ካሉ ምሁራን ዘንድ የተለያዩ ምላሾች ቢያስወረውር የሚጠበቅ ነው። በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ቁጭ ብሎ የሚፅፈው ሄንሪክ ግሬትዝ (Heinrich Graetz) የኢስላምን ውስጣዊ ፀረ አይሁድነት የሚያሳይ ነው በሚል ክስተቱን እጅግ አረመኔ በሆነ መልኩ ሲገልፀው "የዘር ማጥፋትም ነው" ብሏል። ኤስ ደብልዩ ባርስን *Social and Religious History of the Jews* በሚለው መፅሐፉ ክልክ ባለፈ መልኩ በኑ ቁረይዛዎችን ከመሳዳ አመፀኞች ጋር አቆራኝቷቸዋል። (የመሳዳ አመፀኞች በ72 ለሮማውያን እጅ አንሰጥም ብለው በጅምላ ራሳቸውን ያጠፉ ናቸው።) በሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ የነበሩ ኦሬንታሊስቶ ይህ ክስተት ኢስላም ረብሸኛና ኋላ ቀር ሃይማኖት እንደሆነ ያስረግጣል ብለዋል። ፍራንሲስኮ ገብሬይሊ *Muhammed and the Conquest of Islam* በሚለው መጽሐፉ ሙሐመድ በበኑ ቁርይዛዎች ላይ የመፈፀሙ ድርጊት "እንደ ክርስትያንነታችንና ሠላጤነታችን፣ 'ይህ አምላክ ወይም ይህ የአምላክ ገፅታ የእኛ አይደለም' ብለን አስረግጠን መናገር አለብን" ብሏል።





ለነዚህ ክሶች ምላሽ የተወሰኑ ሙስሊም ምሁራን የበኑ ቁረይዛ ግድያ ጭራሹኑ ወይም በተገለፀው መልኩ እንዳልተፈፀመ የሚያረጋግጡ ጥቂት የማይባሉ ጥናታዊ ማስረጃዎችን አቅርበዋል። ለምሳሌ በረካት አሕመድና ደብልዩ ኤን አረፋት ሁለቱም "የበኑ ቁረይዛ ታሪክ ከቅዱስ ቁርአን ዕሴቶች እና ኢስላማዊ ምሳሌ ጋር የሚጣረስ ብቻ አይደለም፤ በኑ ቁረይዛዎችን እንደ የአምላክ ጀግና ሰማዕት ለማቅረብ የሚመኝ ነገር ግን እርስ በእርሱ በሚጣረስ ቀደምት የአይሁድ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው" የሚል ሃሳብ አቅርበዋል።

"የነቢዩ ድርጊት አሁን ዘመን ላይ ከደረስንበት የኤቲክስ መመዘኛዎች አንጻር መመዘን የለበትም። የቁረይዛዎች ግድያ መገምገም ያለበት ከታሪካዊ ዳራ አንፃር መሆን አለበት" ሲሉ ይከራከራሉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ብቅ ያሉት የኢስላም ምሁራን። ኬረን አርምስትሮንግ ስለነቢዩ ሙሐመድ ታሪክ በጻፈችበት ድንቅ መጽሐፏ "የነቢዩ ግድያ ለዚህ ዘመን አንባቢያን ክፉ መስሎ ቢታያቸውም በዘመኑ ከነበረው የነገድ ኤቲክስ አንጻር ህገ ወጥ ወይም ሥነ ምግባር የጎደለው አልነበረም" ብላለች። እንደዚሁም ሁሉ ኖማን ስቲልማን *The Jews of Arab Lands* በሚለው መፅሐፉ ‹‹በኑ ቁረይዛዎች የገጠማቸው ዕጣ ፈንታ "በወቅቱ ከነበረው አሰቃቂ የጦርነት ህግ አንጻር" እንግዳ አልነበረም›› ብሏል። ስቲልማን በመቀጠልም "በመዲና ያሉ አይሁድ ነገዶች የሙሐመድን ድርጊት ያለመቃወማቸው ሆነ በየትኛውም መንገድ ጣልቃ ያለ መግባታቸው ሐቅ (እውነታ) ይህን ክስተት አይሁዶች ራሳቸው "የአረቢያ ትውፊታዊ የጎሳና እና የፖለቲካ ጉዳይ" እንደሆነ እንደተቀበሉት ያመለክታል" ሲል አብራርቷል።

ነገር ግን አርምስትሮንግና ስቲልማን የቁረይዛዎችን ግድያ በታሪካዊና ባህላዊ ምክንያት ቢቀበሉትም፣ መንስኤው ግን በአይሁዶችና ሙስሊሞች መሃከል ስሩን አጥልቆ የሰደደው ርዕዮተ ዓለማዊ ፍጭት

ነው የሚል ሃሳብ ያራምዳሉ። ፍጭቱ አሁንም በመካከለኛው ምስራቅ እየታየ ነው ይላሉ። ስዊዲናዊው ምሁር ቶር አንድሬ (Tor Andreae) ግድያው ‹‹የሙሐመድ "አይሁዶች የአላህ እና የወሕዩ ታሪካዊ ጠላት ስለሆኑ ምንም አይነት ምህረት አይደረግላቸውም" የሚል እምነት ውጤት ነው›› ሲል ዕይታውን አዳብሮታል።

አንድሬ እና የእርሱን ሃሳብ የተቀበሉ ሌሎች በርካቶች ሃሳባቸውን በጨዋነት ከተቹነው ስለ ሙስሊሞች ታሪክ ሆነ ሀይማኖት ምንም ዕውቀት የማይሰተዋልበት መሃይምነት ይባል እንደሆን እንጂ መሬት ላይ ባለው ዕውነታ ጅልነትና በራሱ የማይቆም እንጭጭ ነው።

የበኑ ቁርይዛዎች ግድያ ምንም እንኳ ከባድ ቢሆንም የዘር ማጥፋትም፣ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ፀረ-አይሁድ አቋም ስላላቸውም የፈፀሙት ነገር፣ በእስልምናና ጁዳይዝም መካከል ያለ የሃይማኖት ግጭትም ውጤት ፈፅሞ አይደለም። እንደዚህ አይነት ከእውነት የራቀ ነገር የለም።

ሲጀምር በኑ ቁረይዛዎች አይሁድ ስለሆኑ አይደለም የተገደሉት። ማይክል ሌከር (Michael Lecker) እንዳሳየው የበኑ ቀርይዛ ወዳጅ የሆኑ በኑ ኪላብ የሚባሉ የዓረብ ነገዶችም በክህደት ወንጀሉ ተቀጥተዋል። በግድያው የሞቱት ሰዎች 400-700 ቢደርሱም (እንደ ምንጩ ስለሚወሰን ነው)፣ ከፍተኛውን ቁምት እንኳ ብንወስድ በመዲናና አካባቢው ሲኖሩ ከነበሩት አይሁዶች አንፃር እጅግ በጣም አናሳ ናቸው። የቃይኑቃና ናዲር ነገዶች ከቁጥር ውስጥ ባይገቡ እንኳ በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ አይሁዶች ከበኑ ቀረይዛዎች ግድያ በኋላ ከሙስሊሞች ጋር ለብዙ ዓመታት በሰላምና በፍቅር ኖረዋል። በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነበር በዑመር (ረ.ዐ) አመራር ጊዜ መዲናን ኢስላማዊ በማድረግ ሂደት በሰላም ከመዲና እንዲወጡ የተደረጉት። አንድ ፐርሰንት እንኳ የማይሞሉ ሰዎችን ግድያ





"የዘር ማጥፋት" ድርጊት ብሎ መሠመየም ቅጥ ያጣ ግነት ከመሆኑም በላይ በእውነተኛ የዘር ማጥፋት ሂደት ውስጥ አልፈው በተረፉት ላይ መዘባበት ይሆናል።

ሁለተኛ ሁሉም ምሁራን በአንድነት እንደሚስማሙት የበኑ ቁረይዛ ግድያ በኢስላማዊ ግዛቶች ውስጥ ለሚኖሩ አይሁዶች አያያዝ ቅድመ ሁኔታ አልፈጠረም። እንደውም በተቃራኒው በሙስሊሞች አመራር ሥር አይሁዶች ተጠናክረው ነበር። በተለይ አይሁዶችና ኦርቶዶክስ ያልሆኑ ክርስትያኖች ሃይማኖታቸውን ወደ ንጉሳዊው ሃይማኖት እንዲለውጡ በግድያ ወደሚገደዱባት ቫዛንታይን ኢስላም ሲስፋፋ የአይሁዶች አያያዝ ምርጥ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም አይሁዶችና ክርስቲያኖችን እንደ "ጥብቅ ህዝብ" (ዚሚ) በሚመለከታቸው የሙስሊሞች ህግ ሃይማኖታችውን ወደ እስልምና እንዲለውጡ አይታሰብም።'

የሙስሊሞች ዚሚዎችን ግድያ በኢስላማዊ ህግ የተከለከለም ብቻ ሳይሆን ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) "አይሁዶችን በሃይማኖታቸው እንዳታስቸግሩ፣ የክርስትያኖችን ተቋማት ጠብቁ" ትዕዛዝ የሚጣረስ ነው። ዑመር (ረ.ዐ) የአንድ አይሁድ ቤት በግዳጅ ፈርሶ የተሠራው መስጊድ እንዲፈርስ ሲያዝ የነብዩን "አይሁድንና ክርስትያንን የበደለ እኔ በፍርዱ ቀን እከሰዋለሁ" ማስጠንቀቂያ እየጠበቀ ስለነበር ነው።

አይሁዶችና ክርስቲያኖች በሚከፍሉት ጂዚያ በሚባል የ"ጥበቃ ግብር" የሙስሊሞች ህግ ለሁሉቱም ሙሉ ሃይማኖታዊ ሉዓላዊነት፣ ከሙስሊሙ ዓለም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋም ድርሻ የመካፈል እድል ተከብሮላቸዋል። በመካከለኛ ዘመኗ ስፔን ውስጥ እንደታየው አይነት የሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች የመከባበርና የመተጋገዝ ድንቅ ምሳሌ አልታየም። አይሁዶች በመንግሥቱና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ቦታዎች እስከመቆጣጠር ደርሰዋል። በሙስሊሟ ስፔን

ሃስዳይ ኢብን ሻፕሩት የሚባል አይሁድ ሃያል ከነበሩ ሰዎች መሃከል አንዱ ነበር። ለብዙ አስርት ዓመታት ለኸሊፋው አብዱረህማን III ታማኝ አማካሪ ሆኖ አገልግሏል። በዚያ ዘመን የተፃፉ የአይሁድ መዛግብት ዘመኑን "የአምላክ ምህረት ተገለፀበት" ብለው መጥራታቸው የሚገርም አይሆንም። ሆኖም ግን ሙስሊሟ ስፔን በ1492 በፈረዲናድ ክርስቲያናዊ ጦር ስር በወደቀች ጥቂት ወራት ውስጥ የስፔን አይሁዶች በጥቅሉ ከአካባቢው እንዲወጡ ተደርገዋል። እዚያው የቀሩትን ደግሞ ኢንኪውዚሽን አስተናግዷቸዋል።[15]

በመጨረሻ፤ እጅግ አስፈላጊው ነጥብ የበኑ ቁርይዛዎች ግድያ በተደጋጋሚ እየቀረበ እንዳለው በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና አይሁዶች መካከል ያለ ሃይማኖታዊ ግጭት ነፀብራቅ አይደለም። በጁዳይዝምና ኢስላማዊ ጥናቶች ውስጥ ያለተቃውሞ እየቀረበ ያለው

[15] በውስጡ ባቀፈው ሰፊ የሙስሊሞችና አይሁዶች ህዝብ ምክንያት ከምዕራብ አውሮፓ የመካከለኛዋ ዘመን ስፔን የእውነት የብዝሃ ሃይማኖት እና የብዝሃ ብሄር አገር ነበረች። የስፔን የሃይማኖት፣ ስነ ፅሑፍ፣ አርት እና ስነ ሕንፃ ስልጣኔ መንስኤው ይህ ነበር። አይሁዶች ስፔንንና ስርወ-መንግስቱን በንግድና በበርካታ የአመራር ቦታዎች የተማሩ ሊሂቃን በመሆን በደንብ አገልግለዋል። ነገር ግን ሃብታቸው ራሱን ክርስትናን ከከሃዲያን ጠባቂ አድርጎ በሚመለከተው ወገን ጥልቅ ጥላቻን ፈጠረ። የካቶሊኮቹ ስርወ-መንግስት አመራሮች ብልጥ ታክቲሺያን በመሆናቸው ከዚህ ጥላቻ ተጠቀሙበት። በ1478 የአይሁዱቹንና ተለዋጮቹን ህሱም ተፅዕኖ ለመዋጋት ኢንኪውዚሽንን ለማቋቋም ከፓፓሱ ሲክስተስ አራተኛ ፈቃድ አገኙ። ሃይማኖቱን ለውጫለሁ የሚለውን ምስክርነት ለማዳመጥ ካላቸው ጉጉት የተነሳ ኢንኪውዚሽን አስፈፃሚዎቹ እንደ ስቅየት (ቶርቸር)፣ ተከሳሹ አማካሪ እንዳያገኝ መከልከል፣ ተዳፋሪ ምስክርን የመጋፈጥ (ይቀጥላል) (የቀጠለ) መብት ማሳጣት፣ ኢንኪውዚሽን አስፈፃሚዎቹ የተከሰሱ ሰዎችን ንብረት መውሰድና መከፋፈል የመሳሰሉ ድብቅ ፕሮሲጆሮችን ይጠቀማሉ። ሃይማኖታቸውን ከለወጡት የጁዳይዝምን አምልኮ ተግባር ሲፈፅሙ ተገኝተዋል በሚል በርካቶች ተኮንነው ተቃጥለዋል። (ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፣ ቅፅ 28 ገፅ 39) (ተርጓሚው)





ይህ ንድፈ ሃሳብ የተመሰረተው፣ መልዕክታቸው የጂዶ-ክርስታያን ትውፊት ቤተሰብ ነው ብለው የሚያስቡት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መዲና ያሉ አይሁዶች ነቢይነቴን ይቀበላሉ የሚል ዕሳቤ ነበራቸው በሚል ሃሳብ ላይ ነው። በመሆኑም አይሁዶቹ ነብይነታቸውን ለመቀበል እንዲቀላቸው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተለያዩ የአይሁዶች አምልኮዎችንና ልምዶችን በመቀበል ማህበረሰባቸውን ከአይሁዶች ጋ ለማገናኘት ሞክረዋል። ነገር ግን ባልጠበቁት ሁኔታ አይሁዶች እርሳቸውን ሊቀበሉዋቸው ቀርቶ ቅዱስ ቁርአን መለኮታዊ ራዕይ መሆኑን መከራከር ጀመሩ። የአይሁዶቹ ተቃውሞ ነቢይነታቸው ላይ ጥላ እንዳያጠላበት በመሥጋት ነብዩ አይሁዶች ላይ የሃይል ርምጃ ወሰዱባቸው፤ ማህበረሰባቸውንም ከአይሁዶች ነጠሉ፤ በኤፍ.ኢ.ፒተርስ ቃል "እስልምናን የአይሁድ አማራጭ አድርገው እንደ አዲስ ቀረፁት።"

ይህ ንድፈ ሃሳብ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት። አንደኛው የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ጥበብ የዘነጋ ነው። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተጠረቡ ድንጋዮችን የሚያመልኩ የዓረብ ዘላን አልነበሩም። እርሳቸው ለግማሽ ምዕተ- ዓመት ያህል የዓረቢያ ምድር የሃይማኖት ዋና ከተማ በሆነችው መካ የኖሩ፣ ከአይሁዶችና ክርስትያኖች ጋር ኢኮኖሚዊ ግንኙነት የነበራቸው የተራቀቁ ነጋዴ ነበሩ። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነብያዊ ተልዕኮዋቸው "ለእርሳቸው ግልፅ እንደሆነ ለአይሁዶችም ይሆናል" (ሞንት ጎሞሪን ለመጥቀስ) ብለው ያስቡ ነበር ብሎ ማሰብ እጅግ የሚያሳዝን ግልብነት ነው። እርሳቸውን እንደ ነቢያቸው እንደማይቀበሉዋቸው ለማወቅ እጅግ ግልፅ የሚባሉ የሃይማኖት አስተሳሰቦቻቸውን ማወቅ ከበቂ በላይ ነው። አይሁዶች የራሳቸውን ሰው ኢየሱስን እንደ ነቢይ እንደማይቀበሉ በእርግጠኝነት እያወቁ እንዴት እርሳቸውን ነብያቸው አድርገው ይቀበሉኛል ብለው ያስባሉ?

ይህ ንድፈ ሃሳብ ያለው ትልቁ ህፀፅ ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) አሳንሶ ብቻ መመልከቱ ሳይሆን ለመዲና አይሁዶች የሰጠው ዋጋ ነው፡፡ የመዲና የአይሁድ ነገዶች ወደ አረብነት መለወጥ ብቻ ሳይሆኑ አጠገባቸው ካሉት አረማዊ አረቦች በባህልም ሆነ በሃይማኖት እምብዛም የሚለዩ አልነበሩም፡፡ የዓረብኛ ምንጮች እንደሚስረዱት የመዲና አይሁዶች "ራታን" የሚባል ቋንቋ (ጦበሪይ ፋርስኛ ነው ብለው ቢረዱትም ምናልባት የዓረብኛና አረማይክ ቋንቋዎች ቅይጥ ሊሆን ይችላል) ነበር የሚናገሩት፡፡ እብራይስጥኛ ይናገሩም ሆነ ይረዱ እንደነበር የሚጠቁም ማስረጃ የለም፡፡ በርግጥ ለእብራይስጥ ቅዱሳን መጽሐፍት ያላቸው ዕውቀት ጥቂት ጥቅል ህግጋት፣ የተወሰኑ የፀሎት መጽሐፍት እና በጣት የሚቆጠሩ የቶራህ ዓረብኛ ትርጉም፣ ኤስ ደብልዩ ባሮን "የተለቃቀሙ አፋዊ ትውፊቶች" ብሎ የሚጠራው እንደሚሆን ነው፡፡

የጁዳይዝም ዕውቀታቸው እጅግ ውስን ከመሆኑ የተነሳ አንዳንድ ምሁራን እውነተኛ አይሁዶች መሆናቸውን ይጠራጠራሉ፡፡ ዲ. ኤስ ማርጎሊዩት የመዲና አይሁዶችን የአንድ አምላክ አምልኮ የላላ ስብስብ- እንደ ሐኒፎቹ- በተገቢው አጠራር "ራህማኒስቶች" (ራህማ የአላህ ሌላው መጠሪያ ነው) አድርጎ ነው የሚቆጥራቸው፡፡ ብዙዎች በማርጎሊዩት ትንታኔ ባይስማሙም፣ የመዲና አይሁዶች ከጁዳይዝም ጋር ያላቸውን ቅርርብ ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚያስገቡ ሌሎች ምክንያቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ በኤች.ጂ. ሬይስነር (Reissener) እንደተወሳው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአይሁድ ዲያስፖራ ማህበረሰቦች ሙሉ ለሙሉ ያፀደቁት ስምምነት አለ- እስራኤላዊ ያልሆነ አይሁድ ለመባል "በተልሙድ ውስጥ በተቀመጡት መርሆች መሠረት የሙሴን ህግ መከተል አለበት፡፡" ይህ ስምምነት እስራኤላዊ ሆነው የሙሴ ህግ ቀጥተኛ ተከታይ ያልሆኑትን ሆነ የተልሙድ ትክክለኛ ዕውቀት የሌላቸውን የመዲና አይሁዶችን ከአይሁድነት ያስፍቃቸዋል፡፡ በተጨማሪም የአይሁዶችን መኖር በቀላሉ የሚጠቁም ምልክት





በአርኪዮሎጂ ቁፋሮ አለተገኘም፡፡ እንደ ጆናታን ሪድ በአንድ ቦታ መሠረቱን የጣለ የአይሁድ መለያ ለመኖሩ መስዋዕት ማቅረቢያ የድንጋይ ትክሎች፣ የመጠመቂያ ገንዳ (ሚቅቫኦት) ቅሪቶችና አስክሬን ማስቀመጫዎች የመሳሰሉ ጠቋሚዎች መኖር አለባቸው፡፡ እስከምናውቀው ድረስ ከነዚህ ጠቋሚዎች መሃከል አንዳቸውም በመዲና አልተገኙም፡፡

ሆኖም እንደሚጠበቀው የመዲና አይሁድ ነገዶች የሃማኖታዊ መለያ እንዳላቸው የሚከራከሩ አሉ፡፡ ለምሳሌ ጎርዳን ኒውባይ የመዲና አይሁዶች የራሳቸው ት/ቤቶች እና መጽሐፍት ያላቸው የተለዩ ማህበረሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ ያስባል፡፡ ይህን ሃሳቡን የሚደግፍለት ምንም አይነት አርኪዮሎጂያዊ ማስረጃ ባኖርም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ኒውባይ ራሱ የመዲና አይሁዶች ባህላቸው፣ ሥነ ምግባራቸው ሌላው ይቅርና ሃይማኖታቸው ራሱ ከሌሎች በአረቢያ ምድር ከሚገኙ አይሁዶች እንደሚለይና መሬት ላይ ባለው ዕውነታ (ከሙሴ ህግ በተቃራኒ) እንደልብ ከሚጋቡዋቸው የመዲና አረማዊያኖች ጋ ተመሳሳይ እንደሆነ ያምናል፡፡

በቀላሉ ሲቀመጥ የመዲና የአይሁድ ነገዶች በየትኛውም መንገድ የጁዳይዝም ሃይማኖት ተከታይ አልነበሩም፡፡ ማርጎሊዩት እና ሌሎች ትክክል ከሆኑ አይሁድም ሊባሉ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ቁርአን ሊያነቡዋቸው ከማይቹላቸው ሆነ ምናልባትም በእጃቸው ከሌሉ የእብራይስጥ መጽሐፍት ጋ ስለመመሳሰሉና መቃረኑ ውስብስብ ክርክር ውስጥ ገብተዋል የሚለውን ለመቀበል እጅግ ይከብዳል፡፡

እውነታው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተናገሩት ሆነ የተገበሩት ከመዲና አይሁዶች (የጂዳይዝም እምነት ተከታይ ናቸው ከተባለም) የሚቃረን አይደለም፡፡ ኒውባይ *A History of the Jews of Arabia* በሚለው መጽሐፉ እንዳስፈረው በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን

እስልምናና ጁዳይዝም "በተመሳሳይ ሃይማኖታዊ ተዋስኦ" ሥር ነበር የሚንቀሳቀሱት። ሁለቱም ተመሳሳይ የሃይማኖት ሰብእናዎችን፣ ታሪኮችንና ተምሳሌታዊ አስተምሮቶችን ይጋራሉ፣ ሁለቱም መሠረታዊ ጥያቄዎችን ከተመሳሳይ ዕይታ አንጻር ይመልሳሉ፣ ሁለቱም እጅግ ተቃራራቢ የሞራልና ኤቲክስ ዕሴቶች አሏቸው። በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ልዩነት ካለም፣ ኒውባይ እንደሚጠቁመው "በጋራ ርዕስ ላይ በሚኖራቸው የአተረጓጎም ልዩነት ነው እንጂ ሁለቱም የተለያዩ ራሱን የቻለ ንፅረዖተ ዓለም ስላላቸው አይደለም።" ኤስ. ዲ. ጎይትን ለመጥቀስ "በሙሐመድ ስብከት ውስጥ ለአይሁዶች የሚጎረብጥ ነገር አልነበረም።"

ሌላው ይቅርና የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልዕክተኛነት እና ደቀ-መዝሙርነት ጥሪ የመዲና አይሁዶች የማይቀበሉበት ምክንያት አልነበረም። የነቢዩ ቃላትና እንቅስቃሴ በአረቢያ ውስጥ ሲታመኑ ከነበሩ የአይሁዶች ሃይማኖት ጋር አንድ አምሳል ባይሆን እንኳ በወቅቱ በመዲና ነብይ ነኝ ብለው የተነሱት እርሳቸው ብቻ አልነበሩም። መዲና ኢብን ሰያድ የሚባል የአይሁድ ተማልሎዋዊ እና ካህን መኖሪያም ነበረች። እንደ ነብዩ ከሰማይ መልዕክት ወረደልኝ እያለ የሚያነበው ነገር ነበረው። ራሱንም "የአላህ ደቀ-መዝሙር" ነኝ ይል ነበር። በሚገርም ሁኔታ አብዛኛው የመዲና አይሁድ ነገዶች የኢብን ሰያድን ነብይነት መቀበላቸው አይደለም፣ ምንጮች እንደሚያስረዱት ኢብን ሰያድ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በግልፅ የአላህ ደቀ-መዝሙርና ነብይ እንደሆኑ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና በመዲና አይሁዶች መሃከል ሃይማኖታዊ ግጭት የለም ብሎ በአጭሩ መደምደም ይቻላል። በነብዩና በአይሁዶቹ መሃከል ያለው ግጭት ከፖለቲካዊ የወዳጅነት አሰላለፍና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ተሻግሮ ወደ ሃይማኖታዊ ክርክር የዘለለ እንዳልሆነ ማስተዋል ተገቢ ነው። ግጭቱ በትስስርና ከግብር ነጻ በሆነ ገበያ





የተፋፋመ ነው እንጂ ከሃይማኖታዊ ቀናኢነት የመነጨ አልነበረም። የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክ ፀሐፊዎች ነብዩን "አምላክ ከዐረቦች መሀከል ነብይ ስለመረጠ ከተበሳጩ እና ነብዩን በቅናት፣ ጥላቻ እና ክፋት ከሚያዩዋቸው" "ራቢዎች" ጋ ነገረ መለኮታዊ ክርክር ውስጥ የገቡ አድርገው ቢያቀርቧቸውም ታሪካዊ እውነት የለውም።

ቅዱስ ቁርአን በተደጋጋሚ እንደሚናገረው ሙስሊሞች እያዳመጡ ያሉት መልዕክት አዲስ መልዕክት ሳይሆን *"በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ"* (12:111) ነው። እንደውም ቅዱስ ቁርአን የማይጠበቅ ሀሳብ አቅርቧል- ሁሉም ቅዱሳን መጽሐፍት በሰማይ ካለው "ኡም አል-ኪታብ" (የመጽሐፍት እናት) "አላህ የሚሻውን ያብሳል፤ ያፀድቃልም፤ *የመጽሐፉ መሠረትም* እርሱ ዘንድ ነው።"(13:39) ከሚባል መጽሐፍ የመጡ ናቸው። በዚህም ምክንያት ቅዱስ ቁርአን ሙስሊሞችን ለአይሁዶችና ክርስቲያኖች እንዲህ እንዲሉ ይመክራቸዋል: *"በአላህ አመንን፤ በኛ ላይ በተወረደው (በቁርአን)፣ በኢብራሂምና በኢስማዒልም፣ በኢስሓቅም፣ በያዕቁብም፣ በነገዶችም ላይ በተወረደው፤ ለሙሳና ለዒሳም፣ ለነቢያትም ሁሉ በተሰጠው (አመንን)፤ ከነርሱ መካከል አንድንም አንለይም፤ እኛ ለርሱ ታዛዦች ነን በል።"*(3:84)

አዎን ሙስሊሞች ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) "የነብያት መደምደሚያ ናቸው" ብለው እንደሚያምኑት ቅዱስ ቁርአንም "ከአምላክ የወረደ የመጨረሻው ወሕይ ነው" ብለው ያምናሉ። ቅዱስ ቁርአን ደግሞ ከእርሱ ቀደም የመጡትን መጽሐፍት ላሟላ እንጂ ልደመስስ ምጣሁ አላለም። አንድ ቅዱስ መጽሐፍ ለሌሎች ቅዱሳን መጽሐፍት እውቅና የመስጠቱ ነገር በሃይማኖቶች ታሪክ የሚደነቅ ነገር ቢሆንም፣ የኡም አል-ኪታብ ሃሳብ ከዚህም የዘለለ ጥብቅ መርህን ያመለክታል።

ቅዱስ ቁርአን ደግሞ ደጋግሞ እንደሚናገረው፣ የመዲና ህገ-መንግሥትም እንደሚያፀድቀው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የዑም አል-

ኪታብን ፅንሰ ሃሳብ አይሁዶች፣ ክርስታያኖችና ሙስሊሞች አንድ መለኮታዊ መጽሐፍ እንደሚጋሩና አንድ ዑምማ እንደሆኑ ነው የተረዱት። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አይሁዶችና ክርስቲያኖች "የመጽሐፍ ባለቤቶች"(አህል አል-ኪታብ)፣ በአረማዊነትና ብዙ አምላክ አምልኮ ላይ የተነሱ መንፈሳዊ ወንደማማቾች፣ ከእርሳቸው ሙስሊም ማህበረሰብ ጋር ተመሳሳይ የሞራል ዕሴቶች የሚጋሩ ናቸው- ሙሐመድ ባይሜህ "የአንድ አምላክ አምልኮ ብዝሃነት" እያለ የሚጠራው ድንቅ ሃሳብ- ብለው ነበር የሚያምኑት። በመሆኑም ቅዱስ ቁርአን ቃል ሲገባ *"እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም፣ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፣ በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፣ እነርሱም አያዝኑም።"* (5:69)

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማህበረሰባቸውን ከአይሁዶቹ ጋር ለማቀራረብ የፈለጉበት ምክንያት የዚህ የአንድ አምላክ አምልኮ ዑምማ እምነታቸው እንጂ አይሁዶች ነብይነታቸውን እንዲቀበሏቸው ካላቸው ፍላጎት አልነበረም። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማህበረሰባቸውን ከመዲና አይሁዶች ጋ ያቀራረቡት እነርሱንም ሆነ ክርስትያኖችን የእርሳቸው ዑምማ ክፍል እንደሆኑ ስለቆጠሩዋቸው ነበር። ወደ መዲና ሲመጡ እየሩሳሌምን የሶላት መስገጃ ቂብላ[16] አድርገዋል። አይሁዶች ዘመን እንደለወጡ በመጀመሪያው ወር በአስረኛው ቀን ላይ የሚፆሙትን (አይሁዶች ዩም ኪፑር ይሉታል) የአሹራ ፆም እንዲፆም ግዴታ አድርገው ነበር። ራሳቸውም እንዳደረጉት ተከታዮቻቸው የአይሁድ ሴቶችን እንዲያገቡ ተፈቅዶላቸዋል።

> *"ዛሬ መልካም ሁሉ ለናንተ ተፈቀዱ፤ የነዚያም መፅሐፍን የተሰጡ ሰዎች ምግብ (ያረዱትን) ለእናንተ የተፈቀደ ነው፤ ምግባችሁም ለነሱ የተፈቀደ ነው፤ ከምእምናት ጥብቆቹም፣ ከነዚያ ከናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና የምስጢር ወዳጅ ሳትሆኑ ጥብቆች ሆናችሁ፣ መህሮቻቸውን በሰጣችኋቸው ጊዜ (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)" (5:5)*

16 መቅጣጫ





ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ቂብላ (ወደ ካዕባ) እና የግዴታ ፆም (ከዩም ኪፑር ወደ ረመዳን) የመለወጡ ነገር እርግጥ ቢሆንም ይህ ድርጊት "ከአይሁዶች መነጠል" ተብሎ ሳይሆን መተርጎም ያለበት ኢስላም የራሱን ህልውና አዳበረ ተብሎ ነው። ምክንያቱም የግዴታ ፆሙ ወደ ረመዳን ቢለወጥም ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዬቻቸው የአሹራን ፆም እንዲፆሙ አበረታተዋል። ለእየሩሳሌም ያላቸው ክብርም አልለወጠም። በኢስላም እየሩሳሌም ከመካና እና መዲና ቀጥሎ አሁንም የተከበረች ከተማ ነች። ቅዱስ ቁርአን *"የመጽሐፉን ባለ ቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ"* (29:46) ብሎ እንዳዘዘው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በአካል ከዚህች ዓለም እስከተለዩ ድረስ ከአረቢያ አይሁዶች ጋር የነበራቸው ግንኙነት በሰላማዊ ተዋስኦ ውስጥ ነበር።

ይህ እንዳለ ሆኖ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ፈፅሞ ያልተቀበሉዋቸው የተወሰኑ ነገረ-መለኮታዊ ልዩነቶች ነበሩ። እንደርሳቸው እምነት እነዚህ ልዩነቶች የተፈጠሩት ባለማወቅና በስህተት ሲሆን የኋላ ኋላ የተቀጠሉ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ዋናው የ"ስላሴ" ፅንሰ ሀሳብ ነው። ቅዱስ ቁርአን በግልጽ እንደሚያስቀምጠው አምላክ "አንድ ነው።"(112:1-3)

ይህ እና ሌሎች አንቀፆች ክርስትናን የሚኮንኑ ሳይሆኑ ጭማሪዎቹ ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። እስልምና ገና ከጅምሩ ነበር ኢየሱስን

(ዐ.ሰ) ያከበረው፤ ከትሳልቆቹ የአላህ መልዕክተኞች አንዱ ነው ሲል አፅድቋል። አጠር ባለ መልኩ ቢሆንም ቅዱስ ቁርአን ከድንግል መወለዱን (3:47)፣ ተዓምራቱን (7:49)፣ የመሲህነት መሰየሙን (3:45)፣ የመሳሰሉ የወንጌል እውነታዎችን አካቷል። ቅዱስ ቁርአን የማይቀበለው ነገር ኢየሱስ አምላክ ነበር የሚለውን አስተምሮ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም ቅዱስ ቁርአን አይሁዶችን "የአብረሃምን ማህበረሰብ ተው" (2:130)፣ የቶራህ ህግ ቢሰጣቸውም ያልተከተሉ" (62:5) ሲል ኮንኗቸዋል። ይህም በጁዳይዝም ሃይማኖት ላይ ያነጣጠረ አልነበረም። ኢስላም ለጁዳይዝምና ክርስትና ያለው ክብር ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገባ አይደለም። ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ሰብዕናዎች በቅዱስ ቁርአን ውስጥ ተጠቅሰዋል። (ሙሴ በተለየ መልኩ ለ140 ጊዜ የሚሆን ያህል ተጠቅሷል!)[17]

---

[17]ቀደምት ነቢያት እና መልዕክተኞች በሁሉም ነገር በሚያስብል ሁኔታ የነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) አቻ ናቸው- በአምላክ በመመረጣቸው፣ መለኮታዊ ራዕይ በመቀበላቸው፣ መለኮታዊ መልዕክትን ለሰዎች በማድረሳቸው እና ተወዳዳሪ የሌለው ስነ ምግባር ባለጸጎች በመሆናቸው። ነቢዩ ከእርሳቸው በፊት ስላሉት ነቢያትና መልዕክተኞች ያላቸውን አድናቆትና ክብር አስደናቂ ምሳሌዎችን በማንሳት ገልጸዋል።

ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ከእርሳቸው በፊት የመጡትን አፍቅረዋቸዋል፤ ነቢያቱና መልዕክተኞቹ ባዜሙት የእውነት፣ የመልካምነትና የውበት ዜማ ተደስተዋል። መልዕክተኞቹ በተሰጣቸው እያንዳንዱ ቅዱስ መጽሐፍ አምነዋል፤ ስለመልክተኞቹ ድንቅ ባህሪያት ተናግረዋል።

ነቢያቱ የተላበሱት የስነ ምግባር ጥግ በሌላ በአምላክ በተመረጠ ሰው ካልሆነ በስተቀር በማንም ሰው ሊደረስበት ያለመቻሉ ነገር እውነት ነው።

ነገር ግን የኢብራሒም (አብርሃም)፣ የሙሴ እና የእየሱስ ስሞች ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በወረደላቸው ራዕይ (ወሕይ) ከራሳቸው ስም በበለጠ ጊዜ መጠቀሱ ፈጽሞ የሚገመት አይደለም፤ አልተለመደም። በመለኮታዊ መፅሐፍት፣ ስነ ምግባር እና ዝምድና ደምብ አስደናቂ ነገር ነው።





---

በቅዱስ ቁርአን (ሀ) የኢብራሂም ስም ለ48 ጊዜያት፣ (ለ) የሙሴ ስም ለ140 ጊዜያት፣ (ሐ) የኢየሱስ ስም ለ36 ጊዜያት ሲጠቀሱ (መ) የነቢዩ ግን በሙሐመድ ለ4 ጊዜያት በአሕመድ ደግሞ ለአንድ ጊዜ ተጠቅሷል። በአጠቃላይ ነቢዩ በሁለቱ ስሞች የተወሱት ለአምስት ጊዜያት ነው።

**የሰብአዊነት ጥያቄ**

ታላላቆቹና ስኬታማዎቹ የአሜሪካና የአውሮፓ የህዝብ ግንኙነት ተቋማት ተገናኝተው የሰው፣ የቁስና የቴክኒክ ሃይላቸውን በማቀናጀት ስለኢየሱስ፣ ወይም ሙሴ አሊያም አብርሃም ወይም አንድ ነቢይ እጅግ ሳቢ ምስል ቢያቀርቡ፣ የዓለም ህዝብ ስለዚህ ስራና ጥረት ምን ሊል ይችላል? ያለምንም ጥርጥር ድንቅ አስተሳሰብ፣ ጥርት ያለና ከጥቅም የነጻ ጥረት እና ለተከበሩ ነቢያት ታማኝ መሆን የሚል አስተያየት ይሰጣል። ለዚህ ተግባር የሚገባ ሌሎች የአድናቆት አስተያየቶች ሊሰጡም ይችላሉ።

ይህ ምናባዊ የህዝብ ግንኙነት ዕቅድ ከሆነ፣ ከዚህ በአቀራቡ ድምቀት፣ በይዘቱ ጥልቅነት፣ በዘዬው እውነተኛነት፣ ከአገላለፁ ቅርብነትና በጊዜው ቆይታ በሚለዩዋች ጊዜ የሚበልጥ ዕውነታ አለ።

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከእርሳቸው በፊት የነበሩትን ነቢያትና መልዕክተኞች እጅግ አንጸባራቂ አድርገው ነው ያቀረቧቸው። የነቢያቱ ገለጻ ሆነ አቀራረብ ለኃላ ቀርነት እና ብቃት ማነስ የተጋለጠ የሕዝብ ግንኙነት ዘመቻም ውጤት አይደለም። ይህ በቅዱስ ቁርአን ተካቷል። ስለነቢያቱ ገለጻ እና ቀረባ በሳምንታት፣ በወራት አሊያም በዓመት የተገደበ ዘመቻ አይደለም፤ ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጀምሮ እስከ መጨረሻው ዕለት የተሰጠ ነው። ነቢያቱ የቀረቡበት መንገድም የማይበረሬ መደርደሪያዎችን የሚያደምቁ ወይም ሙዝየም ውስጥ ሊገባ በሚችሉ ኋላ ቀር ቃላት ወይም ተጎጂ ሰነድ ሳይሆን በየዕለቱ በሚነበበው፣ በሶላት ውስጥ በሚነበነበው፣ በት/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በሚጠናው፣ በሬዲዮዎችና በቴሌቪዥኖች በሚደመጠው ቅዱስ ቁርአን ነው። ታዲያ ለዚህ ተግባር የሰው ዘር ምን አይነት አስተያየት ይሰጥ ይሆን? አቅራቢውስ እንዴት ነው መታየትና አቀባበል ሊደረግላቸው የሚገባው? (*Relationships of the Great*፣ በZain Al-abdeen Al-Rikabi, ገጽ 23-24)

የቅዱስ ቁርአን ቅሬታ በጁዳይዝም ሆነ ክርስትና ላይ አይደለም። እንደውም ሃይማኖቶች ከእስልምና ጋር አንድ እንደሆኑ ነው የሚያስተምረው- *"በዚያ ወደኛ በተወረደው፣ ወደናንተም በተወረደው አመንን፤ አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው።"* (29:46) ኢስላም በአይሁዶችና ክርስቲያኖች ላይ ያለው ቅሬታ *"የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በአላህና ወደኛ በተወረደው በፊትም በተወረደው ለማመናችን፣ አብዛኞቻችሁም አመጠኞች በመሆናችሁ እንጂ (ሌላን ነገር) ከኛ ትጠላላችሁ?"* (5:57-59) ነው።

አምላክ በአይሁዶች ላይ የዋለውን *"ጸጋየንና እኔም በዓለማት ላይ ያበለጥኳችሁ መሆኔን"*(2:47) አስታውሶ እያለ ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን ሃይማኖታቸውን ትተው፣ በቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ውስጥ ያለውን እውነታ ያምታቱ ብሎ ሁለቱንም ስብስቦች "ከጌታቸውም ወደነሱ የተወረደውን መጽሐፍ ባቋቋሙ (በሠሩበት)"(5:66) ብሎ ሲወቅሳቸው፤ ከዚህ በፊት ነብዩ ኢሳያስ አይሁዶችን *"እናንተ ኀጢአተኛ ሕዝብ፣ በደል የሞላበት ወገን፣ ክፉ አድራጊ ዘር፣ ምግባረ ብልሹ ልጆች ወዮላችሁ! እግዚያብሔርን ትተዋል፤ የእስራኤልን ቅዱስ አቃለዋል፤ ጀርባቸውን በእርሱ ላይ አዙረዋል።"* (ኢሳያስ 1:4)፣ መጥመቁ ዩሀንስ *"እናንተ የእፉኝት ልጆች፣ ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን መከራችሁ? እንግዲህ ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤ ደግሞም በልባችሁ፣ 'አብርሃም አባታችን አለን' ማለትን አትጀምሩ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ማንሳት እንደሚችል እነግራችኋለሁና።"*(ሉቃስ 3:7-8)፣ ኢየሱስ *"እናንተ ግብዞች፤ ኢሳይያስ ስለ እናንተ እንዲህ ብሎ በትንቢት የተናገረው ትክክል ነው፤ 'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ በከንቱ ያመልኩኛል፣ ትምህርታቸውም የሰው ሥርዓት ነው።'"* (ማቴዎስ 15:7-9) ያደረጉትን ፈለግ መከተሉ ነው። ታዲያ አንድ ነብይ ከመልዕክተኛነት አንፃር ያለበት ኃላፊነት ምን ሊሆን ነው?





ኢስላም ከመጽሐፉ ባለቤቶች ጋ ያለው የማይታረቅ ልዩነት እንዳለ ሆኖ የሃይማኖቶችን መለያየት ፈፅሞ አልተቀበለም። እንደውም "ክርስትያኖች ስህተት ናቸው!" ለሚሉ አይሁዶች እንዲሁ "አይሁዶች ትክክል አይደሉም!" ለሚሉ ክርስትያኖች (2:113)፣ "ከሁለቱ አንዳችሁ ወደ ገነት አትገቡም" ለሚሉ ሁለቱ ስብስቦች (2:111) ቅዱስ ቁርአን ማስታረቂያ አምጥቷል።

> *"የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በኛና በናንተ መካከል ትክክል ወደሆነችው ቃል ኑ፤ (እርሷም) አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው በላቸው። እምቢ ቢሉም፦እኛ እስላሞች መሆናችንን መስክሩ በላቸው።" (3:64).*

ይህ የማስታረቂያ ሃሳብ አሁንም በሶስቱ "የአብረሃም እምነት" ተከታዮች መካከል ሊሰርፅ አለመቻሉ በጣም አሳዛኝ ነው።

* * *

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መካን ከተቆጣጠሩ በኋላ ሲያጠቋቸው ለነበሩት በሙሉ ምህረትን አድርገዋል፤ የቁረየሾች የጎሳ ህግ ቁረየሾቹ የእርሳቸው ባሪያ እንዲሆኑ ቢያስገድዳቸውም። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመካ ነዋሪዎች ነፃ እንደሆኑ አወጁ። አንድም ሰው እስልምናን እንዲቀበል አልተገደደም።

# ጂሐድ እና ሽብር

## በፕ/ር ጆን ኤል ኤስፖሲቶ[18]

በጂሐድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን አራት ሙስሊሞች በተጋባዥነት የቀረቡበት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ብትመለከቱ፣ "ጂሐድ ምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ አራት የተለያዩ ምላሾች ሊታደምጡ ትችላላችሁ። አንደኛው ጂሐድ ማለት መልካም ሕይወት ለመምራት፣ በመደበኛነት ለመስገድና ለመጾም፣ መልካም የትዳር ጓደኛ እና የቤተሰብ አባል ለመሆን የሚደረግ ጥረት ነው ሊል ይችላል። ሌላው የኢስላምን መልዕክት ለሰዎች ለማዳረስ ጠንክሮ መሥራት ሊል ሶስተኛው በፍልስጤም፣ ካሽሚር፣ ቼቺኒያ ወይም በኮሶቮ እየተጨቆኑና በደል እየደረሰባቸው ያሉትን ሙስሊሞች ነፃ ለማውጣት መታገል ነው የሚል ይሆናል። የመጨረሻው ተናጋሪ፣ እንደ ኦሳማ ቢን ላዲን ለመሰለው፣ በሙስሊም ዓለም ውስጥ ያሉት መንግሥታት መገልበጥና አሜሪካን ማጥቃት ሊሆን ይችላል። እነዚ አረዳዶች የቱን ያህል የተለያዩ ቢሆኑም ጂሐድ ለአሁን ጊዜ ሙስሊሞች ያለውን ማዕከላዊ ቦታ በአንድነት ይመሰክራሉ። ጂሐድ የኢስላም ዐ ኛ ዕንሰ ሃሳብ ወይም እምነት፣ የአምላክ ፈቃድ ተከታይነት ማስመስከ ያ ወይም የአማኝነት መለያ ነው።

ከሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ ጂሐድ የሚለው ቃል በሠፊው ጥቅም ላይ ውሏል። ነፃ አውጪዎች፣ ታጋዮች እና ሽብርተኞች ተልዕኮዋቸውን ሕጋዊ ለማድረግና አባላትን ለመመልመል

[18] ፕ/ር ጆን ኤል ኤስፖሲቶ በሃይማኖቶች እና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ፕሮፌሰር ሲሆን በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ፣ ዋልሽ ስኩል ኦፍ ፎሬይን ሰርቪስ የሙስሊም-ክርስቲያን ግብብ ማዕከል መስራች መሪ ነው። በርካታ መፅሐፍትን ደርሶ ለንባብ ያበቃ ሲሆን UNHOLY WAR: Terror in the name of ISLAM ከሚለው መፅሐፉ ይህ ምዕራፍ ተተርጉሟል።





ተጠቅመውበታል። የአፍጋኒስታን ሙጃሂዲኖች፣ ጣሊባኖች እና የሰሜን ሕብረቶች የውጪ ኃይሎችን ለመታገል ሆነ እርስ በርስ ለመጫረስ ጂሐድ አውጀዋል። በካሽሚር፣ ቼቺኒያ፣ ዳጋስታን፣ ደቡብ ፊሊፒንስ፣ ቦስኒያ እና ኮሶቮ የሚገኙ ሙስሊሞች ትግላቸውን ጂሐድ ብለው ጠርተውታል። ሒዝቦላ፣ ሐማስ እና የፍልስጤሙ ኢስላሚክ ጂሐድ ከእስራኤል ጋ የሚያደርጉት ጦርነት ለእነርሱ ጂሐድ ነው። የአልጄሪያው ታጣቂ እስላማዊ ግሩፕ (ሰብሰብ) የሃገሪቱን መንግሥት በሽብር ጂሐድ ወጥሮታል። ኦሳማ ቢን ላዲንም በሙስሊም መንግስታትና በምዕራቡ ላይ ዓለም አቀፍ ጂሐድ አውጇል።

የጂሐድ አስፈላጊነት ከቅዱስ ቁርአን በአምላክ መንገድ ላይ ታገሉ ከሚለው ትዕዛዝና ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ቀደምት ተከታዮቻቸው ምሳሌ የተገኘ ነው። እነዚሁ ቅዱስ ቁርአን፣ የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ቀደምት ተከታዮቻቸው ምሳሌ የሙስሊሞች እምነት መሠረቶች ምንጭ ናቸው። ጂሐድ በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ በሥፋት ጥቅም ላይ የዋለና የተበደለ፣ ብዙ አንድምታ ያለው ዕንሰ ሀሳብ ነው። ምንም እንኳ ጂሐድ በኢስላማዊ ትውፊት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ክፍል ቢሆንም ከቅርብ አመታት ወዲህ ግን አንዳንድ ሙስሊሞች ዓለም አቀፍ ኢስላማዊ አብዮትን ለማፋፋም ሁሉም ሙስሊሞች ሊሳተፉበት የሚገባ ሁሉን አቀፍ ኃይማኖታዊ ግዴታ ነው የሚል አቋም ይዘዋል።

ዛሬን እዚህ በርካታ ሙስሊሞች እየኖሩበት ያለው ሁኔታ ጂሐድ ያስፈልገዋል ብለው ያምናሉ። አካባቢያቸውን ሲመለከቱ በሙስና የነቀዙ አምባገነን መንግሥታት እና ጥቂት ቱጃሮች፣ ከአገራቸው (በሔራዊ) ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ኪስ በመሙላት የተጠመዱ ትናንሽ ስግብግቦች፣ በምዕራቡ ዓለም ዕሴቶች፣ አልባሳት፣ ሙዚቃ፣ ቴሌቪዥንና ፊልሞች የታጨቀ ዓለም ነው የሚያዩት። የምዕራቡ ዓለም መንግሥታት የሚታዩት እንደ ጨቋኝ መንግሥታት ደጋፊዎች፣ የክልሉን ሰብአዊና ተፈጥሮዋዊ አንጡራ ሐብት በዝባዦች፣ ባህላቸውን አራቋቾች፣ በመረጡት መንግሥት የመመራትንና ፍትሃዊ ማህበረሰብ የመገንባት ፍላጎታቸውን ገፋፊዎች

ነው። ብዙ ሙስሊሞች የሙስሊሞችን ኃይል ለመመለስና ዕድገታቸውን ዕውን ለማድረግ ወደ ኢስላም መመለስ፣ ኢስላማዊ መንግሥት መመሥረትና እስላማዊ ማህበረሰብ መገንባት እለበት ብለው ያምናሉ። ጥቂት ሙስሊሞች ደግሞ የለውጥ ራዕያቸውን ከጦር መሣሪያ ጋ በማቀናጀት በአገር ውስጥም ሆነ ውጪ የሚገኙትን ሙስሊሞች ነፃ የሚያወጣ የአምላክ ጦር ለመፍጠር ቀስቅሰዋል።

ጂሐድ ከአንድ በላይ ትርጉሞች ካሉት እንዴት ነው በትርጉሞቹ ላይ ግንዛቤ የሚወሰድባቸው? የትኛው አረዳድ ትክክል ነው? የትኛው(ኞቹ) ትርጉም(ሞች) በጎ መሻሻሎችንና ለውጦችን ይደግፋል(ሉ)? የትኞቹስ አክራሪነትንና ሽብርተኝነት ይሁንታ ለማስጠት ጥቅም ላይ ይውላሉ? እነዚህ ጥያቄዎች አዲስ አይደሉም። ሙስሊሞች ለዘመናት ሲከራከሩባቸው ኖረዋል።

ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው የሙስሊም ማህበረሰብ ታሪክ ቅዱስ ቁርአን ስለጂሐድ በሚያስተምረው አስተምህሮት ማዕቀፍ ሊነበብ ይችላል። የቅዱስ ቁርአን አስተምሮት ኢስላማዊ ማንነት ለመገንባት፣ ለጽድቅና፣ ለመንፈሳዊና አካላዊ መነቃቃትና መሥፋፋት እንዲሁም ራስን ለመከላከል መሠረት ነው። ጂሀድ በምቾት እና ቅምጥል አስቸጋሪና ውስብስብ ሕይወት ላይ የሚደረግ ትግል፣ በጥሩ ሥነ ምግባር የታነፀ እና ጻድቅ ማንነትን ለመገንባት በእኩይ ውስጣዊ ማንነት ላይ የታወጀ ትግል፣ መልካም ተግባራትን ለመስራት እንዲሁም ማህበረሰብን ለማደስ የሚደረግ ያላሰለሰ ጥረት የሚል አንድምታ አለው። አንድ ሰው ከሚኖርበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ኢፍታሃዊነትና ጭቆናን መዋጋት፣ ኢስላምን ማስፋፋትና መጠበቅ ግድ ከሆነም አካላዊ (በጦር መሳሪያ የታገዘ) ትግል እንዲያደርግ ማስተማር የሚል ትርጉምም ይኖረዋል።

ሁለቱ የጂሀድ አተገባበሮች- መንፈሳዊውና አካላዊው- በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታዋቂ ንግግር ጸድቋል። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እጅግ ብዙ ዋጋ





ካስከፈላቸው ጦርነት ሲመለሱ ለተከታዮቻቸው "ከትንሹ ጂሃድ ወደ ትልቁ ጂሃድ ተመለስን"[19] ይሉዋቸዋል። ትልቁ ጂሃድ አንድ ሰው በራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ ችጋራምነትና እኩይነት ላይ የሚያደርገው ትግል ነው።

በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ ጂሃድ የተተረጎመበትን የተለያዩ መንገዶች መረዳት በዕንፈኛ አካላት እና በብዙሃኑ ሙስሊም መካከል ያለውን ልዩነት እንድናይ ያስችለናል።

ዑሳማ ቢን ላዲን ሆነ ሌሎች የአሸባሪ ቡድኖች መሪዎች ሲናገሩ አውቀው ሆነ ሳያውቁ አጀንዳቸውንና ስልታቸውን ሕጋዊ ለማድረግ ወደ ኋላ ይመለሳሉ፤ ራሳቸውን በነቢዩ ጥላ ሥር ይከልላሉ። ወታደራዊ የጂሀድ አመለካከታቸውን ግን ከመካከለኛው ዘመን የሃይማኖት ሊቅ እና የሕግ ሰው ኢብን ተይሚያህ ወይም ከዘመነኛው አብዮታዊ ኢስላም መሪ ሰይድ ቁጥብ አመለካከት ጋ ያገናኙታል። የቅዱስ ጦርነት ታሪክን እየደገሙ ወይስ የራሳቸውን ኢቅዱሳዊ የሽብር ጦርነት ፈጠራ አጋዥ እየፈለጉ?

በአሁኑ ወቅት ሙስሊሞች እያካሄዱት ያለው ወደ ኢስላም መንፈስ የመመለስ ትግል ለዘመናት ሲያደርጉት የነበረ ነው። ጂሃድን የመንግሥት ባለሥልጣናት ሆነ አነርሱን የሚታገሉት፣ "ውስጠኞቹ" እና "ውጪኞቹ" መጠቀም የጀመሩት ገና ከጅምሩ ነበር። የቀደምት ሙስሊሞች ታሪክ አሁን እየተካሄደ ላለው ነገር ግልፅ የሆነ አተያይና ታሪካዊ አረዳድ ይሰጠናል።

---

[19] ሙስሊሞች ለዚህ የነቢዩ ታላቅ ንግግር ከከንፈር ንብነባ በስተቀር ተገቢውን ዋጋ የሰጡት አይመስልም። አሌክስ ደ ዋላስ በትክክል እንደተመለከተው በአሁኑ ወቅት በሙስሊሙ ዓለም እየታየ ያለው ምስቅልቅል ሙስሊም ተዋጊዎች በዚህ ንግግር ፈተና መውቀዳቸው ነው። "በተግባራዊ ጂሃድ ለተሳተፉ ሙጃሂዲኖች የድል ጊዜ እጅግ አደገኛ ነገር ነው። ይህ የሚሆነው ነቢዩ ሙሐመድ በትክክል "ትልቁ ጂሃድ" ብለው በጠሩት ሲፈተኑ ነው። ሥልጣን የጨበጡ እስላማዊ ጦረኞች- በሱዳን ይሁን አፍጋኒስታን- ይህ የእነርሱ ታላቅ ፈተና እና ታላቅ ውድቀት ሆኖ አግኝተውታል።" De Waal, Alex (ed) (2004). *Islamism and its Enemies in the Horn of Africa.* SHAMA BOOKS, ADDIS ABABA. ገጽ 8

እናም ጂሃድን ለመረዳት ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ቅዱስ ቁርአን መጀመር አለብን።

## የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጂሐድ

ኢስላምና ቅዱስ ቁርአን ልክ እንደሌሎች የዓለም ታላላቅ ኃይማኖቶችና ቅዱስ መጽሐፎቻቸው ለተከታዮቹ ለሁሉ ጊዜና ቦታ የሚሆኑ መመሪያዎችን የሚሰጡ ሁለንተናዊ መልዕክት የያዘ ነው። በተለያዩ ጊዜ እና ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ አማኞች ስላሉበት ተጨባጭ ትርጉም እና ምሪት የሰጡዋቸውን አስተምሮቶችን፣ መርሆችንና ዕሴቶችን ከሃይማኖታቸውና ቅዱስ መጽሐፍቶቻቸው አግኝተዋል። አይሁዶች የሒብሪው ቅዱስ መጽሐፍቶቻቸውን ሲያገላብጡ እንዴት እምነታቸውንና ማህበረሰባቸውን ሊጠበቁ እንሚችሉ ከዳዊትና ኢያሱ ታሪኮች መመሪያዎችን ያገኛሉ። ስለሰላም እና አስፈላጊነቱ የሚሰብኩና የሚያስረዱዋቸውን አንቀፆች ለማግኘት ብዙም አይቸገሩም። ክርስቲያኖችንም ሰላማዊነትን እና ፍትሃዊ ጦርነትን የሚያቀነቅኑ ትውፊቶች ሞልተዋቸዋል። እንደዚሁም ሁሉ ቅዱስ ቁርአንና የነቢዩ ሱና[20] ሰዎች የተለያዩ ብሔሮችና ሕዝቦች በሞሉባት ዓለማችን በሰላም ሊያኗኑሯቸው የሚያስችሏቸውን ንድፈ ሐሳቦች ይሰጣሉ።

ኢስላም የተነሳበት የሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከባቢ ጦርነት ቋሚ ሁነት ነበር። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የኖሩበትና የአምላክን ወሕይ የተቀበሉባት አረቢያና የመካ ከተማ የጎሳ ግጭቶችና የበቀል ግድያዎች የነገሱባቸው ነበሩ። አረቢያ የምትገኝበት ሰፊው የቅርብ ምሥራቅ ክልል በጦርነት በሚታወቁ የባዛንታይንና ፋርስ ኢምፓየሮች የተከፈለ ነበር። ሁለቱ ኢምፓየሮች የወቅቱን ታዋቂ ዓለም ጠቅልሎ ለመግዛት የሚፎካከሩ ነበሩ።

---

[20] የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር፣ ተግባር እና ሌሎች ሲያደርጉ አይተው በዝምታ ያለፏዋቸው።





የሰባተኛ መቶ ክፍለ ዘመን አረቢያ ወደ ምስራቁ ዓለም በተዘረጋ አትራፊ የንግድ መሥመር መካከል ትገኛለች። በመሆኑም የሁለቱ ተፎካካሪ ኢምፓየሮች ተጨማሪ የፉክክርና ተደጋጋሚ ጣልቃ ገብነት መነሰኤ ነበረች። ኢስላም የተነሳውና የተስፋፋው የፖለቲካ አጣብቂኝ፣ ግጭት በሞላባት አረቢያ እና በኢምፓየሮች ጦርነት ውስጥ ነበር። የሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አስተምሮት በዚህ ውጥንቅጥ ውስጥ ጭማሪ በመሆኑም አንድ የግጭት ምክንያት መሆኑ አልቀረም።

የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተሐድሶ መልዕክት በኃይማኖትና የፖለቲካ ሥርዓቱ አራማጆች፣ የጎሳ መሪዎች እና የማህበረሰቡ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ልክ እንደ አሞጽ እና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አዲሱ ኃይማኖታዊ መልዕክት የነበረውን ሥርዓት የሚቃወምና ለማህበረሰቡ እጅግ ደካማ አባላት- ሴቶች፣ ልጆች እና ወላጅ አልባዎች- ፍትህ ጠበቃ የቆመ ነበር። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ቅዱስ ቁርአን የአረቢያን ጣዖታት እና ባለብዙ አማልክት አምልኮን ከመኮነናቸውም በላይ በመካ ማህበረሰብ ውስጥ የነገሰውን አስቀያሚ ቁስ አምልኮ፣ ክፋት እና ንቅዘት የመሃይምነት እና ኢአማኒነት መገለጫ ስለሆነ ጃሂሊያ የሚል ስያሜ ሰጥተውታል። ጃሂሊያ በትርጉሞች የበለጸገ ቃል ሲሆን የዚህ ዘመን አጥባቂዎች የምዕራቡን ዓለም ለመግለፅ ይጠቀሙበታል።

የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነቢያዊ ጥሪ ሰዎች ማህበረሰባቸውን ለመለወጥ እንዲታገሉ (ጂሃድ እንዲያደርጉ) እና መልካም ሕይወት እንዲኖሩ፣ ታማኝነታቸው ለነገዶቻቸው ሳይሆን ለሃይማኖታቸው እንዲሆን ነበር። እያንዳንዱ ሰው ተጠያቂነቱ ለነገዱ ሕግ ሳይሆን ለመለኮታዊ ሕግ መሆን አለበት የሚለው የማይታጠፍ አስተምሮቱ የአረቢያ ማህበረሰብን ከመሠረቱ አናግቷል። የሙሐመድ የአምላክ መልዕክተኛነት ደረጃ እና ከተከታዮቻቸው ጋ በማህበረሰቡ ንቅዘቶች ላይ የከፈቱት ጦርነት የኃይል ባለቤቶቹን (ከሃዲዎቹን) ሥጋት ውስጥ ጥሏል። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በኃይማኖትና አምልኮ፣ በኢኮኖሚያዊ ግንኙነትና እንቅስቃሴ፣ በወንድና ሴት

እንዲሁም ቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ሥር ነቃይ ፕሮግራም ይዘው መጥተዋል። ቅዱስ ቁርአን የአረቦቹን የጣዖት አምልኮ ሽሮ አንድ አምላክ ብቻ ነው ያለው ሲል አወጀ። የአብዛኛው ነጋዴ ብልሹ ተግባራት እና በወላጅ አልባዎች ላይ እየተፈጸመ የነበረውን ብዝበዛና ንብረት ቅሚያ አጥብቆ ኮንኗል። የሕጻናት ግድያን አውግዞ የወንዶችንና ሴቶችን ኃይማኖታዊ እኩልነት ሰብኳል። ለሴቶች የትዳር እና የውርስ መብት ሰጥቷል። እንደነዚህ አይነቶችን ጥልቅ ተግደርዳሪ መልዕክቶችንና የመልካምነት ተልእኮ ሕያው አድርጎ ለማቆየት፣ እነርሱም በሕይወት ለመቆየት መዋጋት፣ ጂሃድ ማወጅ ነበረባቸው።

የዚህ ጥንስስ እስላማዊ ማህበረሰብ አርአያ ለማህበረሰብ ጠጋኞች ጥልቅ ትርጉም አለው። የሙስሊሙ ማህበረሰብ ሊቀዳውና ሊሆን የሚገባው አምሳል ማህበረሰብ ነው። ለ'ዚህ ማህበረሰብ በፊት የተነሱት ጠጋኞች የነበራቸውን፣ ወደፊት የሚነሱት ደግሞ ሊኖራው የሚገባውን ጥልቅ ክብርና አመለካከት በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ከተነሳው ሰይድ ቁጥብ ንግግር ማየት እንችላለን።

> *"በአንድ ወቅት ይህ መልዕክት (ቅዱስ ቁርአን) በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አምሳያ የሌለውን ልዩ ትውልድ- የነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ጓደኞች ትውልድ ፈጥሯል። ከ'ዚያ በኋላ እንደዚያ ልቅ ትውልድ ሊፈጠር አልቻለም።"*

## ሒጅራ እና ጂሐድ፡ ለጭቆናና ግጭት የተሰጠ ምላሽ

የመጀመሪያዎቹ አሥር የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የስብከት ዓመታት በታላቅ ተቋውሞና ጭቆና የተሞሉ ነበሩ። ለመልዕክቱ የተሰጠው አዎንታዊ ምላሽ አናሳ ነበር። አማኞቹ አናሳ ከመሆናቸው በላይ በከፍተኛ ቋሚ ጫና ሥር ነበሩ። ይህ የነቢዩ ጥንስስ ማህበረሰብ ለጭቆናና በደል የሰጠው ምላሽ፤ ጭቆናና ተቃውሞ ለደረሰባቸው፣ የማመን መብታቸው አደጋ ውስጥ ለወደቀባቸው፣ የዕምነት ማህበረሰባቸው ደህንነትና ቀጣይነት ለሚያሳስባቸው





ሁሉ ትምህርት የሚወስዱበት ተምሳሌት ነው። የሂጅራ (ከኢ-ኢስላማዊ አሰቃይ ጃሂሊያ ቦታ መሰደድ) እና ጂሐድ መንትያ ሃሳቦች ተፈጠሩ። ፋታ ባልነበረው ስቅየትና በደል ውስጥ የነበሩት ነቢዩ እና ተከታዮቻቸው በ622 ከመካ በግምት በ402 ኪሎ ሜትሮች ላይ ወደምትገኘው የስሪብ ተሰደዱ፤ ሂጅራ አደረጉ። ለዚህ ስደት በሃይማኖቱ የተሰጠውን እስኪል ቦታ ለመረዳት የሙስሊሞች የዘመን አቆጣጠር ጅማሬ፣ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከተወለዱበት ወይም መልእክቱን ከተቀበሉበት ዕለት ይልቅ ከኢስላማዊ ማህበረሰብ ለመፈጠር ምክንያት ከሆነው ከዚህ ክስተት ጋ መቆራኘቱን ማየት ይቻላል።

በነገድና ጎሳ ግጭት ስትታመስ በነበረችው አረቢያ ውስጥ ሰዎችን ከነገድና ከጎሳ አባልነት ከሚገኝ ደህንነትና ምቾት አውጥቶ በሠፊ የኢስላም ርዕዮተ ዓለም ጥላ ሥር ማሰባሰብ ሌላው የነቢዩ የለውጥ ፅንሰ ሀሳብ ነበር። ይህ ፅንሰ ሀሳብ በወቅቱ ለነበረው ሥርዓተ ማህበር ምን ያህል አደጋ እንደሆነ መገመት አይከብድም። ከፖለቲከኞችና የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል። በመሆኑም በተለምዶ "የመከላከል ጂሃድ" ተብለው የሚታወቁ የቅዱስ ቁርአን አናቅዕት መውረድ የጀመሩት ሙስሊሞች ወደ መዲና እንደተሰደዱ ነበር። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ተከታዮቻቸው ሕልውናቸውን ለማቆየት ሲሉ መዋጋት ግድ ሲሆንባቸው ፍቃድ ተሠጣቸው። *"ለነዚያ ለሚገድሉት (ምእመናን) እነርሱ የተበደሉ በመሆናቸው (መጋደል) ተፈቀደላቸው፤ አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በርግጥ ቻይ ነው።"* (22:39)

በዚህም አንቀፅ "የመከላከል ጂሃድ" አፅንኦት ተሰጥቶታል *"እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሐዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፤ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።"* (2:190)

ብዙሃኑ ሙስሊም ሆነ የተወሰኑት ፅንፈኞቹ "ቅዱስ ጦረኞች" ሂጅራንና ጂሃድን ለየዓላማቸው ይጠቀሙበታል።

## ራስን የመከላከልና ተስፋፊ ጂሃድ

ከ622 ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ባሉት አስር ዓመታት ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመዲና ኃይላቸው ሲጠናከር የዐረብ ነገዶችን አንድ አድርገዋል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ በተከሰቱ ወሳኝ ክስተቶች ስለ ጂሃድ መሪ መርህዎች የሚናገሩ አንቀፆች ከአምላክ ይወርዱ ነበር። የሙስሊሙ ማህበረሰብ እያደገ ሲመጣ ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ የስልጣን ባለቤትነት፣ ዓመፅና የእርስ በርስ ጦርነት እንዴት ይስተናገድ? በሰላምና ጦርነት ወቅት ተገቢው ባህሪይ ምን መሆን አለበት? መስፋፋትንና (አገር) ምርኪያን፣ አመፅንና መከላከልን እንዴት ህጋዊ እና አመክኖዋዊ ማድረግ ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎች የተነሱት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአካል ከተለዩ ብዙም ሳይቆይ ነበር። ለነዚህ ጥያቄዎች ከቅዱስ ቁርአን መነሻነት መልስ ይሠጥባቸው ነበር። ቅዱስ ቁርአን ጦርነትን በተመለከተ ዝርዝር መርሆዎችንና መመሪያዎችን ሠጥቷል- ማን መዋጋት አለበት፣ እነማንስ ያለመዋጋት ፍቃድ ተሰጥቷቸዋል (48:17፣ 9:91)፤ ጠላትነት መቼ መቆም አለበት (2:192)፤ የጦር እስረኞች እንዴት መያዝ አለባቸው (47:4)። በ2:194 ላይ እንደወረደው አንቀፅና መሰሎቹ ተመጣጣኝ ኃይልን ስለመጠቀም አፅንኦት ይሠጣሉ- *"ክብሮችም ሁሉ ተመሳሳዮች ናቸው፤ በናንተም ላይ (በተከበረው ወር) ወሰን ያለፈባችሁን ሰው፣ በናንተ ላይ ወሰን ባለፈው ብጤ በርሱ ላይ ወሰን እለፉበት"*። ሌሎች ደግሞ ሰላም ስለማስፈን ጠንካራ ድጋፍ ይሰጣሉ። *"ወደ ዕርቅም ቢዘነበሉ ወደ እርሷ ተዘንበል"* (8:61)። በተጨማሪም *"…አላህም በሻ ኖሮ በእናንተ ላይ ሃይል በሰጣቸውና በተጋደሉዋችሁ ነበር፤ ቢተዋችሁና ባይጋደሉዋችሁም ወደ እናንተም ዕርቅን ቢያቀርቡ፣ አላህ ለናንተ በነርሱ ላይ (የመጋደል) መንገድን አላደረገም።"*(4:90) እና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል።

በጦርነት ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ያልሆኑትን ሴቶችን እና ልጆችን፣ እንዲሁም በጦርነት ላይ እስካልተሳተፉ ድረስ መነኩሴዎችንና የኃይማኖት አባቶችን ማጥቃት የተከለከለው ገና በጠዋቱ ነበር። የነቢዩ ምሳሌዎችም





የሙስሊሙ ማህበረሰብ እንዴት መንቀሳቀስ አለበት ለሚለው ጥያቄ መልስ ሰጥተዋል። (የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንቅስቃሴዎች የተዘገቡበት የታሪክ ስብስብ ሐዲስ ይባላል።) እስካሁን ድረስ ሙስሊሞች በተገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ በሚያጋጥሙዋቸው ሁነቶች ላይ እንዴት ውሳኔ መስጠት፣ ምን አይነት ባህሪዎችን ማዳበር እንዳለባቸው ምሪት ሲሰጡ ነበር። ወደ ፊትም ይሠጣሉ።

በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚያም በቀደምት ተከታዮቹ አመራር የሙስሊሙ ማህበረሰብ በከፍተኛ ፍጥነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሮማ ኢምፓየር የበለጠ ከስሜን አፍሪካ እስከ ሕንድ በተሰጠጠ ክልል ለመስፋፋት ችለዋል። በተራዘመ ጦርነት የተዳከሙትን የሮማንና ፋርስ ኢምፓየሮችን በቁጥጥራቸው ሥር ያዋሉዋቸው ወዲያውኑ ነበር።

ቅዱስ ቁርአን በግልጽ "በኃይማኖት ማስገደድ የለም" (2:256) ብሎ ስለደነገገ ለሙስሊሞች መስፋፋትና ምርኪያ መግፍኤ ኃይማኖታዊ ምክንያት- ሰዎችን በኃይል ወደ እስልምና ለማስገባት- ሳይሆን መሃይምነትን እና እምነት የለሽነትን በፍትሃዊ ማህበረሰብ እንዲለወጥ የጽድቅ ሥርዓቱን ማስፋፋት ነበር። ኃይማኖትን ለማስፋፋት የሚደረግ ጂሃድ የአምላክን ቃል እና ፍትሃዊ ሥርዓትን ለሰዎች ከማዳረስ የኢስላም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ጋ የተያያዘ ነው።

> *"ከናንተም ወደ በጎ ነገር የሚጠሩ፣ በመልካም ሥራም የሚያዙ፣ ከክፉም ነገር የሚከለክሉ ሕዝቦችም ይኑሩ። እነዚያ እነርሱ የሚድኑ ናቸው።"(3:104) እና "ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ፤ በጽድቅም ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ" (3:110)*

የኢስላምን አምሳሎች (Ideals) ለመዘርጋት ወይም ለመከላከል የተሰው ሰማዕት በኢስላም ልዩ ደረጃ አላቸው። ቅዱስ ቁርአን የሰማዕትን ሃሳብ የሚደግፉና በትግል ወቅት የወደቁትን የሚያፅናኑ ብዙ አናቅፅት

አሉት፡፡ "በአላህ መንገድ ብትገደሉ ወይም ብትሞቱ፣ ከአላህ የሆነው ምህረትና እዝነት (እነርሱ) ከሚሰበስቡት ሀብት በእርግጥ በላጭ ነው፡፡"(3፡157) እና "እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ህያው ናቸው፤ ይመገባሉ፡፡" (3፡169) እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል፡፡ የሱኒና ሺዓ ትወፊቶች ለሰማዕትነት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ ሱኒዎች ቀደምት ሙስሊሞች ከመካ ዓረቦች እና ከጃሂሊያ እምነት የለሽ ባህል ጋ ሳደረጉት ትግል ትኩረት ሲሰጡ ሺዓዎች ደግሞ ቀደምት ኢማሞች ኢስላማዊ ዕሴቶችን በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ለማፅናት ያደረጉትን ትግል በየዓመቱ ያስታውሳሉ፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ለኢስላም ሲሉ የሞቱ ስለሚያገኙት ምንዳዎች ብዙ ተናግረዋል፡፡ ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት ሰማዕት ከተቀሩት የሚለዩባቸውን ነጥቦች ኢስላማዊ አስተምሮቶች በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡

ከኢስላማዊው ማህበረሰብ ዕድገት፣ መስፋፋትና መበልፀግ ጋ የመሪዎች የኃይል አጠቃቀምና እና የአኗኗር ዘይቤ ምን መምሰል አለበት እንዲሁም ቅዱስ ቁርአን ስለ "የኢስላም ቀጥተኛው መንገድ" ምን ይላል የሚሉ ጥያቄዎች በመነሳታቸው የኃይማኖት ሊቆች (ዓሊሞች) ተፈጠሩ፡፡ ዓሊሞች የሙስሊም ሕይወት መመሪያ የሆነውን ሸሪዓ (ኢስላማዊ ሕግ) አዳበሩ፡፡

ለዓመታት የሸሪዓ እና የሕግ ባለሙያዎች ጂሃድ መቼ መታወጅና መቆም እንዳለበት ወሳኝ ሆነዋል፡፡ ሙስሊም የፖለቲካ መሪዎች ጂሃድ ሲያውጁ ሙፍቲህ[21] እየተባሉ የሚጠሩት የሕግ ሊሂቃን ስለጂሃዱ ሕጋዊነት እና ሕገ ወጥነት ህጋዊ አስተያየት (ፈተዋ) ይሰጣሉ፡፡ ይህ ሂደት እስካሁን ድረስ ቀጥሏል፡፡ ለምሳሌ በባህረ ሰላጤው ጦርነት ወቅት ሳዳም ሁሴን ባወጀው ጂሃድ በተቃራኒ ከአሜሪካ ጎን ለመቆም ሙስሊም መሪዎች

[21] የእስልምናን ዕውቀት ጠንቅቆ የተረዳና በሙስሊሙ ማህበረሰብ ለሚፈጠርማንረኛውም አይነት ችግር ሃይማኖታዊ መፍትሄ የሚሠጥ





የድጋፍ ፈተዋ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሳውዲ አረቢያም ሙስሊም ያልሆኑ ወታደሮች በግዟቷ ለማስገባት የድጋፍ ፈተዋ አግኝታለች፡፡

በተለምዶ "የሰይፍ አናቅፅት" እየተባሉ የሚጠቀሱት የቅዱስ ቁርአን አንቀፆች በኢአማኒያን ላይ ጦርነት ለማወጅ እየተመረጡ ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር፡፡ በቀደምት የኸሊፋ ዘመን የነበሩ በመንግሥት ልዩ ቦታ የተሰጣቸው ዓሊሞች እነዚህ አናቅፅት የመከላከል ጂሃድ አናቅፅትን ሽረዋል የሚል መከራከሪያ ያቀርቡ ነበር፡፡ ለምሳሌ "የተከበሩ ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ያዙዋቸውም ክበቡዋቸውም" (9፡5) ከነዚህ "የሰይፍ አናቅፅት" መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህን አንቀፅ ለብቻው ቆንፅለን ስናየው ምሉዕ ሃሳቡን እንስተዋለን፡፡ ከዚህ አንቀፅ ቀጥሎ የሚከተለው ተጠቅሷል *"ከአጋሪዎች አንዱ ጥገኝነት ቢጠይቅህ፣ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው፤ ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው፤ ይህ እነርሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመሆናቸው ነው፡፡"* (9፡6)

የሰይፍ አንቀፆቹ በፖለቲካዊ መሪዎቹና ዓሊሞቻቸው ተስፋፊ ጂሃዳቸውን ህጋዊ ለማድረግ ድጋፍ አድርገው ቢያቀርቡም ከጥንስሱ ጀምሮ ከነበረው የሙስሊም ማህበረሰብ ጀምሮ ለዘመናት በኖሩት ሙስሊሞች ዘንድ የነበረው አረዳድ በሙስሊሞች ነጻነት እና መብት ላይ ጥቃት እስካልደረሰ ድረስ ሰላማዊ ግንኙነት ኢስላማዊ ገዥ መርህ ነው የሚል ነበር፡፡

## አንጃዊነት እና ጂሃድ በቀደምት ኢስላም

የኢስላም ህብረተሰብ እምነት፣ አንድነት እና ህልውናው በእርስ በ'ርስ ጦርነት፣ በመሪዎቹ ግድያዎች፣ አንጃዊነት፣ ብጥብጥና ሽብር አደጋ ውስጥ የወደቀው ገና በጠዋቱ ነበር፡፡ ሥርዓት የለሽነት (ፊትና) በፖለቲካ እና በማህበረሰብ ደህንነት ላይ የተጋረጠ እኩይ ነበር፣ አሁንም ነው፡፡ ቅዱስ ቁርአንና የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማህበረሰብ ምሳሌ ኢስላምን ፖለቲካንና ማህበረሰብን የአምላክን ፈቃድና ፍትሃዊ ሥርዓት ከመመሥረት ጋ

አቆራኝተውታል። የሙስሊሙ ማህበረሰብ አመራርን እና ሥልጣንን በተመለከተ በሁለት ዋና እና ተፎካካሪ ቅርንጫፎች- ሱኒና ሺዓ ተከፈለ።

የሺዓ ኢስላም መነሻ ከነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት ጋ የተያያዘ ነው። በ632 የሙስሊሙ ማህበረሰብ የነቢዩን ፖለቲካዊ አመራር ማን ይተካ በሚል ቀውስ ይታመስ ጀመር- የሚተካቸው እጅግ ጻድቅ ሙስሊም ይሁን ወይስ የነብዩ ቤተሰብ? የነብዩ ተከታዮች በጥድፊያ አቡበክርን ሲመርጡ የፖለቲካ ተቃውሞ ዘር አብሮ ተተከለ። አቡበክር የነብዩ አማች፣ ቀደምት ሰለምቴ እና በማህበረሰቡ የተከበረ ሰው ነበሩ። ኸሊፋው የማህበረሰቡ ፖለቲካ መሪ ነው። ኸሊፋው የነብይነት ደረጃ ባይኖረውም እንደ ማህበረሰቡ መሪነት የሚያገኘው የስልጣን እና ኃይማኖታዊ ጥቅሞች አሉት።

የጁምዓ (ዓርብ) ሶላትን ይመራል፤ ከዚህ ሶላት ቀድሞ በሚደረገው ዲስኩር ስሙ ይነሳል። እንደ ኢስላም ጠበቃነቱ ኸሊፋው ጂሃድን ይመራል፤ ማህበረሰቡን በሸሪዓዊ ሕግ ያስተዳድራል። የአቡበክርን ምርጫ የተቀበሉት ሱኒ በመባል ተጠሩ- የሱና (የነብዩ ምሳሌ) ተከታይ ማለት ነው።

ይህ ሽግግር ወደ ክፍፍል፣ አመፅና ታሪካዊ ሽኩቻ ያመሩ ተከታታይ ክስተቶች እንዲፈጠሩ አደረገ። አናሳዎቹ የሙስሊም ማህበረሰብ- ሺዓዎቹ፣ በአቡበክር ምርጫ ላይ ጠንካራ ተቃውሞ አነሱ። ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከመሞታቸው በፊት ከቤተሰባቸው ታላቁን ወንድ ዓሊይን የማህበረሰቡ መሪ ወይም ኢማም እንዲሆን መርጠውታል ብለው ያምናሉ። ዓሊይ የነብዩ የአጎት ልጅ ሲሆን የነብዩን ተወዳጅ ሴት ልጅ ፋጡማን አግብቷል። ሺዓ ማለት የዓሊይ ተከታይ ወይም ደጋፊ ማለት ነው። ዓሊይ በኋላ ላይ በአራተኛ ኸሊፋነት ቢመረጥም ከአምስት አመታት (656-661) የአመራር ጊዜያት በኋላ ተገድሏል። የእርሱም ልጅ የሆነው ተወዳጁና ጀግናው ሑሴን የኢስላምን እሴት ለማፅናት እና ለማነቃቃት ሲል ባደረገው ትግል ተሰውቷል። ሁሴንና ጦሩ በኻሊፍ ያዚድ በ680 ይሸነፋል። በከርበላ ጦርነት የሑሴን ሰማዕት መሆን በሺዓ ሙስሊሞች ዘንድ የዓለም





ኢፍትሃዊነት መገለጫ ሆነ። ሺዓዎች ኢ-ኢስላማዊ ባሉዋቸው የዐመፀድና የአባሳድያውያን ስርወ መንግሥታት መሪዎች ላይ ባነሱዋቸው ጂሃዶች የሑሴን ሰማዕትነት መንፈሳዊ መነቃቂያ ሆኗቸዋል።

የሺዓ ታሪክ እና ኃይማኖታዊ ተምሳሌቶች በሁሉም ዘመን ተሃድሶ ለማምጣት ጥቅም ላይ ውለዋል። በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዘመናዊዎቹ የሺዓ ኃይማኖት መሪዎች የአብዮት እንቅስቃሴዎችን ለማፋፋም የሁሴንን ሰማዕትነት ትውስታ በአዲስ ተርጉመውታል። የከርበላ ጭፍጨፋ ዋና አቀናባሪ የሆነውን ያዚድን በማስታወስ አያቶላ ኮሜኒ የኢራኑን ሻህ የዚህ ዘመን ያዚድ ነው በማለት አስወግደውታል። ሱኒዎች በብዛት በሚኖሩበት ኢራቅ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ባህሪን እና ኩዌት ውስጥ ለሚኖሩ ሺዓዎች፣ ኮሚኒ በጨቋኝ መንግሥቶቻቸው ላይ እንዲነሱና የሚገባቸውን ውርስ እንዲቀበሉ ጠይቀዋል።

## የሱኒና ሺዓ የጂሃድ ፅንሰ ሃሳብ

በመካከላቸው ታሪካዊ ልዩነት ቢኖርም አሁንም ባልተፈታ ቅራኔ ውስጥ ቢሆኑም፣ ሱኒና ሺዓ ስለጂሃድ ተመሳሳይ አረዳድ አላቸው። ሁለቱም ጂሃድን በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግል እንደሆነ ይረዳሉ፤ ትልቁ ጂሃድ (ጻድቅ ለመሆን ከነፍስ ጋ የሚደረግ ትግል) እና ትንሹ ጂሃድ (በጦር መሳሪያ የሚደረገው ትግል) ብለው ይከፍሉታል። ጂሃድ በእያንዳንዱ ሙስሊምና በኢስላማዊ ማህበረሰብ ላይ ሕይወትን፣ መሬትን (አገርን) ወይም እምነትን የመጠበቅ እና ለማስፋፋት የተጣለ ኃይማኖታዊ ግዴታ ነው። ነገር ግን ጂሃድ የማወጅ ስልጣን ያለው ማን ነው በሚለው ላይ ይለያያሉ። ለሱኒዎቹ ኸሊፋው ከኃይማኖቱ ሊሂቃን (ዓሊሞች) ድጋፍ ጋ ጂሃድ የማወጅ ኃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ሥልጣን ተሰጥቶታል። ሺዓዎች ይህ ሥልጣን ከሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሕጋዊ ተከታዮች (ኢማሞች) ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተወስዷል የሚል አቋም አላቸው። ሆኖም ግን ኢማም

በሌለበት ወቅት የመከላከል ጂሃድ ብቻ ማወጅ ይፈቀዳል። ሁሉም ሕጋዊ ጂሃድ የመከላከል ጂሃድ አይነት ስለሆነ ኢማሙ በሌለበት ማወጅ ይቻላል ሲሉ የሃይማኖት ምሁራን (ዓሊሞች) ፍቃድ ሰጥተዋል። ይህ ምክንያ የኢራኑን ኢማም ኮሚኒ ሆነ የሊባኖሱ ሂዝቦላ ጂሃድ እንዲያውጁ አስችሏቸዋል።

## ጂሃድ፡ ዓለም አቀፍ የሙስሊም ዑማ በመፍጠር ሂደት ውስጥ

ሱኒዎችና ሺዓዎች ከቅዱስ ቁርአን እና ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተመዘዘ የጋራ እምነት ሲኖራቸው፣ የዓለም አቀፉ የኢስላማዊ ማህበረሰብ አባል ናቸው። የአንድ ቤተሰብ አባላት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንደሚለያዩት ሁሉ የዑማው ወይም ዓለም አቀፉ የአማኞች ቤተሰብ አባላት እንዲሁ ተለያይተዋል። በቤተሰቡ አባላት መካከል የመረረ ግጭት ቢኖርም በኢስላምና ሃይማኖታዊ ዕሴቶቹ ተሳስረዋል። የተለያዩ ነገዶች ወይም ብሔሮች አሊያም የአገር ዜጎች የጋራ ጠላት ሲመጣባቸው አንድ እንደሚሆኑት አንድ ይሆናሉ። ጠላቱ ሲወገድ (ሲከስም) ወደ ግጭታቸው ዳግም ይመለሳሉ።

በኢራን ኢስላማዊ አብዮት ሰኬት ብዙ ሙስሊሞች ተደስተዋል፣ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፣ ተነቃቅተዋል። ነገር ግን በኢራን ኢራቅ ጦርነት ወቅት ኢማም ኮሚኒ በደቡብ ኢራቅ የሚገኙ ሺዓዎችን ከጎናቸው ለማሰለፍ ሲሞክሩ ይህ ትስስር ሟሙቷል። በጦርነቱ በብሔርተኝነት እና ለዘመናት በቆየው የፋርስ-አረቢያ ፉክክር የኢራቅ ሺዓዎች ከእናት አገራቸው ጎን ተሰልፈዋል።

የመጀመሪያው የመዲና ሙስሊም ማህበረሰብ በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ምሪት በፍጥነት ሲስፋፋ እና በመካከለኛው አረቢያ ገናና ሲሆን የዑማ ፅንሰ ሀሳብ አብሮ ዳብሯል። በወታደራዊ እንቅስቃሴና በበሳል ዲፕሎማሲ የዓረቢያ ነገዶች በጋራ እምነት፣ ርዕዮት ዓለም፣ ማዕከላዊ አስተዳደርና ሕግ ሥር ተሰባስበው የአረብ የጋራ ኮመን ዌልዝ (common wealth) ተመሠረተ።





ለመጀመሪያ ጊዜ በነገዶች መካከል የነበረውን ዕልቂት የሚያስወግድ እና የነገዶችን ሕብረት በጋራ ኃይማኖታዊ ትሥሥር የሚለውጥ መንገድ ተገኘ። ቅዱስ ቁርአን እንደሚያዘው ሙስሊሞች ከየትኛውም አይነት የትስስር ምክንያት በላጭ በሆነው የአላህ ገመድ የተሣሠሩ አማኝ ማህበረሰብ ናቸው። ራሳቸውን ለአላህ የማስገዛት እና ኃይማኖታቸውን የማስፋፋት ግለሰባዊ እና ማህበራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ይጠበቃል።

የኢስላም ድንበር ተሻጋሪ ገፅታውን ከሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ዓለም አቀፍ ኃይል ሲሆንና ስልጣኔ ሲገነባ በተነሱት ኢምፓየሮች እና ሱልጣኔቶች ማየት ይቻላል። በአውሮፓ ኮሎኒያሊስቶች አማካኝነት የሙስሊሞች ኢምፓየር መፈረካከስና በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተፈጠሩ አገራት ምክንያት የዑምማ ፅንሰ ሃሳብ ሩቅ እንዲሆን አድርጎታል። ነገር ግን በዚሁ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተፈጠረው ኢስላማዊ መነቃቃትና ፈጣን የመገናኛ ብዙሃን አውታሮች የሙስሊሞችን ንቃተ ህሊና ከዓለም አቀፍ ኢስላማዊ ማህበረሰብ አንጻር አንቅቷል። ተፅዕኖ አሳዳሪው አክቲቪስቱ እና ርዕዮተ ዓለም ቀማሪው ሰይድ ቁጥብ በአሁኑ ዘመን ያለውን ዓለም አቀፍ የዑምማ ግንዛቤ አብራርቶታል።

> *"በዚህ ታላቅ ኢስላማዊ ማህበረሰብ ሥር አረቦች፣ ፋርሶች፣ ሶሪያዎች፣ ግብጾች፣ ሞሮኮዎች፣ ቱርኮች፣ ቻይናዎች፣ ህንዶች፣ ሮማዎች፣ ግሪኮች፣ ኢንዶኔዥያዎች፣ አፍሪካዎች- በአጭሩ ሁሉም አገሮች እና ሕዝቦች ተሰባስበዋል። የተለያዩ መለያዎቻቸው ኢስላማዊ ማህበረሰብና ባህል ለመፍጠር የራሱን ሚና ተጫውቷል። ይህ ድንቅ ስልጣኔ ለአንድ ቀን እንኳን የ"አረቦች ስልጣኔ" ሆኖ አያውቅም። ፍፁም "ኢስላማዊ*

*ስልጣኔ" ነበር። "ብሔረተኛ"ም አልነበረም፤ ሁልጊዜም "የእምነት ማህበረሰብ" ነበር።*[22]

የዑምማ ንቃተ ኅሊና ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በዋነኝነት በመገናኛ ብዙሃን የዘገባ ሽፋን አማካኝነት ተጠናክሯል። የሙስሊሞች ስሜት፣ ድጋፍና ትብብር እፍጋኖች በሶቪየት ህብረት ላይ ካወጁት ጂሃድ ጋ ተተኩሷል። በሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ከዓረብ እና ሌሎች አገራት የሶቪየት ህብረትን ወረራ ለመመከት በአፍጋኒስታን ተሰባስበዋል። የኢራን አብዮትም ተመሳሳይ ውጤት ነበረው።

ዓለም አቀፍ የዓረቦችና ሙስሊሞች ጋዜጦችና እንደ አል ጀዚራ፣ ሲ.ኤን.ኤን፣ ቢ.ቢ.ሲ. እና ኢንተርኔት የመሳሰሉ ሚዲያዎች በፍልስጤም እና አፍጋኒስታን፣ ቦስኒያ፣ ኢራቅ፣ ቼቺኒያ እና ካሽሚር የሚገኙ ሙስሊሞች የሚያደርጉትን ፉርጆ ብዙ ትግል በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ሙስሊሞች እስከ መኝታ ቤታቸው ድረስ አምጥተውላቸዋል፤ የዕለት ተዕለት ሃሳባቸው እና አጀንዳቸው አድርገውላቸዋል። ሙስሊሞች እየኖሩበት ያለውን አሳዛኝ ሁኔታ ለመለወጥ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ኢስላማዊ ድርጅቶች በዓለም ዙሪያ መፈጠራቸውና መስፋፋታቸው ለለውጥ የሚደረገውን የጂሃድ ቋንቋ አፋፍሟል።

## ሽብርና ጂሃድ በአምላክ ስም

ልክ እንደ አሁኑ ሙስሊም ህብረተሰብ፣ ቀደምት የእስላም ዓለም የፅንፈኞችን ሽብር አይቷል። የኸዋሪጆች እና የአሳሲኖች ተቃዋሚ የፖለቲካ አንጃዎች በአምላክ ስም ያደረጉት ኢቅዱሳዊ ጦርነቶች ለዚህ ጥሩ አመላካች ምሳሌዎች ይሆናሉ።

[22] ሰይድ ቁጥብ. ማይል ስቶንን (Stuttgart: Ernst Klett Printers, 1978) ገጽ 88-89





ኸዋሪጆ (ኸረጀ- ወጣ፣ ተገነጠለ ማለት ነው) መጀመሪያ ላይ የዓሊ ደጋፊዎች ቢሆኑም ዓሊ የአምላክን ፈቃድ ለድርድር አቅርቧል በሚል የ'ርሱ ጠላት ሆነዋል። ከዓሊ ከተገነጠሉ በኋላ (በነገራችን ላይ ዓሊን የገደሉት እነዚሁ ሰዎች ናቸው) ቅዱስ ቁርአንን እና ሱናን በጥብቅ የሚከተል ማህበረሰብ መፍጠር በሚል ተዕልኮ የራሳቸውን ማህበረሰብ ፈጠሩ። በዚህ እርምጃቸው የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሂጅራ መከተላቸው ቢሆንም እጅግ ፅንፈኛ እና ጦረኛ የጂሃድ አይነት ተከትለዋል። መጀመሪያ ራሳቸው ማህበረሰባቸውን በፈጠሩበት አምሳል ለመኖር ይጥራሉ፣ ከዚያ ማህበረሰባቸውን ከፈጠሩበት ክልል በአምላክ ስም በጠላቶቻቸው ላይ ጦርነት ይከፍታሉ።

ኸዋሪጆች "በመልካም እዘዙ፣ መጥፎን ተከላከሉ" የሚለውን የቅዱስ ቁርአን ትዕዛዝ በቀጥታ፣ ሙሉ ለሙሉ እና ያለብቃት እና ተቀባይ ተአቅቦ መተግበር አለበት ብለው አምነዋል። ዓለማቸው እምነትና ክህደት፣ ሙስሊሞች (የአምላክ ተከታዮች) እና ካፊሮች (የአላህ ጠላቶች)፣ ሰላምና ጦር በሚል ለሁለት የተከፈለች ናት። ማንኛውም ከህጉ ጋ ቃል በቃል ያልተሳሞረ ድርጊት (እንቅስቃሴ) እጅግ ከባድ ኃጢያት ነው። ኃጢያተኛው ክህደት ስለፈፀመ እንዲገለል ይደረጋል። እነዚህ ኃጢያተኞች እንደ ወንጀለኛ ሳይሆን እንደ ከሃዲ ስለሚታዩ ተፀዕተው እስካልተመለሱ ድረስ እንደ አገር ክህደት ወንጀል የሞት ቅጣት ይተላለፍባቸዋል።

ኸዋሪጆች የእነርሱን ፅንፈኛ አመለካከት ያልተቀበሉትን ሙስሊሞች እንደ ካፊር ወይም ጣዖት አምላኪ ስለሚመለከቱዋቸው የአምላክ ጠላቶች ናቸው። ኸሊፋው በድምፅ ብልጫ መመረጥ አለበት የሚል አቋም ቢኖራቸውም፣ ስልጣን ላይ መቆየት የሚችለው ግን ቀጥተኛ እና ኃጢያት የለሽ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ከባድ ኃጢያት ስለሚሆን ከሃዲ ይሆናል። የሕግ ከለላ ስለማይኖረው ከሥልጣን መውረድና መገደል አለበት።

ራሳቸውን በእኩይ ኃይል ላይ ጂሃድ ያወጁ የአምላክ ጦር አድርገው ስለሚመለከቱ፣ ግቡ መንገዱን ይወስነዋል (የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው) አስተሳሰብ በ'ነርሱ ዘንድ ትክክል ነው። የአምላክን ፈቃድ እና ልዕልና የዘነጉ ኃጢያተኞችን ማሸበር፣ የጎሬላ ጥቃት ማድረስ እና አብዮት ማስነሳት ሕጋዊ ብቻም አይደለም ግዴታም ጭምር ነው። ይህ አስተሳሰብ የግብፁን ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳትን በገደሉት የ"ኢስላሚክ ጂሃድ" እና "ኢኢስላማዊ" ሙስሊም መሪዎችና በምዕራቡ ዓለም ላይ ጂሃድ ባወጁ የፅንፈኞች ቡድኖች ተቀባይነት አግኝቷል።

ከታሪክ አንጻር ኸዋሪጆች ከቀጥተኛው ኢስላማዊ የፖለቲካና ኃይማኖታዊ ዕይታ የተገነጠሉ (ውጪ የሆኑ) ናቸው። ተመሳሳይ ዕጣም አሳሲኖችን ገጥሟቸዋል።

ነውጠኛው የሺዓ አማፂ የሆነው አሳሲ'ንስ በመሲሃዊ ራዕይ መግፍኤ የተቋቋመ ነበር። ተገንጥለው ከሚኖሩበት ድብቅ ቦታዎች በመነሳት ኢአማኒያንን ያጠቁ ነበር። በሰሜናዊ ፋርስ በሚገኘው ታላቁ የአልሙት ተራራ ላይ በመሽጉ "ታላቅ አለቆች" የሚመሩ ነበሩ። እያንዳንዱ ታላቅ አለቃ "የተራራው ሽማግሌ" በመባል ይጠራል። አሳሲ'ንሶች በአባሳድያውያን ሥርዎ መንግሥት ላይ ባወጁት ጂሃድ፣ በድብቁ ኢማም ስም የሚገድሉዋቸው የአባሳዲያውያንን ልዑሎች፣ ጄኔራሎችና የሃይማኖት ሊሂቃን ላይ ሽብር ፈጥረዋል። በሙስሊም እና መስቀለኞች ጠላቶቻቸው ልብ ውስጥ የፈጠሩት የሽብር ጫና እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ፣ የመጨረሻው "የተራራው ሽማግሌ" በ1256 በሞንጎሎች ከተገደለ በኋላ እ'ንኳ በሶሪያ እና ፋርስ ስማቸውና ዝናቸው ጥቅም ላይ ይውል ነበር።

## የጂሐድን ትርጉም ፍለጋ

ሙስሊሞች ቅዱስ ቁርአንና ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስለጂሐድ ያላቸው አስተምሮት አረዳድ ከሚኖሩበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ይለዋወጣል። የጂሐድ አስተምሮት የአንድ ሰው ወይም ተቋም ሞኖፖል አይደለም።





የተለያዩ ግለሰቦች እና ባለስልጣናት ከሚኖሩበት ፖለቲካዊና ታሪካዊ ማዕቀፍ አንጻር የሚሠጡት ምላሽ ድምር ነው።

በምዕራቢያውያን ሊሂቃን ዘንድ ጂሐድ ከተናኚሽ ቅዱስ ጦርነት ጋ ስለተጣመረ በምዕራቡ ዓለም ነዋሪዎች ዘንድ ኢስላምን የረብሻና ፅንፈኞች መፈልፈያ ሃይማኖት አድርጎ የመመልከት ነገር በሰፊው አለ። ፅንፈኛ ሃይማኖተኞች እና አሸባሪዎች ከነርሱ ጋ በሃሳብ ያልተስማማውን ለማጥቃት ሲፈልጉ እንዳሻቸው የሚያነሱት ቃል ጂሃዲ ነው። አሸባሪዎች ኢስላምንና ጂሐድን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሊያግቱት ይችላሉ። ይህ ደግሞ ልክ ክርስቲያንና አይሁድ አሸባሪዎች ቅዱስ ጦርነታቸውን በክርስትና እና ጁዳይዝም ሽፋን ከሚያደርጉት በምንም አይለይም።

ኢስላም የሰይፍ ሃይማኖት ነው፣ ሙስሊሞች ዕምነታቸው በሰዎች ጉሮሮ ውስጥ ለማዋጥ የትኛውንም መንገድ፣ ሃይልና ጦርነትን ጭምር የሚጠቀሙ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ ሙስሊም ባልሆኑ ግለሰቦች ዘንድ ሃይማኖቱን በተመለከተ የሰፈነ ዕይታ ነው። ሁሉም የሙስሊም ሊሂቃን ሙስሊም ባልሆኑት ላይ በሃይማኖታቸው ብቻ ወይም ሃይማኖታቸውን ለማስለወጥ ወታደራዊ የጂሐድ እንቅስቃሴ ማድረግን ከልክለዋል። ኢብን ኸልዱን ጥቂት ግለሰቦች "በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ ቅዱስ ጦርነት ማድረግ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው። የሙስሊም ተልዕኮ ዓለም አቀፋዊ በመሆኑ ሁሉም ሰው በማግባባት ወይም በሃይል እስልምናን እንዲቀበሉ" ሲሉ በደፈናው ተናግረዋል። ሌሎች እጅግ ጥቂት የመካከለኛው ዘመን ፀሐፍቶች፣ እንደ ክርስቲያን አቻዎቻቸው የጂሐድ ዓለማ ኢአማኒያንን ከምድረ ገጽ ማጥፋት ነው ብለው እስከመጻፍ ደርሰዋል።

ቀደምት የቅዱስ ቁርአን ተንታኞችና የሕግ ሰዎች አለማመንን ከፖለቲካዊ ኢፍትሃዊነት ባይለዩም፣ ለእምነት ልዩነት ሲባል ያወጁት አንድም ጂሐድ የለም። በርካታ ዘመናዊ ሙስሊም አብስልሳዮች አለማመንን ከጭቆናና ኢፍታሃዊነት ስለለዩ አለማመን ጦርነት ለማወጅ በቂ ምክንያት የለውም ሲሉ የጋራ አቋም ወስደዋል። ለምሳሌ የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ታዋቂው የግብጹ አዝሃር ዩኒቨርስቲ ሊቅ ማህሙድ ሻልቱት ሙስሊሞች ከኢአማንያን ጋ እንዲዋጉ የሚያዙ የቅዱስ ቁርአን አናቅፅት ሁሉንም ኢአማኒያን የሚመለከት ሳይሆን የሰዎችን የማመን ነፃነት የሚገቱ ኢአማኒያንን የሚመለከት ነው ሲል ይከራከራል።

ሰይድ ቁጥብ እንኳ የሃይል እምነት ለውጥን አጥብቆ ይቃወማል። ለርሱ ስኬታማ ጂሐድ ማለት የሰዎችን የመምረጥ ነጻነት ማሳካት ነው።

> *"ኢስላም እምነቱን ሰዎች ላይ በሃይል የመጫን ፍላጎት የለውም። ኢስላም ግን "እምነት" ብቻ አይደለም። ... ኢስላም ሰዎች ከሌላ ሰው ባርነት ነፃ የሚወጡበት አዋጅ ነው። እናም ሰውን በሰው ላይ የሚያስገዙ፣ ሰዎችን ለሌሎች ሰዎች ባርነት የሚዳርጉ ሥርዓቶችንና መንግስታትን ለማጥፋት ይጥራል። ኢስላም ሰዎችን ከዚህ የፖለቲካ ተፅእኖ ነጻ ሲያወጣ፣ መንፈሳዊ መልዕክቱ ለአዕምሮዋቸው በሚመጥን መልኩ ከቀረበላቸው በኋላ የማመንና ያለማመን ነጻነት ይሰጣቸዋል። ሆኖም ግን ይህ ነጻነት ጣያታቸውን ወይም የተወሰኑ ሰዎችን በህዝቦች ላይ እንዲጭኑ ይፈቅድላቸዋል ማለት አይደለም።"[23]*

የዚህ ዘመን ምሁራን ኢስላም የተለያዩ ሃይማኖታትን ህግጋትን የሚቀበል እንደሆነ የቅዱስ ቁርአንን አናቅፅት በመጥቀስ ያሳያሉ። ለምሳሌ ***"እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ፤ ሳቢያኖችም፤ ክርስትያኖችም፣ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፣ በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም።"*** (5:69 እና 2:62)

[23] ዝኒ ከማሁ፣ 109-10





# ***አክራሪነትን የሚፈጥረው ምንድነው?***

## ***በፕ/ሮ ጆን ኤል ኤስፖሲቶ እና ዳሊያ ሞጋሂድ[24]***

በዓለም አቀፍ ሽብር ላይ ጦርነት ከተጀመረ ስድስት ዓመታት[25] ቢያልፉትም የሙስሊሞች ፅንፈኝነትና ሽብር እያደገ መጥቷል። ከሰሜን አፍሪቃ እስከ ደቡብ ምስራቅ እስያ የዘለቁ ጥቃቶች ተስፋፍተዋል። ካሳብላንካ፣ ማድሪድ፣ ከሎንደን እስከ ኢስታንቡል፣ ጃካርታ እና ባሊ የጥቃቶቻቸው ዒላማዎች ነበሩ። ዑሳማ ቢን ላዲን በአንድ ወቅት ታዋቂና ዝነኛ የነበረውን ጂሐድ-አፍጋኖች ከዓለም ዙሪያ በተሰባሰቡ ሙስሊሞችና ምዕራብያውያን ድጋፍ የሶቭየት ሕብረትን ወረራ ለመቀልበስ ያደርጉትን ትግል- ወደ አጥፍቶ ጠፊ በምቦኞች፣ ዕገታና መሠረተ ሰፊ የሽብር እኩይ ጦርነት ለውጦታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአውሮፓና አሜሪካ ፀረ-ኢስላም አመለካከት ሲያሻቅብ በዐረቡና ሙስሊሙ ዓለም ፀረ-አሜሪካ አመለካከት በእጅጉ ተስፋፍቷል። በኢራቅ፣ እስራኤል፣ ፍልስጤም፣ አፍጋኒስታን፣ ፓኪስታን እና ኢንዶኔዥያ በሚደርሱ የሽብርተኞች ጥቃቶች የምዕራቡን ዓለም ነዋሪ ስሜት ሲያጎሹ፤ የኢራቅ ወረራ፣ የአቡ ግሬብ እና ጓንታናሞ ኢ-ሰብአዊ ጥቃቶች እና እስራኤል በጋዛ እና ደቡብ ሊባኖስ የምትፈጽመው ተደጋጋሚ

[24] ዳሊያ ሞጋሂድ ካይሮ ግብጽ ብትወለድም በ 4 አመቷ ወደ አሜሪካ ሄዳ በዚያው አድጋለች። የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከሚስኮንሲስ ዩኒቨርስቲ በኬሚካል ኢንጂነሪንግ ሜጀርና በአረብኛ ማይነር አግኝታለች። ከዚያም በዩኒቨርስቲ ኦፍ ፒተርስቡርግ ከጆሴፍ ኤም ካትዝ ግራጁዌት ስኩል ኦፍ ቢስነስ ኤም ኤዋን ወስዳለች። ከጆን ኤስፖሲቶ ጋ *Who Speaks For Islam? : What a Billion Muslims Really Think* የሚል መጽሐፍ በጋራ አሳትማለች። መጽሐፉ ጋሉፕ ከ35 ሙስሊሞች በብዛት ከሚኖሩባቸው አገራት በሚኖሩ 50000 ሙስሊሞች ላይ ለስድስት ዓመታት ባደረገው ጥናት ላይ ተመስርቶ የተጻፈ ነው። በጥናቱ ውስጥ ኢትዮጲያም ተጠቃላለች። ይህ ጥናት በአይነቱ የመጀመሪያው ተብሎለታል። ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ *What Makes Radical?* የሚለው ምዕራፍ ተተርጉሟል።

[25] መጽሐፉ የተፃፈው በ2007 ነው።

ወረራ እና የንፁሃን ዜጎች ግድያና ውድመት የሙስሊሙን ዓለም አስቆጥተዋል፡፡

• በዚህ ዳራ ነው እንግዲህ ዩናይትድ ስቴትስ ሽብርን ይደግፋሉ በምትላቸው አገሮች ላይ ሴኩላር ዲሞክራሲ ለመመስረት የምትፈልገው፡፡ በነዚህ አገሮች ስኬታማ ዲሞክራሲ መመሥረት የ"ሽብር ላይ ጦርነቱ" ዋና ድል ነው የሚል ዕሳቤም አስልታለች፡፡ የአሜሪካና አውሮፓ መሪዎች ስለ ሃሳብ ጦርነትም ይናገራሉ- የሙስሊሞችን ልብና አዕምሮ መግዛት ወሳኝ ስለሆነ፡፡ ነገር ግን ይህ ከመሳካቱ በፊት የተለያዩ ተግዳሮቶችን ማለፍ ግድ ይላል፡፡ የስልጣኔዎች ግጭት ነጋሪት እየተጎሰመና አይቀሬነቱ እየተነገረ ባለበት ክባቢ ውስጥ ምን ሊደረግ ይችላል? የዲፕሎማሲ አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ ልንለውጣቸው ስለምንፈልጋቸው ሰዎች ትክክለኛ መረጃ መኖር ይበልጥ አስፈላጊ ነው፡፡

የቀድሞው የዩ.ኤስ መከላከያ ሴክሬታሪ ሮበርት ማክናማራ (Robert McNamara) እንደሚለው በቬትናም ጦርነት አሜሪካን ለሽንፈት ያበቃት ስለጠላቶቿ- ስሜን ቬትናሚያውያን- ምንም አለማወቋ ነው፡፡ አሜሪካ ጠላቶቿ ምን እንደሚያስቡና እንደሚፈልጉ አታውቅም ነበር፡፡፡ ጦርነቱን ስትመለከተው የነበረው ከጥቅል ጸረ-ፖለቲካዊ ጽንሰ ሃሳብ አንጻር- ከ"ዶሚኖ ታምሪ" አንዱ ክፍል ነበር፡፡ የኮሚኒዝምን መስፋፋት ለመገደብ እየተደረገ የነበረው እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ ትግል ቅኝት ነበረው፣ ልክ አሁን በዓለም አቀፍ ሽብር ላይ እንደተከፈተው ጦርነት፡፡[26]

የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከዓለም አቀፉ ሽብር ጋር ትግሉን እያደረገ ባለበት ወቅት "ሌሎችን"- የሙስሊሙን ብዙሃን ማህበረሰብ እና አናሳ ፅንፈኞቹን- ቀረብ ብሎ ማየትና መረዳት መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ አንዳንድ ሊጠየቁ የሚገቡ እና በጋሎፕ ጥናት መልስ የተሰጠባቸው ጥያቄዎች

[26] አንዳንድ ሙስሊሞች ይህን ጦርነት በኢስላም ላይ የተከፈተ ጦርነት አድርገው ነው የሚረዱት፡፡





- ፖለቲካዊ ፅንፈኞች የሚባሉት እነማን ናቸው?
- በኢስላምና ሽብር መካከል ያለው ዝምድና ምንድን ነው? በጂሃድና አጥፍቶ መጥፋት ሽብር መካከል ያለው ትስስርስ?
- ለምን እኛን (ምዕራቡን) እና አኗኗራችንን ይጠላሉ?
  - ፖለቲካዊ ፅንፈኞች ስለነፃነታችንና ቴክኖሎጂያችን ያላቸው ዕሳቤ ምንድን ነው?
  - ስለምዕራቡ ዓለም አገራትና መሪዎች ምንድነው የሚባሉት?
  - አሜሪካን እንዴት ነው የሚያይዋት?
- የፅንፈኝነት ዋና መግፍኤ ምንድነው?

## ፖለቲካዊ ፅንፈኞች የሚባሉት እነማን ናቸው?

ለአስርት ዓመታት ምሁራንና ተመራማሪዎች ሽብርተኞችና ፅንፈኞች እንዴት እንደሚፈጠሩ ሲከራከሩ ቆይተዋል፡፡ የሽብር መንስኤዎች ስነ ልቦናዊ (ሽብርተኞች ጤናማ እና ምክንያታዊ ያልሆኑ ናቸው)፣ ስነ ማህበራዊ (መሃይማን እና ከህብረተሰቡ የተገለሉ ናቸው)፣ ኢኮኖሚያዊ (ድሆች፣ ሥራ ፈቶች እና ተስፋ የቆረጡ ናቸው)፣ ፖለቲካዊ (ዲሞክራሲን፣ ነጻነትና መልካም የሰብአዊ መብት አያያዝን የሚቃወሙ ናቸው) እና ሃይማኖታዊ (አክራሪዎች ዘመናዊነትና ቴክሎጂን በሚጠላ ሽብርተኛ ሃይማኖት (እስልምናን) የሚያምኑ) ናቸው ሲባል ተከርሟል፡፡

በፅንፈኞች ላይ ገናና ሆኖ በቆየና ሥሩን አጥልቆ በሰደደው ቅይድ አስተሳሰብና ቅድመ ግምት መሰረቱን የጣለው አረዳድ- ሃይማኖታዊ አክራሪነት፣ ድህነትና ስራ አጥነት ድምር የጽንፈኝነትና የሽብርተኝነት መግፍኤ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ እንዳይመረመር አድርጎታል።

ፅንፈኞችን የቆየ ጎሚ ያላቸው ምክንያታዊ ያልሆኑ ሰዎች አድርጎ የማየት ዳተኝነት የመስከረም አስራ አንዱ ጥቃት በደረሰ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ዕርቃኑን ቀርቷል። ሚዲያዎች "ድንቅ ግኝት" ብለው የጠሩትን- አብዛኛዎቹ ጥቃት አድራሾች ድሆች፣ የስነ ልቦና ችግር ያለባቸው፣ መሃይሞች እና ከማህበረሰባቸው የተገለሉ እንዳልሆኑ፤ እንደ ዑሳማ ቢን ላዲን እና ዶ/ር አይመን አል-ዘዋሂሪ እና ሌሎች የአል-ቃኢዳ መሪዎች አብዛኞቹ በጣም የተማሩ፣ ከመካከለኛ ወይም ከላይኛው የማህረሰቡ መደብ የተገኙ እና የተረጋጋ ቤተሰብ ያላቸው እንደሆኑ- ዘገቡ። ይህ የግለሰቦቹ ማንነት ዝርዝር እጅግ አስፈላጊ ጥያቄ እንዲነሳ አድርጓል- ለምን ከጤናማ እና ጥሩ ማህበራዊ ዳራ የተገኙ ሰዎች ሽብርተኞች ሆኑ?

ነገር ግን የመስከረም አስራ አንዱን ጥቃት ያደረሱት ግለሰቦች ሆነ የአል-ቃኢዳ እና ሌሎች የሽብር ቡድኖች መሪዎች ማንነት ሊያስደንግጠን ይገባ ነበርን? የቅርብ ጊዜያት ታሪክን ባስታወስን ባልተገባን ነበር። ሙስሊም ፅንፈኝነት አዲስ ክስተት አይደለም።

ከግብፅ እና አልጀሪያ ጀምሮ እስከ ሊባኖስ፣ ፓኪስታን፣ ኢንዶኔዥያን እና ደቡብ ፊሊፒንስ ፅንፈኛ ቡድኖች ለአስርት ዓመታት ነበሩ። በፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳት ገዳዮች ላይ ጥናት ያደረጉ ግብፃዊው ሶሾሎጂስት ሰዓድ አድዲን ኢብራሂም እና ሌሎች እንደደመደሙት

> *"የጦረኛ ኢስላማዊ ሰብስቦች አባላት ማህበራዊ ማንነት እንደሚያሳየው ወጣቶች (በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ ያሉ)፣ ከገጠር ወይም ከአነስተኛ ከተማ የተገኙ፣ የመካከለኛ እና አነስ ያሉ መካከለኛ መደብ አባላት የሆኑ፣ ከፍተኛ የስኬታማነት መነቃቃት ያላቸው፣ ተመንዳጊዎች፣ ሳይንስ ወይም ኢንጂነሪንግ ያጠኑ እና ከጤናማና የተደላደለ ቤተሰብ የተገኙ... አብዛኛዎቹ ወጣቶች የግብጽውያን ባለአርአያዎች የሚባሉ ናቸው።"*





በተመሳሳይ መልኩ፣ ከተወሰኑት በስተቀር ከ9/11 ጥቃት ፈጻሚዎች ጀምሮ እስከ 7/7 የሎንዶን ቦምብ አፈንጂዎች ያሉ የአሁኖቹ ጦረኞችና አሸባሪዎች ከመካከለኛ እና ሀራተኛ መደብ የተገኙ፣ እጅግ የተማሩ ግለሰቦች ናቸው። አንዳንዶቹ ሃይማኖተኞች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ አልነበሩም። እንደ ሚዲዎች ዘገባ ከ9/11 ጥቃት ፈጻሚዎች ውስጥ አብዛኞዎቹ ሃይማኖተኛ ሙስሊም የማያሳየውን ባህሪይ ሲያሳዩ የማይተገብረውን ሲተገብሩ ነበር እጅግ ጠጪዎች፣ ዳንስ ቤቶችና የወሲብ ፊልም ሱቆች አዘውታሪዎች ነበሩ

ከመድረሳም (ከሐይማኖት ት/ቤት [illegible] ውም ሃይማኖት ተቋም ያልተመረቁት በርካታ ናቸው። [illegible] ወይም [illegible] ት/ቤቶች እና ዩንቨርስቲዎች ተምረዋል። ቢን ላዲን ማኔጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ እና ኢንጂነሪንግ ነበር ያጠናው። አል-ዘዋሂሪ የቀዶ ጥገና ባለሙያ፣ ለዓለም አቀፉ የንግድ ተቋማትና ፔንታጎን ጥቃት ኃላፊ የሆነው መሀመድ አታ እና ሌሎች የአል-ቃኢዳ አመራሮች ከመካከለኛው የህብረተሰብ መደብ የተገኙ ባለሙያዎች ናቸው። የዎል ስትሪት ጆርናል ዘጋቢ የሆነውን ዳንኤል ፐርልን በማገትና በመግደል ተከሶ የሞት ፍርድ የተፈረደበት እንግሊዛዊ ተወላጅ ዑመር ሽይክ የላይኛው የህብረተሰብ መደብ አባላት በሚማሩበት የግል ትምህርት ቤት እና የሎንዶን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ ተማሪ ነበር።

አክራሪነትን እና ምንነቱን ለመረዳት ከባለሙያዎች ግጭት ከሞላበት አስተያየትና የዐረብ መንገዶች ንግግር ቅርሚያ የዘለለና የተሻገረ ዓለም አቀፋዊ ምልከታ ይጠይቃል። በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሙስሊሞች የሚሰጡት አስተያየት ምንድን ነው? ምን ያህል ሙስሊሞች ፅንፈኛ አመለካከት አላቸው? ተስፋቸውና ስጋታቸው ምንድን ናቸው? ግንባር ቀደም ፍላጎታቸውስ? ምን ያደንቃሉ? ምንስ ይኮንናሉ?

እንደ ጋሉፕ ጥናት 7% የሚሆኑ መላሾች የ9/11ን ጥቃት "ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው" ብለው ሲደግፉ አሜሪካንም የሚመለከቷት በክፉ አይን ነው። የ9/11 ጥቃት "ትክክል አይደለም" ብለው የሚያኑትና "መካከለኛ" ብለን ከምንጠራችው 40% የአሜሪካ ደጋፊ ሲሆኑ የተቀሩት 60% ደግሞ ለአሜሪካ በጎ አመለካከት የላቸውም።

የ7%ቶቹን መላሾች መልስ ከብዙሃኑ መላሾች መልስ ጋ ስናነፃፅረው አስደናቂ ውጤቶች ተገኝተዋል። ፅንፈኛ ፓለቲካዊ አሰላለፍ ስላላቸው "ፖለቲካዊ አክራሪ" ሆነዋል የምንላቸው 7%ቶቹ ሁሉም የሽብር ተግባር ይፈጽማሉ ማለት አይደለም። ሆኖም ግን ጽንፈኛ አመለካከት ያላቸው በሽብር ተግባር ላይ ለተሰማሩ ስብስቦች የአባልነት ምልመላ ቋት ናቸው። እነዚህ ስብሰቦች ፓለቲካዊ ሁነቶችን ለመለወጥ በእጅጉ የቆረጡ በመሆናቸው በየትም ቦታ በሚገኙ ዜጎች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የሚደግፉ ይበዙባቸዋል። 13% ከፓለቲካዊ አክራሪዎች፣ 1% ከመካከለኞቹ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚደረጉ ጥቃቶችን ሙሉ በሙሉ ይደግፋሉ።





## የሃይማኖትና ሽብር ግንኙነት ምን ይመስላል?

አሸባሪዎች የሚጠቀሙት ሃይማኖታዊ ቋንቋና ምልክቶች በሽብር ውስጥ ሃይማኖት ማዕከላዊ ቦታ እንዲይዝ አድርጓል። በርካታ ሀያሲያን ዓለም አቀፋዊ ሽብርተኝነትን ጦረኛ ወይም ሽብርተኛ ሃይማኖት ካሉት እስልምና ጋ አቆራኝተውታል። ለምሳሌ ደራሲ ሳም ሃሪስ በዋሺንግተን ታይምስ ኮመንታሪ ላይ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፦

> *ከ"ሽብር" ጋ ጦርነት እንዳልገጠምን የምናምንበት ጊዜ አሁን ነው። ጦርነታችን ከኢስላም ጋ ነው። ይህ ከሁሉም ሙስሊሞች ጋ ጦርነት ውስጥ ነን ማለት ባይሆንም ሙስሊሞች በቁርአን ውስጥ እንዲኖሩት ከተሰጣቸው የሕይወት መመሪያ ጋ ግን በርግጥ ጦርነት ውስጥ ነን። ሙስሊም አክራሪዎች ለኛ ስጋት የሆኑብን የኢስላም መሰረቶች ለኛ ስጋት ስለሆኑ ነው። እያንዳንዱ አሜሪካዊ ቅዱስ ቁርአንን ማንበብና በገጾቹ ሙስሊም ያልሆኑት እንዴት እንደተራከሱ መረዳት አለበት። "ኢስላም በአክራሪዎች የታገተ ሰላማዊ ሃይማኖት ነው" የሚለው ሃሳብ አደገኛ ተምኔት ሲሆን፣ አሁን ደግሞ ሙስሊሞች ሊያቀነቅኑት የማይገባ ተምኔት ነው።*

ለውረንስ ኦስተርም በፕሮንት ፔጅ መፅሔት ተመሳሳይ ስሜት አስተጋብቷል። እርሱ ሲጽፍ "ችግሩ "አክራሪ ኢስላም" ሳይሆን ኢስላም ራሱ ነው። ከዚህ በመነሳት ኢስላምን ማዳከምና መቆጣጠር አለብን....." ብሏል።

ጥሬ መረጃዎቹ ግን ምን ይላሉ? ለሃይማኖት ቀናኢ መሆን ከአክራሪነት ዕይታ ጋ ትስስሮሽ አለው? መልሱ "የለውም" ነው። ከአክራሪዎቹ ሆኑ መካከለኞቹ እጅግ በርካታዎቹ (94% እና 90% በቅደም ተከተላቸው) ሃይማኖት የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው አስፈላጊ

ክፍል ነው ይላሉ። በአክራሪዎቹና መካከለኞቹ መካከል መስጊድ በመሳተፍ ረገድ ይህ ነው የሚባል ልዩነት የለም።

ጋሎፕ ለመላሾች ተጨማሪ ጥያቄ አቅርቦላቸው ነበር- የአሸባሪዎችን ተግባር እንቃወማለን የምትሉ ምክንያታችሁ ምንድን ነው? ምላሹ ሁሬ ተቀባይነት ባገኘው አረዳድ ላይ የሚያላግጥ ነው። የዓለማችን የሙስሊም ብዙሃን አገር የሆነችው ኢንዶኔዥያ መላሾች ለሽብርተኞች ተግባር ተቃውሟቸው "ሰብአዊነትን ወይም ሃይማኖታዊ ማስረጃዎችን" አቅርበዋል። ለምሳሌ አንድ ሙስሊም እንስት በቅዱስ ቁርአን 5:32 ላይ ያለውን ጥቅስ በራሷ አባባል "የአንድ ሰውን ነፍስ ማጥፋት ዓለምን እንደማጥፋት ነው" ስትል መልሳለች።

በተቃራኒው የ9/11ን ጥቃት ከሚደግፉ ኢንዶኖገርያዊ መካከል አንድም ሰው ሃሳቡን እንዲደግፍለት አንድ የቅዱስ ቁርአን ጥቅስ ማምጣት አልቻለም። የነዚህ ስብስቦች ምክንያት ሴኩላርና ዓለማዊ ነው። ለምሳሌ አንድ ኢንዶኔገርያዊ መላሽ "የአሜሪካ መንግስት ሌሎች አገራትን እጅግ ተቆጣጣሪ ነው፤ ቅኝ ገዥ ይመስላል" ብሏል።

የሽብርተኝነትን ተግባር በሚደግፉና በሌሎች መካከል ያለው እውነተኛ ልዩነት ሃይማኖታዊ ቀናኢነት ሳይሆን ፓለቲካ ነው።

ታዲያ እንዴት በአክራሪዎች ዘንድ ገናና የሆነውን ሃይማኖታዊ ንግሮች ሁነት ልንረዳው እንችላለን? መረጃዎች በግልጽ እንደሚያመለክቱት በፕሬዝዳንት ገማል አብዱልናስር ጊዜ ሴኩላር አረብ ብሔርተኝነት ገናና እንደነበረው በአሁኑ ወቅት በዐረቦችና ሙስሊሞች ዘንድ ሃይማኖት ገዥ ርዕዮተ ዓለም ሆኗል። ከጥንስሱ ጀምሮ የአክራሪ ሴኩላሮች ስብስብ የሆነው የፍልስጤም ነጻ አውጭ ተቋም (PLO) የሽብር ወይም አባላት ምልመላ ተግባር ለመፈጸም የፍልስጤም ብሔርተኝነት ሲጠቀም ነበር። ያኔ





በ1960ዎቹ ዓረብ ብሔርተኝነት አክራሪነትንና ሽብርተኝነትን ለመደገፍ ጥቅም ላይ እንደዋለው አሁን ደግሞ ተራው የሃይማኖት ሆኗል።

በሃይማኖትና ሽብር መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር ሁሬና እጅግ የተወሳሰበ ማዕቀፍ ይጠይቃል። በታሪክ በሃይማኖት፣ ፓለቲካና ህብረተሰብ መካከል ጥብቅ ቁርኝት አለ። መሪዎች ድርጊታቸውን ቅቡል ለማድረግ፣ ለቅዱስ ትግል የሚደረግን ውጊያና ሞት ለማገላት ሃይማኖትን ተጠቅመዋል።

## ሃይማኖትና ፓለቲካ፡ ትላንትና ዛሬ

ዛሬ በርካቶች በሃይማኖትና ፓለቲካ መካከል ያለው ግንኙነት የኢስላም ብቸኛ መለያ አድርገው ይመለከታሉ። ነገር ግን ሌሎች ሃይማኖቶች ከፓለቲካ ጋ የነበራቸውን ቁርኝት ታሪክ ሲመዘግብ የኖረው ሀቅ ነው። በጁዳይዝም የፍልስጤም መሬትን የመማረክና በዚያ የመስፈር ሂደት ሲመራ የነበረው በአምላክ ነበር። ንጉስ ዳዊትና ንጉስ ሰለሞን የተቀቡት በአምላክ ነበር። በክርስትናንም ወ[illegible] ንጉሦችና አፄዎች ሲነግሱ የነበረው በጳጳሶች የይሁንታ ድጋፍ ነበር። [illegible] ዑርባን II "የአምላክ ፍቃድ ነው" ያሉትን መስቀታዊ ትዕዛዝ ያስፈፀሙ ቅዱስ ጦርነት መስቀለኞቹ ተዋግተዋል። "ዘውድና መስቀል" የሚባለው ኢምፔሪያሊያዊ መስፋፋትና ክርስቲያናዊ ተልዕኮ ለአውሮፓ ኮሎኒያሊስቶች (ቅኝ ገዥዎች) እና ማራኪዎች መግፍኤ ነበር። በህንድ ነገሥታት መለኮታዊ ስርዓት እና የሂንዱይዝምን የመደብ ክፍፍል ሥርዓት ደጋፊ ቀኖና- ዳርማ- ጠባቂዎች ነበሩ።

በቅርብ አስርት ዓመታት ውስጥም በዓለም ዙሪያ በተካሄዱ የነጻነት፣ ወረራን የመከላከል ትግሎች እንዲሁም በሽብር ጥቃቶች ውስጥ ሃይማኖት የጎላ ሚና ተጫውቷል። ይህን በህንድ በሂንዱችና ሲኮች መካከል ባለ ግጭት፤ በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ በሙስሊም ቦስኒያዎች፣ ካቶሊክ ክሮዋቶች እና ኦርቶዶክስ ሰርቦች መካከል በነበረው ጦርነት፤ በሊባኖስ

በክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞችና ድሩዝ ሚሊሺያዎች መካከል በተካሄደው የእርስ በእርስ ጦርነት፤ በአየርላንድ በፕሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች፣ በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በናይጄሪያ፣ በሙስሊሞቹ (ሃማስና ኢስላሚክ ጀሃድ) እና አይሁድ አክራሪዎች (የጉሽ ኢሙኔይም፣ የሜይር ካሀን ካች ፓርቲና እና ዩጋል አሚር) በእስራኤልና ፍልስጤም ማየት እንችላለን።

በአሜሪካም ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ውስጥ እጅግ በርካታ የሽብር ጥቃቶች የተፈሙት በክርስቲያን የሽብር ቡድኖች ነው። የካቶሊክ፣ ሉትራንና ፕሪስፓይቴሪያን አክቲቪስቶች የሶዶማዊያንን ቡና ቤቶች በቦምብ አጋይተዋል። የፅንስ ማስወረድ አገልግሎት የሚሠጡ ክሊኒኮች አባላት ላይ ተኩሰዋል ወይም ግድያ ፈፅመዋል፣ ክሊኒኮቹንም በቦምብ አጋይተዋል። የነጭ ክርስቲያኖች ልዕልና የሽብር ቡድን በአትላንታ ሴንቴንያል ኦሎምፒክ ፓርክ እና በሌሎች ቦታዎች በርካታ ጥቃቶች ፈጽሟል። ቲሞቲ ማክቬይ በኦክሎሃማ የአልፍሬድ ሲ፡ ፒ.ሙራህ ፌዴራል ህንጻን ያጋየው በዊሊያም ፒርስ ክርስቲያናዊ አስተምሮት ነው። መሪዎች ቅዱስና እርኩስ ጦርነታቸውን ህጋዊና ቅቡል ለማድረግ የተለያዩ ሃይማኖቶችን ተገልግለውባቸዋል።

## ሃይማኖትና አጥፍቶ መጥፋት

እጅግ የተስፋፋውና አውዛጋቢው የሽብር ተግባር አጥፍቶ መጥፋት ነው። ከ1980ዎቹ ጀምሮ በሙስሊምና ታሚል ታይገር ጦረኞች የመከላከል ስትራቴጂያዊ መሳሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል። አጥፍቶ ጠፊዎች በቅዱስ ጦርነትና በሰማዕት የገነት ምንዳዎችን ታገኛላችሁ አስተሳሰብ ከተቀየዱ ሃይማኖታዊ አክራሪዎች ወይም ጽንፈኞች ጋ ተቆራኝተዋል። ምንም እንኳ ሽብርተኞች ፈቃደኞችን ለመመልመል ሃይማኖትን ቢጠቀሙም፣ በርግጥ ግን ሃይማኖት የሽብርት ጥቃትን ለመፈጸም ቁልፍ ሚና ይጫወታል?





ከ1980 እስከ 2004 ድረስ በተፈጸሙ እያንዳንዱ የሽብር ጥቃቶች ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው የውጪ ሃይል ወረራ በእያንዳንዱ ላይ በሚያስብል ሁኔታ እንደ መንስኤ ቀርቧል።

ሮበርት ፓፔ *Dying to Win: The Logic of Suicide Terrorism* በሚለው መፅሐፉ ሲናገር

> "ማዕከላዊው ሐቅ የአጥፍቶ መጥፋት የሽብር ጥቃቶች በሃይማኖት መግፍኤነት የሚፈጸሙ አይደሉም፤ አሸባሪዎቹ የዘመናዊ ዲሞክራሲ አገራት ጦራቸውን የእናት አገሬ ምድር ከሚሉት ምድር እንዲያውጡ ለማስገደድ የሚፈፅሟቸው ግልጽ ስታራቴጂያዊ ግቦች ናቸው። ከሊባኖስ እስከ ስሪላንካ፣ ቼቺኒያ፣ ካሽሚርና ዌስት ባንክ የተፈፀሙ እያንዳንዱ ጉልህ የአጥፍቶ ጠፊ የሽብር ዘመቻ ከ95% በላዩ፣ ማዕከላዊ ግቡ ዲሞክራሲያዊ መንግስታት አገራቸውን ለቀው እንዲወጡ ነው።"

እውተኛን ወይም የታሰበን ወረራና ኢፍትሃዊነትን ለመከላከል፣ ሃይማኖታዊ ሆነ ሃይማኖታዊ ያልሆኑ ቡድኖች የሽብር ድርጊታቸውን በተደጋጋሚ ሃያል በሆነው ሃይማኖታዊ ማዕቀፍ ውስጥ ያስቀምጣሉ።

በስሪላንካ የማርክሲስት ሌኒኒስት ቡድን የሆነው ታሚል ታይገር ዋናው ታክቲኩ አጥፍቶ መጥፋት ነበር። አገራቸውን ከሺን ሃሌስ ቡድሂስቶች ነጻ ለማውጣት ወደ ታሚል ሂንዱ ማንነት ተጠግተዋል። ሐማስ የተመሰረተው የእስራኤልን ወረራ ለመከላከል ነበር። ነገር ግን ህልውናውን ለማቆየት እና የሽብር ተግባሩን ለመፈጸም ሃይማኖትን እየተጠቀመ ነው። ሌላው ይቅርና ሴኩላሩ የአል-አቅሳ የሰማዕታት ብርጌድ የአጥፍቶ መጥፋት ተግባሩን ለመፈጸም ሃይማኖትን ነው የሚጠቀመው። ድርጅቱ ስያሜውን ያደረገው በእየሩሳሌም በሚገኘው ቅዱስ ሃይማኖታዊ ቦታ- አል-አቅሳ ነው። የወደቁ

ታጋዬቹን "ጂሃዲስት" ወይም ሰማዕት ነው ብሎ የሚጠራቸው። የ9/11ን ጥቃት ከፈጸሙት አንዳንድ አሸባሪዎች ሃይማኖተኞችም አልነበሩም። ነገር ግን ከሞት ጋ ሲፋጠጡ ፊታቸውን ወደ ሃይማኖት አዙረዋል።

በ2004 በማድሪድ የቦምብ ጥቃት የፈጸሙት የአል-ቃኢዳ አባላት ነበሩ። ስፔን በወረራ የያዘችው አገር ባይኖርም በወቅቱ የነበሩት የስፔን ጠቅላይ ሚኒስትር የኢራቅን ወረራ ይደግፉ ስለነበር ከምርጫ በፊት መራጮችን ለማስፈራራት ነበር። (ስትራቴጂው የተሳካ ነበር። አዲሱ መንግስት ስልጣን ላይ እንደወጣ በኢራቅ ያለውን የስፔን ጦር ሙሉ በሙሉ አውጥቷል።) እንደ ፓፔ ጥናት ከ1995 እስከ 2004 መጀመሪያ ድረስ ከተፈፀሙ የአል-ቃኢዳ ጥቃቶች 2/3 የሚሆኑት አሜሪካ ጦሯን በስፋት ካሰፈረችባቸው ቦታዎች የተነሱ ነበሩ።

ፓፔ እንደሚለው

> *"ከኛ ወረራ በፊት ኢራቅ በታሪኳ አንድም የአጥፍቶ መጥፋት የሽብር ጥቃት አልተመዘገበባትም ነበር። ከኛ ወረራ ጀምሮ ግን የአጥፍቶ መጥፋቱ ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ አድጓል። በ2003 20 ጥቃቶች፣ 48 በ2004፣ በ2005 በመጀመሪያዎቹ አምስት ወራት ብቻ ከ50 በላይ ጥቃቶች ተፈጽመዋል። አሜሪካ በኢራቅ 150,000 ወታደሮችን ባሰፈረችባቸው እያንዳንዱ ዓመት የአጥፍቶ መጥፋቱ ሽብር በእጥፍ አድጓል።"*

## አሜሪካንን እንዴት ነው የሚመለከቷት?

በኢንተርናሽናል ሄራልድ ትሪቡን የካርኒጌው ምሁር ፈዋዝ ገርጅስ በጻፈው ጽሁፍ ላይ በካይሮ ከግብጻዊው የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ሐዝም ሰላም ጋ ያደረገውን ቃለ መጠየቅ የተወሰኑ መስመሮች እንደሚከተለው ያስታውሳቸዋል። በሃያዎቹ የእድሜው ክልል ውስጥ የሚገኘው ይህ





አክቲቪስት ለገርጅስ "አሜሪካኖች በኢራቅ የሚያደርጉትን ተመልከት። አሜሪካ ሙስሊሞችን ቅኝ ለመግዛትና ዘይታቸውን ለመስረቅ የዲሞክራሲ ጭንብል እየተጠቀመች ነው።" ነበር ያለው። ገርጅስ ጆርጅ ድብልዩ ቡሽ በዐረቡ ዓለም ዲሞክራሲ እንዲስፋፋ እየጣረ እንደሆነ ሲያስታውሰው፣ ሰሊም "በፍጹም እርሱ ቀውስና የእርስ በእርስ ጦርነት ነው የሚያስፋፋው" ብሎ መልሶለታል።

አሜሪካ ዲሞክራሲ ማስፋፋት ግቤ ነው ብትልም ሠፊ የሙስሊም ማህበረሰብ ይህን ግቧን በቁም ነገር እንደያዘችው በጥርጣሬ ነው የሚመለከቱት።

- በግብጽ 24%፣ በዮርዳኖስና ቱርክ 16% ብቻ ናቸው አሜሪካ ዲሞክራሲ አስፋፋለሁ የምትለውን ነገር የተቀበሉት።
- የተሻለ ተቀባይነት ያላት በሊባኖስ (54%)፣ ሴራሊዮን (68%) እና አፍጋኒስታን (53%) ብቻ ነው።

ፓለቲካ አክራሪዎች ለዓለም ጉዳዬች ቅርብና ጨለምተኞች ናቸው። አሜሪካንና የዲሞክራሲ አስፋፋለሁ ግቧን በጥርጣሬ የሚመለከቱት የሚበዙት በነዚሁ ዘንድ ነው። 52% የሚሆኑት መካከለኞች በጥርጣሬ ሲመለከቷት የፓለቲካዊ አክራሪዎቹ ወደ ሶስት አራተኛ (72%) ያሻቅባል።

በርካታ ሙስሊሞች ዲሞክራሲንና የሰብአዊ መብት አያያዝን በተመለከተ አሜሪካኖችንና ምዕራቡ ዓለምን በዓረቡና ሙስሊሙ ዓለም ላይ በሁለት ፊትነት (ደብል ስታንዳርድ) ምልከታ ይከሷቸዋል። "እስራኤል ፍልስጤማውያንን ስትደበድብ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብና ዩ ኤን በአላየንም ዝም ይላሉ" ይላል የጆሱ ፓለቲከኛና ሙስሊም ማህበረሰብ መሪ ሳልሀ ባየሪ። በመቀጠልም "ነገር ግን ፍልስጤማውያን መልሶ ማጥቃት ሲያደርጉ

አሜሪካ፣ ዩ ኤን እና ሌሎች የእስራኤል ወዳጆች እንደ ሽብር ተግባር ወስደውት ኩነኔ ያወርዳሉ። ይህ ችግር ነው። ይህ ሙስሊሞችን በተመለከተ ሁለት ፊታዊ እይታ እንዳላቸው ያሳያል" ብሏል።

በዓረቡ ዓለም ዋና የምዕራቡ ዓለም የትምህርት ተቋም ከሆነው የካይሮ አሜሪካ ዩንቨርስቲ አንዲት ሴት ተማሪ ከገርጅስ ጋ ባደረገችው ቃለ መጠይቅ "ቡሽ እስራኤል ፍልስጤምንና ሊባኖስን እንድታጠቃ ሽፋን ነው የሰጣት። በሽብር ላይ የተከፈተው ጦርነት መደምደሚያ የሌለው በኢስላም ላይ የተከፈተ ጦርነት ነው።" ብላለች።

በአስር ሙስሊም ብዙሃን በሆኑ አገራት የሚኖሩ ሙስሊሞች የተለያዩ አገራትን እንዴት እንደሚመለከቷቸው ስቀረበላቸው ጥያቄ አሜሪካን በሚከተሉት መግለጫዎች ነው የገለጹዋት፡- ጨቋኝ (68%)፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የመጠቀች (68%)፣ ተናካሽ (66%)፣ ዕብሪተኛ (65%)፣ በስነ ምግባር የዘቀጠች (64%)።

## "በኢስላም ላይ የተከፈተ ጦርነት"

"በኢስላምና ሙስሊሞች ላይ የተከፈተ ጦርነት" የሚለው ሐረግ ከሞሮኮ እስከ ሚንዳናኦ ድረስ በሰፊው የሚታመን ንግግር ነው። በ2007 ወርልድ ፐብሊክ ኦፒኒየን ዶት ኦርግ ባደረገው ጥናት በሞሮኮ፣ ኢንዶኔዢያ፣ ግብጽና ፓኪስታን ጎልቶ በሚታይ ብዙሃን ሙስሊሞች ዘንድ የአሜሪካ ዓላማ "የኢስላሙን ዓለም ማዳከምና መከፋፈል ነው" ተብሎ ይታመናል። ምላሽ ከሰጡት በርካታዎች፣ በመካከለኛ ምስራቅ ክርስትናን ማስፋፋት እና ኢስላም እንዳያድግና ምዕራቡን ዓለም ከመገዳደር ለመከላከል (በየቅደም ተከተላቸው) እንደ አሜሪካ ፍላጎት ተጠቅሰዋል። ለብዙዎች የምዕራቡ፣ በተለይ የአሜሪካ ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ እና የባህል ልዕልና የራስን ዕድልን በራስ በመወሰንና ኢስላማዊ ማንነት ላይ የተጋረጠ ስጋት ነው።





ጋሎፕ በ"አንተ/አንቺ አስተያየት ከምዕራቡ ዓለም የምትኮንነው/ንኚው ምንድነው?" ብሎ ላቀረበው ክፍት ጥያቄ በመካከለኞቹ ሆነ አክራሪዎች በተደጋጋሚ የተሰማው መልስ "ወሲባዊነትና ልቅ ባህል" የሚል ነበር። "የሥነ ምግባር ንቅዘት እና ለሙስሊሞች ያላቸው ጥላቻ" ምላሾች ተከትለዋል።

ሌላው የቅሬታ ምንጭ በምዕራቡ ሚዲያ ሙስሊሞች የሚሳሉበት መንገድ ነው። በ900 ዐረብ ገፀ ባህሪይ በተሳሉባቸው ፊልሞች ላይ በተደረገ ጥናት በአብዛኞቹ ላይ የዘረኝነት ገፀ ባህሪ ቀረጻ ታይቷል። በምዕራብያውን ብዙሃን መገናኛዎች ለተርታው ሙስሊም እና ባህሉ የተሰጠ ምንም ሽፋን የለም ማለት ይቻላል። ካለም ፍጹም ተበላሽቶ ነው የሚቀርበው። በተጨማሪም በሙስሊሙ ዓለም ታዋቂ የሆኑት የምዕራቡ ዓለም የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና ፊልሞች ተመልካቹን የምዕራቡን ዓለም ፋሽን፣ ሰብዕናዎችና ስኬቶች ተከታይ ግልብ ነው የሚያደርጉት።

ከመካከለኞቹ ይልቅ በርካታ ቁጥር ያላቸው ፓለቲካዊ አክራሪዎች የምዕራቡ ዓለም ባህል፣ ኢሞራላዊነትንና የሞራል ንቅዘት ለቅሬታቸው ዋና ምክንያቶች ናቸው። ነገር ግን (ይህ በጣም አስፈላጊ ነው) በሙስሊሙ ዓለምና በምዕራቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል አንድም መላሽ "ኢሞራላዊ አይሁኑ፣ አይንቀዙ" ያለ የለም። የንዴታቸው አስኳል ምክንያት ይህ አይደለም። ሙስሊሞች መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር እየጠየቁ ያሉት የምዕራቡ ዓለም ማንነቱን ይለውጥ ሳይሆን የሚሠሩትን ያስተካክሉ ነው- ኢስላምንና ሙስሊሙን እንዲያከብሩ እንዲሁም በተወሰኑ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲዎቻቸው ላይ ተጨባጭ ለውጥ ያድርጉ። የአሜሪካ ዩኒቨርስቲ ላደረገው ጥናት የአስራ ስድስት ዓመቱ ዩርዳኖሳዊ የሁለተኛው ደረጃ ተማሪ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡-

> *የምዕራቡ ዓለም ሰዎች ከታፈኑበት አረፋ ወጥተው*
> *ወደዚህ የዓለም ክፍል ቢመጡ በፓለቲካ ምን ያህል*
> *እንደተበደልን (ዘይት፣ ኢራቅ፣ ፍልስጤም፣ ኢራን)*

*በተመለከቱ ነበር ብዬ አምናለሁ። ምዕራቡ የግድ ስለዚህ ዓለም ከታማኝ መረጃዎች መማርና ተጨባጭ ዕይታ መያዝ እንዲሁም ቡሽ የሚሠራው በሙሉ ትክክል ነው ብሎ ከማሰብ መቆጠብ አለባችው።*

ስለዓለም አቀፍ ፓለቲካ ባላቸው ዕውቀትና ባህላዊ ዕሴቶቻቸውን ለመጠበቅ ባላቸው ቁርጠኝነት ፓለቲካዊ አክራሪዎቹ የምዕራቡን ዓለም ፓለቲካዊ፣ የጦር እና የባህል ግኑኝነት እንደ አደጋ በመመልከቱ ረገድ መረር ያሉ ናቸው። ስለ አገራችው መጻኢ ጊዜ ያላቸው ትልቁ ስጋታቸው ምን እንደሆነ ሲጠየቁ ፓለቲካዊ አክራሪዎቹ በተደጋጋሚ የሚጠቅሱዋቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው- በአገራችው የውስጥ ጉዳይ የሌሎች አገሮች ጣልቃ ገብነት፣ ብሔራዊ ደህንነት፣ ቅኝ መገዛት፣ ወረራ፣ አገራዊ ዘረፋ፣ ሃያል ትክክል ነው አስተሳሰብ፣ የአሜሪካ ገናናነት። መካከለኞቹ በተጻራሪ የሚጠቅሱት የኢኮኖሚ ችግሮችን ነው።

ይህን የተወጠረ ስሜት (ስጋት) የሚያሳይልን፡ ምዕራቡ ዓለም ከዓረብ-ሙስሊሙ ዓለም ጋ በመቻቻል ለመኖር ፍላጎት የለውም የሚለውን ሃሳብ ከመካከለኞቹ ይልቅ ፓለቲካዊ አክራሪዎቹ ይደጋግሙታል- 40% አክራሪዎች፣ 20% መካከለኞች። በምዕራቡ እና በዓረቡ/ሙስሊሙ ዓለም የተሻለ መግባባት የሚፈጠርበት ጊዜ መቼውንም አይመጣም በሚለውም ላይ አክራሪዎቹ እንዲሁ የበለጠ ድርሻ ይወስዳሉ 37%፤ ይህን ሀሳብ የሚያስተጋቡ መካከለኞች 20% ናቸው።

ይበልጥ የሚያስገርመው ነገር ግን ለሌሎች ጥያቄዎች ከሰጡት ምላሾች ጋር ተመጋጋቢ የሆነው ከተጠያቂ ፓለቲካዊ አክራሪዎች መካከል ግማሽ የሚሆኑት "አንድ ሰው ላመነበት ነገር መስዋዕት መሆኑ" "መሉ ለሙሉ ህጋዊ ነው" ብለው ያምናሉ። ይህ አስተሳሰብ ከመካከለኞቹ 18% የሚሆኑት ያስተጋቡታል።





በሎንዶን 7/7 የሽብር ጥቃት በኃላፊነት ከተጠየቁ አራት ግለሰቦች መካከል ሙሐመድ ሲዲቅ ካን፣ በአል-ጀዚራ ኔትወርክ በተለቀቀው የቪዲዮ ምስል ስለ መግፍኤው ሲናገር

*"እኔ እና እንደኔ ያሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ለምናምንበት ስንል ሁሉን ነገር ትተናል ...ህዝቤን በቦምብ መደብዳባችሁ፣ በጋዝ ማጠናችሁን፣ እስራችሁንና ስቅየታችሁን እስካላቆማችሁ ድረስ ይህን ውጊያ አናቆምም። እኛ ጦርነት ላይ ነን፣ እኔ ደግሞ ወታደር ነኝ። አሁን እናንተም ያለንበትን ሁነት እውነታ ታጣጥማላችሁ።"* ብሏል።

## ለሽብር ተግባር ሽፋን መስጠት የሙስሊሞች ሞኖፓሊ ነውን?

**ዋናው ጥያቄ፡ በርግጥ አንድ ሙስሊም የሽብር ተግባር ሲፈፅም ከሃይማኖታዊ ቀናኢነት በመነጨ ካልሆነ፣ ታዲያ ለምን የሽብር ተግባርን መደገፍ በሙስሊሞች ዘንድ በስፋት ያለ የሚመስለው? ወይስ በርግጥ አለን? መልሱ የለም ነው፣ ሙስሊሞች አክራሪ ዕይታን የመደገፍ ሞኖፓሊ የላቸውም። እንደውም ከአሜሪካ ህዝብ አንጻር በንፁሃን ሰዎች ላይ የሚደረግ ጥቃትን ካለምንም ቅደመ ሁኔታ በመቃወም የተሻሉ ናቸው።**

በቅርብ የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው "ንጹሐን ዜጎችን ዒላማ አድርጎ በእነርሱ ላይ ቦምብ ማፈንዳት ሆነ ሌሎች የሽብር ጥቃቶች መፈጸም በፍጹም ትክክል አይደለም" ያሉ አሜሪካዊያን 46% ሲሆኑ 24% የሚሆኑት እነዚህ ጥቃቶች "አብዛኛውን ወይም አንዳንዴ ትክክለኛ ናቸው" ብለዋል።

ይህን በዚያው ዓመት ሙስሊሞች በብዛት ከሚኖሩባቸው አገራት ከተወሰደ ጥናት ጋ አመሳክሩት፣ 74% የሚሆኑ ኢንዶኔዥያውያን

የሽብር ተግባር "በፍጹም ህጋዊ" አይደለም ሲሉ ይህ ፐርሰንት በፓኪስታን 84%፣ በባንግላዴሽ 81%፣ በኢራን 80% ተመዝግቧል።

በተመሳሳይ መልኩ 6% የሚሆኑ አሜሪካኖች በንፁሐን ዜጎች ላይ የሚደረግ ጥቃት "ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው" ሲሉ፣ በአንጻሮ ይህ ውጤት በሊባኖስና ኢራን 2% ሲሆን በሳዑዲ አረቢያ 4% ሆኗል። በአውሮፓ፣ በፓሪስና ለንደን የሚኖሩ ሙስሊሞች ከተቀረው ነዋሪ አንጻር ለ"ቅዱስ ዓላማ" ሲባል እንኳ በንፁሐን ዜጎች ላይ የሚደረግን ጥቃት እና ሽብርን በመቃወም ረገድ የተሻለ ሆነው ተገኝተዋል።[27]

አሁንም ቀላል የማይባል ጥያቄ ሊጠየቅ ይችላል- ሙስሊሞች በርግጥ የሽብርን ተግባር የሚቃወሙ ከሆነ ለምን ይሆን አሁንም ሽብር በሙስሊሞች ምድር የሚፈለፈለው?

[27]ጥናቱን ያደረገው WorldPublicOpinion.org Poll ሲሆን በሴፕቴምበር18/2007http://www.worldpubilicopinion.org/pipa/pdf/jan 07/Iran_Jan 07_rpt.pdf ድረ ገፃቸው የተወሰደ ነው።





## *ከ"ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው" ባሻገር*

### *በፕ/ር ያሚድ ሳፊ[28] እና በዶ/ር አቡ አል ፋድል[29]*

በማርች 2002 አጋማሽ አካባቢ አንድ በሳዑዲ የሚታተም ጋዜጣ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በተወለዱበት መካ ከተማ የተፈጠረ አንድ አሰቃቂ ክስተት ዘግቦ ነበር። ክስተቱ የህዝብን ቁጣ፤ የመንግስት ጥብቅ ምርመራ እና የዐቃቢ ህግ ክስ የሚያስከትል ቢሆንም ምንም እንዳልተፈጠረ በቸልታ ታልፏል። አሁን ጭራሹኑ ተረስቷል። እንደ መንግስት ገለጻ በሴቶች የህዝብ ትምህርት ቤት በደረሰ ቃጠሎ ቢያንስ አስራ አራት የሚሆኑ ሴቶች በእሳት ተቃጥለው ወይም በጭስ ታፍነው ሞተዋል።

በቦታው ተገኝተው የነበሩ ወላጆች የተፈጠረውን ዘግናኝ ሁኔት እንዲህ ነበር የገለጹት- ልጃገረዶቹ የሚማሩባቸው ክፍሎች ከውጪ ተቆልፈዋል፣ የሳዑዲ የኃይማኖት ፓሊሶች (ሙጠዋዑን ይባላሉ) ከእሳቱ ያመለጡትን ሴቶች እየደበደቡ ወደ እሳቱ ይመልሳሉ፣ እነርሱን ሊያድኑ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩትን የእሳት አደጋ ሰራተኞችን ይከለክላሉ። ክስተቱን እንደተመለከቱት ወላጆች፣ የእሳት አደጋ ሰራተኞች እና

[28] ፕ/ር ያሚድ ሳፊ በኖርዝ ካሮሊና ዩኒቨርስቲ በሃይማኖቶች ጥናት ፕሮፌሰር ሲሆን የበርካታ ሥራዎች ባለቤት ነው።
[29] ዶ/ር አቡ አል ፋድል ከዬል ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ አለው፤ ከፔንሲልቫንያ ሎው ስኩል ጂ ዲ፣ ከፕሪስተን ዩኒቨርስቲ በኢስላሚክ ሎው ኤም ኤና ፒ ኤች ዲ አግኝቷል። ዶ/ር አቡ አል ፈድል በርካታ ሥራዎች ያሉት ሲሆን የሚከተለው ምዕራፍ ያሚድ በኤዲተርነት አቡ አል ፋድል በተሳታፊነት በተገኙበት Progressive Muslims: On Gender, Justice, and Pluralism Collection ተቀንጭቦ የተተረጎመ ነው።

መደበኛ ፓሊሶች ሙጠዋዑኖቹ ሴቶቹ ከእሳቱ እንዳያመልጡ የከለከሉዋቸው በ"ሥርዓቱ" ስላልለበሱና በሴቶቹና በወንዶቹ መካከል አካላዊ ግንኙነት እንዳይፈጠር ነበር። እነዚህን የሃይማኖት ፓሊሶች የሚቆጣጠረው የመንግስት አካል ፓሊሶቹ የመማሪያ ክፍሉቹን ከውጪ እንዳልቆለፉ፣ ሴቶቹንም ሆነ የአደጋ ተከላካዩቹን እንዳልደበደቡ ቢክድም በቦታው የነበሩ ወላጆች ለጋዜጣው ያረጋገጡት የተቃራኒውን ሁነት ነበር። በርካታ ወላጆች ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት ከሙጠዋዑኖቹ ጋር ክርክር የገጠሙ ሶስት ሴቶች በዱላ ተደብድበዋል። በርካታ ሴቶች የሙጠዋዑኞቹን ትዕዛዝ ተቀብለው ሂጃባቸውን ለመልበስ ወደ ት/ቤቱ ቢመለሱም፣ በኋላ ላይ ግን ሞተው ተገኝተዋል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ዓለምን ባስደነገጡ እያስደነገጡ ባሉ በርካታ ትዕንቶች ተቀስፏል። እነዚህ መቅሰፍቶች እጅግ ሰፊ ከመሆናቸው የተነሳ ከአውሮፓና አሜሪካ እስከ ጃፓን እና ሩሲያ ያሉ ነዋሪዎች ኢስላማዊ ባህልን ከጭካኔና ከርዳዳነት ጋር ሲያያይዙት ይታያል። አንድ ከየትኛውም የዓለም አካባቢ ከመጣ ሰው ጋር በኢስላም ዙሪያ ከሚደረግ ውይይት በተደጋጋሚ በጉልህ የሚታየው የኢስላም ምስል ሰብአዊነት የሌለበት ወይም ሰብዓዊ ያልሆነ ነው። በርግጥም ለበርካታ ሙስሊም ያልሆኑ ግለሰቦች ኢስላም የሚታያቸው ለሰው ልጆች እዝነትና ርህራሄ የሌለው ክስኪሳ ሃይማኖት ሆኖ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው በሳዑዲ የተከሰተው ትዕይንት የመጨረሻው አይደለም። በዘመናዊው የኢስላም ታሪክ ከተፈጸሙ ጤነኛ ያልሆኑና ለግንዛቤ ከራቁ ትዕይንቶች መካከል አንዱ ቢሆን እንጂ። ዘ ሳታኒክ ቨርስስ እና በደራሲ ሰልማን ሩሽዲ ላይ የተላለፈው የሞት ብይን፣ በፓኪስታና ናይጄሪያ የመደፈር ጥቃት ሰላባ የሆኑ ሴቶችን በድንጋይ ቀጥቅጦ መግደል፣ የጣሊባኖች የሴቶች አያያዝ፣ በአፍጋኒስታን የቡድሃ ሃውልቶች መፍረስ፣ በሳዑዲ አረቢያ በቤት ሰራተኞች ላይ የሚደርሰው





የወሲብ ትንኮሳ፣ በግብፅ ፀሐፊዎችን ማግለል፣ በሽብር ጥቃት ንፁሐን ዜጎችን መቅጠፍ፤ እነዚህ ክስተቶች በሙስሊሙ ህብረተሰብ የታሪክ ገፆች ላይ አሳዛኝና አስቀያሚ ጠባሳ ያሳረፉ የተወሰኑ ምእራፎች ናቸው።

በእነዚህ አስቀያሚ ጠባሳዎች ያፈሩ እና ቅሬታ የተሰማቸው ያን ያህል ረች ያልሆኑ መከራከሪያዎችን አቅርበዋል። ከሙስሊሞች በብዛት የሚሰማው መከራከሪያ ሃይማኖቱን ከተከታዮቹ ጋር በአንድነት ማየት ትክክል አይደለም የሚለው ነው። ተከታዩቹ በሃይማኖቱ ስም የሚፈፅሙትን ነገሮች ሆነ የሚያሳዩትን ባህሪዎች ሃይማኖቱ ያፀድቃቸዋል ወይም ደንግጎታል ማለት አይደለም። ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆነ እና በተደጋጋሚ የሚነሳው ሌላው መከራከሪያ የኢስላም ቀኖናዎች ከሙስሊሞች ባህል ይለያል የሚል ነው። ምን ማለት ነው፣ ለእንደነዚህ አይነት ያልተገቡ ባህሪያት እና ድርቶች ተጠያቂው ኢስላም ሳይሆን ባህል ነው።

እነዚህን መከራከሪያዎች ረች አይደሉም የምላቸው ትክክል ስላልሆኑ አይደለም። ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ሉ ... ዋቹ ወይም ሐቅ ናቸው። መከራከሪያዎቹ ረች አይደሉም ያልኩበ ምክንያት የተለያዩ ተከታይ መከራከሪያዎችንና ችግሮችን የዘነጉ መሆናቸው ነው። ለምሳሌ የአሁኑን ጊዜ ለመረዳት ታሪክ ያለውን ሚና እና ሁልጊዜ በእምነት ስርዓትና በእርሱ ዙሪያ በበቀሉት ማህበራዊ ሁነቶች መካከል ቀዶ ጥገናዊ ልዩነት ማድረግ እንደማይቻል ይዘነጋሉ። በተለይ እነዚህ መከራከሪያዎች ቀኖናዎችን በመወሰንና በመተግበር ላይ ሰብአዊ ግለሰባዊነት ያለውን ሚና ግንዛቤ ውስጥ የከተቱ አይደሉም።

ከላይ በሳዑዲ ትምህርት ቤት በልጃገረዶቹና በመካ የሃይማኖት ፓሊሶች መካከል የተፈጠረው ክስተት ሁሉንም ሙስሊሞች ረዘም ላለ ጊዜ በጥንቃቄ እንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ይገባል። ክስተቱ የአይን እማኞቹ በዝርዝር እንዳወሱት ከተፈፀመ ሙስሊሞች ከቅርብ ጊዜያት

ወዲህ ያሳለፉትን ተሞክሮዎች በድጋሚ ሊያጤኑ ግድ ይላል። ይህ ክስተት በኢስላም ውስጥ ያለ አንድ የአስተሳሰብ መስመር በሴቶች ላይ ያለውን አሳዛኝ ምልከታ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ወቅት የተንሰራፋውን የኢስላምን ቀኖናዎችና ህግጋት በአግድም መረዳት ነው። እጅግ በወረደ ደረጃ አንድ ሰው የኢስላም የሂጃብና ፆታዊ የመለያየት ደንቦች እጅግ የከረሩ ናቸው ብሎ ቢያስብ እንኳ የሰውን ሕይወት የማዳን ኢስላማዊ ህግጋት እነዚህን ደንቦች በበለጠ ነበር። በተጨማሪም በአንድም ሆነ በሌላ ሁኔታ ሴቶች እንዲገለሉ የደነገገ ህግጋት አሉ ካልን ቅዱስ ቁርአን ራሱ አስረግጦ እንደሚናገረው በአንድ እና አንድ ምክንያት ብቻ ነው- ሴቶችን ከባለጌዎችና ከአደጋ ለመከላከል።[30] እነዚህ እንስቶች እንዲሞቱ የተፈረደባቸው ምክንያት ከዚህ የቅዱስ ቁርአን ምክንያት እና ሴቶች እንዲገለሉ አድርገዋል ከሚባሉ ህገ-ምክንያቶች ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው።

ሌላም በትዝብት ልንመለከተው የምንችለው ነገር አለ። የእነዚህ ሴቶች ህይወት ለሳዑዲ የሃይማኖት ፖሊሶች ቅንጣት ታክል ዋጋ ቢኖረው ኖሮ፣ እነዚህ ፖሊሶች የተማሪዎቹን ክፍሎች ከፍተው በአካባቢው የተሰበሰቡትን ወንዶች አባረው ሴቶቹ በወንዶች ሳይታዩ ከቃጠሎ እንዲያመልጡ ባደረጉ ነበር። የኃይማኖት ፖሊሶቹ እንደውትንሽ ቢያስቡ ኖሮ በጭንቅላታቸው ላይ የጠመጠሙትን (ጉትራ ይባላል) መቀነት አውልቀው በሴቶቹ ጭንቅላት ላይ ባደረጉ ነበር።

ሆኖም ግን መሠረታዊው ነጥብ የሳዑዲ ፖሊሶች የመፍትሄ ሃሳብ የማፍለቅ አቅም ደካማ መሆን፣ የእነርሱም ግራ የሆነ ሴቶችን የማግለል ሱስም፣ ወይም የሰው ህይወትን ከመጤፍ አለመቁጠርም አይደለም። መሠረታዊው ነጥብ ይህ ክስተት በአሁኑ ሙስሊሞች ዘንድ ያለውን አስከፊ የሞራል ዝቅጠት አሳይ ምሳሌ መሆኑ ነው።

[30] ቅዱስ ቁርአን 33፡ 59





ይህ ክስተት ሌሎች ክስተቶችን ያጀበ ነበር። ክስተቶቹ በርካታ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ከሞቱበት የ9/11 ጥቃት ጀምሮ ዕይታ ከተቸራቸው አነስተኞቹ ድረስ የዘለቁ ናቸው። እምብዛም ያልታወቀ ነገር ግን በአስቃቂነቱ ከላይ ከተጠቀሰው ጋር የሚስተካከል አንድ ክስተት እንደ ምሳሌ እንይ። በዲሴምበር 13 1996 አብዱልከሪም አል ነቀሽባንዲ የተባለ ግለሰብ በቀጣሪው ልዑል ሱልጣን ቢን ሳዑድ ቢን አብዱልዓዚዝ ላይ የድግምት ሥራ ሰርተሃል ተብሎ እንዲገደል ይወሰንበታል። በአብዱልከሪም ላይ የቀረበው ማስረጃ የተወሰኑ የቅዱስ ቁርአን አንቀፆች የተጻፉበት ክታብ በሥራ ጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ መገኘቱ ነው። እንደ አብዱልከሪም ገለጻ ከቀናተኛና ከፉ መንፈስ እንዲጠብቀው ክታቡን የሰጡት እናቱ ኃበሩ። ነገር ግን ተከሳሽ ዘንድ የተገኘው ይህ ክታብና በቤቱ የተገኙ ሌሎች የሱፊዝም መፅሐፍት እንደመናፍቅ አስቆጥረውት (አዕማል ቢዳዕያ ወ ሽርኪያ) በመንግስቱ አስገድለውታል።

በኢስላም ስም በተደጋጋሚ አስነዋሪ ኢፍትሃዊ ተግባር የሚፈፅሙ ሰዎች ሙስሊሞችን ቆም ብለው የምር እንዲያስቡ ሊያደርጓቸው ይገባል። ከአንድ አማኝ ሙስሊም ዕይታ አንጻር፣ አላህ ከሙስሊሞች ጋር የገባው ቃል ኪዳን የምር ያስጨንቀኛል። ቅዱስ ቁርአን ሙስሊሞች ፍትህ መዘርጋት እና እውነት መመስከር ሲሳናቸው አላህ (ሱ.ወ) በሌሎች ህዝቦች እንደሚተካቸው በሚያስጠነቅቁ አንቀፆች የተሞላ ነው። ሙስሊሞች በአላህ ላይ የጣልነው ውለታ የለም። በቅዱስ ቁርአን የተገለጹት ለሙስሊሞች የተሰጠው ቃል ኪዳን ችሮታ አይደለም። ቅድመ ሁኔታ አለበት። ቅዱስ ቁርአን በተደጋጋሚ በአፅዕኖት እንደሚናገረው ቃል ኪዳኑን አለመጠጣት በአላህ ለመጥፎ ነገሮችና ውጤቶቻቸው መተው ያመጣል።[31]

[31] ቅዱስ ቁርአን 9፡ 67፤ 59፡ 19

ላለፉት 20 ዓመታት በኢስላም ስም የተፈጸሙትን ፍጹም አስቀያሚ ተግባራትን የተመለከተና በእነዚህ ተግባራት የማይጨነቅ ሙስሊም ካለ አውቆ የተኛ አሲያ የታበየ መሆን አለበት። በዚህ ማዕቀፍ በአብዱልከሪም አል ነቀሽባንዲ ላይ የተፈፀመው ግድያ ሆነ የ9/11 የአሸባሪዎች ጥቃት ሁልጊዜ በተወሰኑ ሙስሊሙን በማይወክሉ ጽንፈኞች ላይ እያላከኩ መቀጠል አይቻልም። ከሶሾሎጂ አንፃር አስነዋሪ የረብሻ ተግባራት አብዛኛው በማህበረሰብ ውስጥ ሲብላሉ የቆዩ አደገኛ አስተሳሰቦች ውጤቶች ናቸው። ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጤነኛ ያልሆኑ ባህሪያትን የማህበረሰቡ የተገፉ ነቀዞች መገለጫዎች ናቸው እያሉ በቸልተኝነት ማለፍ አደገኛም የዋህነትም ጭምር ነው። በነጭና ጥቁር ለመናገር፣ ሰዎች ድንገት አንድ ቀን ከእንቅልፋቸው ተነስተው የሽብር ተግባር አይፈጽሙም ወይም የ"ጥንቆላ" ስራ ሰርተሃል ብለው ሰዎችን አይገድሉም። እንደነዚህ አይነት ተግባራት የማህበረሰቡን የሞራል እና ሥነ ምግባር ዕሴቶችን የሚያፈረሱና የሚያሟሙ የረጅም ጊዜ አስተምሮቶች ውጤቶች ናቸው። በተለይ ነገረ መለኮታዊ አወቃቀርን በተመለከተ እንደዚህ አይነቶችን የጭካኔ ተግባራትን ለመፈጸም ሆነ የማህበረሰቡን የነቀፌታ ምላሽ ለመሸበብ ለረጅም ጊዜ የቆየ ጠመቃና ማላመድ ይጠይቃል። እንዲህ አይነት ጠመቃና ልምምድ ሙስሊሞች በሃይማኖታቸው ስም ለሚፈጸሙ አስነዋሪ ተግባራት በሚሰጡት የዝምታ ምላሽ ማየት ይቻላል።

ኢስላም በተደጋጋሚ ለሚንጸባረቁ ኢሞራላዊ ባህሪያት ሽፋን ሆኖ ሲቀርብ ሲመለከት፣ ለሃይማኖቱ ቀናኢ የሆነ ሙስሊም ሁሉ ሊያሳስበው የሚገባ ነገር ነው።

በብዙ መንገድ የመጪው ጊዜ የሚዘወረው በታሪክ ነው። እያንዳንዱ በኢስላም ስም የሚፈጸም ህገ ወጥ ተግባር ታሪካዊ አሳይነት አለው።





እያንዳንዱ ታሪካዊ አሳይ በበኩሉ ህጋዊ ክብደት ሊኖረው ይችላል። በመሆኑም በመጪው ጊዜ የኢስላም ትርጉም ላይ ተፅዕኖ ያስድራል ።

በእኔ ዕይታ ሙስሊም ምሁራን በኢስላም ስም በሚፈፀሙ በተለያዩ ታሪካዊ አሳዩዎች ላይ መሳተፍ እና ሃይማኖታዊ አረዳድ ላይ ወሳኝ ሚና መጫወት አለባቸው። ከዚህ ሃላፊነት መሸሽና አሳዛኝ በሆነ ተለማማጭ ምላሽ ለማለፍ መሞከር ኢስላምን እንደ መክዳት፣ መልካምን የማስፋፋት እና ሕሱምን የማቀብ ግዴታን እንደመጣስ ይቆጠራል።

## ከ "ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው" ባሻገር

ከመስከረም 11 /2001 ጥቃት በኋላ እኔ የማውቃቸው ሙስሊሞች በሙሉ "ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው፣ የእነዚህ ሽብርተኞች ተግባር እውነተኛውን ኢስላም አይወክልም" የሚለው ሀረግ በፍቅር ሲደጋግሙት ተመልክቻለሁ። ሆኖም በተወሰኑ ምክንያቶች በዚህ "ቅዱስ ሃረግ" የማገኘው እርካታ እየቀነሰ መጥቷል።

እዚህ ጋር በአንድ ነገር ላይ ግልፅ ልሁን፣ በመሠረታዊነት ኢስላማዊ ያማህበረሰብ ፍትህ ግዴታዎች ከተሟሉ ኢስላማዊ አስተምህሮቶች ለግለሰቦች ሆነ በዓለም ደረጃ የሰላም ጎዳናን ያሳያሉ። ሆኖም ግን "ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው" የሚለውን ሀረግ ወደ ቅዱስነት መለወጥ በውስጡ አሳዛኝ ተለማማጭነትን ይዟል። በውስጣችን ያሉትን አክራሪዎች የመገዳደር ወኔ ያጡ ሙስሊም አፈ ቀላጤዎች ይህን ሐረግ ሲደጋግሙት መስማት አሳዛኝ እንደሆነው ሁሉ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት (ጆርጅ ድብልይ ዩ ቡሽ) የአፍጋኒስታንንና ኢራቅ ሙስሊሞችን በቦምብ ሊደበድብ እየተዘጋጀ፣ የፍልስጤማውያንን አስቃቂ ጭቆና እየደገፈ እስልምናን እንደ "የሰላም ሃይማኖትነቱ" እንደሚያከብር መስማት በጣም ያሳምማል። በሁሉቱም አተያይ "ኢስላም የሰላም

ሃይማኖት ነው" ለጆሮዬ ተለማማጭነትና ንፍቅና የሞላበት ቀፎ ሀረግ እየሆነ መጥቷል።

እንደ ሙስሊምነታችን በማህበረሰባችን ውስጥ ካሉ ችግሮች ጋር የመጋፈጥ ግዴታ አለብን። ሁሉም ህብረተሰብ ውብና የተከበሩ አባላት እንዳሉት ሁሉ አስቀያሚዎችና አክራሪዎች አሉት። ሙስሊሞችም ሰዎች ናቸው፤ ከሌሎች ሰዎች የሚለዩበት ቅንጣት ነገር የለም። እኛም ጻድቆች እና ኃጥአች፣ ጽንፈኞችና አርአያዎች አሉን። በዚህ የታሪክ ወቅት የኛ ዋና ሀላፊነት በማህበረሰባችን፣ በቤተሰቦቻችን እና በልቦቻችን ውስጥ ካሉ ጨቋኞችና አክራሪዎች ጋር መጋፈጥ ነው። "ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው" በሚለው ቀላል ንግግር ውስጥ መደበቅ ችግሮቻችንን አይፈታልንም።

ይህን "ቅዱስ" መፈክር የማልወድበት ሌላ ምክንያት አለኝ። የ"ጦርነት" እውነተኛ ምንነት እንደጠፋን ሁሉ የ"ሰላም" እውነተኛ ምንነትም ጠፍቶናል። በርካቶች ሰላም የጦርነት አለመኖር ወይም ቢያንስ የግጭት አለመኖር እንደሆነ እያሰቡ ነው። ሆኖም ግን እንደ ተራማጅ ሙስሊምነታችን በኢእኩልነት እና ኢፍትሃዊነት የተጎነጎነ ስርዓትን ረብሻ በሌለበት መንገድ የመታገል ግዴታችንን መርሳት የለብንም። ይህ ከጊዜያችን ትልቁ ተግዳሮቶች መካከል ዋናው ነው- ከሰውነት የተዋረዱ እና የተጨቆኑ ህዝቦች የሚያደርጉትን ትግል መደገፍና ትግላቸውን ከረብሻ በፀዳ መልኩ እንዲያደርጉ ማበረታታት።

የ"ሰላም" ፅንሰ ሃሳብ ገዥ ሃይሎች የሚያራምዱትን ኢፍትሃዊ ሁነት ለመጠበቅ እና ለማስጠበቅ እንደሚጠቀሙበት ይታወቃል። ይህን በእስራኤልና በቀድሞዋ ዘረኛዋ ደቡብ አፍሪካ ተመልክተናል። ተራማጅ የሆነ ሙስሊም ሁሉ ይህን ግልብ ሰላምን በመንቀፍ በፍትህ ላይ የቆመ ሰላምን ሕያው ለማድረግ መታገል አለበት። በቅዱስነታቸው ዳላይ ላማ የተስተጋባው ሰላም እንዲህ አይነቱ ነው። የሰላም ኖቤል ሽልማታቸውን





ሲቀበሉ ባደረጉት ንግግር እንዲህ ብለው ነበር- "ሰላም በጦርነት አልባ አረዳዱ በብርድ ሆነ በረሃብ እየረገፈ ላለው ምንም ዋጋ የለውም... ሰላም ዘላቂ የምትሆነው የሰዎች ሰብአዊ መብት ሲከበር፣ የተራቡ ሰዎች ምግብ እንዲያገኙ ሲደረግ እና ግለሰቦችና ህዝቦች ነጻ ሲሆኑ ነው።"

"ኢስላም የሰላም ሃይማኖት ነው" የሚለው ንግግር ያለንበትን ተጨባጭ ደቋሽ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና መንፈሳዊ ኢፍትሃዊነትን እንዳንታገል እንቅፋት እንዲሆንብን ልንፈቅድለት አይገባም። ይህን ማድረግ ሰብአዊነትን መሸጥ፣ ፍትህ እንድንሰራና መልካምንነትና ውበትን (ኢህሳንን) ህያው እንድናደርግ የተጣለብንን መለኮታዊ ኃላፊነት መተው ነው። እንደ ሙስሊምነታችን ሁላችንም የምንኖርበትና የምንተነፍስበትን ከአላህ ለሰዎች የተሰጠው ክብር ዕውን የሚሆንበት ፍትሃዊና ሁሉን አቀፍ ማህበረሰብ ለማምጣት ማለም አለብን። ይህ ክብር አንዱ ለሌላው የሚሰጠው አይደለም፤ እያንዳንዱ ግለሰብ ያለው ነገር ነው። ምክንያቱም ቅዱስ ቁርአን እንደሚናገረው መለኮታዊው መንፈስ በሁላችንም ውስጥ ነውና የተነፋው።

## ቀጣይ ሥራዎች

1. የነቢዩ መንፈስ
2. አምላክና ሰው፡ ሃይማኖት እና ሂውማኒዝም
3. አምላክ፡ ሃይማኖት እና ሳይንስ
4. ኢቮሉሽን ወይስ አዳም እና ሔዋን

## ከመጽሐፉ የተወሰደ

የበኑ ቁረይዛ ግድያ በሁሉም መስክ ካሉ ምሁራን ዘንድ የተለያዩ ምላሾች ቢያስወረውር የሚጠበቅ ነው ፡፡ በአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ቁጭ ብሎ የሚፅፈው ሄንሪክ ግሬትዝ (Heinrich Graetz) የኢስላምን ውስጣዊ ፀረ አይሁድነት የሚያሳይ ነው በሚል ክስተቱን እጅግ አረመኔ በሆነ መልኩ ሲገልፀው "የዘር ማጥፋትም ነው" ብሏል ፡፡ ኤስ ደብልዩ ባርሰን Social and Religious History of the Jews በሚለው መፅሐፉ ከልክ ባለፈ መልኩ በኑ ቁረይዛዎችን ከመሳዳ አመፀኞች ጋር አቆራኝቷቸዋል ፡፡ (የመሳዳ አመፀኞች በ72 ለሮማውያን እጅ አንሰጥም ብለው በጅምላ ራሳቸውን ያጠፉ ናቸው ፡፡) በሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ የነበሩ ኦሬንታሊስቶ ይህ ክስተት ኢስላም ረብሸኛና ኋላ ቀር ሃይማኖት እንደሆነ ያስረግጣል ብለዋል ፡፡ ፍራንሲስኮ ገብሬይሊ Muhammed and the Conquest of Islam በሚለው መጽሐፉ ሙሐመድ በበኑ ቁርይዛዎች ላይ የመፈፀው ድርጊት "እንደ ክርስትያንነታችንና ሠላጤነታችን ፣ 'ይህ አምላክ ወይም ይህ የአምላክ ገፅታ የእኛ አይደለም' ብለን አስረግጠን መናገር አለብን" ብሏል ፡፡

*****

በጂሐድ ርዕስ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን አራት ሙስሊሞች በተጋባዥነት የቀረቡበት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ብትመለከቱ ፣ "ጂሐድ ምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ አራት የተለያዩ ምላሾች ልታደምጡ ትችላላችሁ ፡፡ አንደኛው ጂሐድ ማለት መልካም ሕይወት ለመምራት ፣ በመደበኛነት ለመስገድና ለመጾም ፣ መልካም የትዳር ጓደኛ እና የቤተሰብ አባል ለመሆን የሚደረግ ጥረት ነው ሊል ይችላል ፡፡ ሌላው የኢስላምን መልዕክት ለሰዎች ለማዳረስ ጠንክሮ መሥራት ሲል ሶስተኛው በፍልስጤም ፣ ካሽሚር ፣ ቼቼኒያ ወይም በኮሶቮ እየተጨቆኑና በደል እየደረሰባቸው ያሉትን ሙስሊሞች ነፃ ለማውጣት መታገል ነው የሚል ይሆናል ፡፡ የመጨረሻው ተናጋሪ ፣ እንደ ኦሳማ ቢን ላዲን ለመሰለው ፣ በሙስሊም ዓለም ውስጥ ያሉትን መንግሥታት መገልበጥና አሜሪካን ማጥቃት ሊሆን ይችላል ፡፡

ጂሐድ ከአንድ በላይ ትርጉሞች ካሉት እንዴት ነው በትርጉሞቹ ላይ ግንዛቤ የሚወሰድባቸው? የትኛው አረዳድ ትክክል ነው? የትኛው(ኞቹ) ትርጉም(ሞች) በጎ መሻሻሎችንና ለውጦችን ይደግፋል(ሉ)? የትኞቹስ አክራሪነትንና ሽብርተኝነት ይሁንታ ለማስጠት ጥቅም ላይ ይውላሉ?...

*****

አክራሪነትን እና ምንነቱን ለመረዳት ከባለሙያዎች ግጭት ከሞላበት አስተያየትና የዐረብ መንግዶች ንግግር ቅርሚያ የዘለለና የተሻገረ ዓለም አቀፋዊ ምልከታ ይጠይቃል ፡፡ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሙስሊሞች የሚሰጡት አስተያየት ምንድን ነው? ምን ያህል ሙስሊሞች ዕንፈኛ አመለካከት አላቸው? ተስፋቸውና ስጋታቸው ምንድን ናቸው? ግንባር ቀደም ፍላጎታቸውስ? ምን ያደንቃሉ? ምንስ ይኮንናሉ?

ዋጋው ብር 22.00